3198

# የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች አነዳደፍና ይዘቶች አደረጃጀት ብቃት ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ - ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት /ቴሲስ/

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን
በማስተማር ሥነ ዘዴ ትምህርት
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

በ

ዩሴፍ ደመቀ ውበት

ግንቦት/1989 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች አነዳደፍና ይዘቶች አደረጃጀት ብቃት ትንተና

በ
ዮሴፍ ደመቀ ውበት
ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ማውጫ

ገጽ


ምስጋና
አጠቃሎ
ምዕራፍ 1
መግቢያ

1.1 የጥናቱ መነሻ ችግር ............................................. 1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ............................................. 2
1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ............................................. 3
1.4 የጥናቱ ወሰን ............................................. 4
1.5 ያጋጠሙ ችግሮች ............................................. 4
1.6 የሙያ ቃላት ተግባራዊ ማብራሪያ ............................................. 4

ምዕራፍ 2
የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1 የቋንቋ መርሀ - ትምህርት ምንነት ............................................. 6
2.2 የመርሀ - ትምህርት አዘገጃጀት ............................................. 8

2.2.1 የፍላጎት አሰሳ ............................................. 9
2.2.2 የትምህርት ዓላማዎች አመሠራረት ............................................. 10

2.2.2.1 የትምህርት ዓላማዎች ጠቀሜታ ............................................. 12
2.2.2.2 ዓላማን በመንደፍ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች.. 14
2.2.2.3 የዓላማ አነዳደፍ መርሆዎች ............................................. 17
2.2.2.4 የትምህርት ዓላማ ምንጮች ............................................. 21

2.2.2.4.1 ተማሪው እንደ መረጃ ምንጭ... 21
2.2.2.4.2 በዘመኑ ያለው ማኅበረሰብ እንደ መረጃ ምንጭ............................................. 22
2.2.2.4.3 የትምህርት ባለሞያዎች እንደ መረጃ ምንጭ............................................. 23
2.2.2.4.4 የትምህርት ፍልስምና እንደ መረጃ ምንጭ............................................. 23

2.2.3 የይዘት አመራረጥ ............................................. 24

2.2.3.1 የይዘት መምረጫ መስፈርቶች ............................................. 25
2.2.3.2 የይዘት አደረጃጀት ............................................. 28
2.2.3.3 የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች............................................. 29

ገጽ

2.2.3.3.1 ተከታታይነት ............................ 29
2.2.3.3.2 ተሰጣጣቂነት............................ 30
2.2.3.3.3 ውህደት................................ 31

ምዕራፍ 3
የጥናቱ ዘዴ

3.1 የመረጃ ምንጮች ........................................................ 33
3.2 የናሙና አወሳሰድ ........................................................ 34
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ............................................. 34
3.4 የመጠይቆችና የቃል መጠይቆች አዘገጃጀት ............................... 36
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ................................................... 37

ምዕራፍ 4
የመረጃና የጥናቱ ውጤት ትንተና

4.1 የመረጃ ትንተና ............................................................ 39

4.1.1 በቫሌትና ሪኒ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችና ሙከራዎች አከፋፈል ስልት፣ ከመምህራንና በሥርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና.................................... 39

4.1.1.1 በክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማግኘት ለመምህራን ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና 39
4.1.1.2 በክፍል ሁለት በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን አነዳደፍ ብቃት ለመለካት የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና........... 40
4.1.1.3 በክፍል ሶስት በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችን አደረጃጀት ብቃት ለመለካት የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ...................... 58

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ.................................................. 78

4.2.1 በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎች አነዳደፍ ብቃት........................................ 78
4.2.2 በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች አደረጃጀት ብቃት.................................................. 79

ምዕራፍ 5
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሣቦች

5.1 ማጠቃለያ ................................................................ 81
5.2 የመፍትሔ ሃሣቦች ........................................................ 83

አምደ ቃላት.................................................................... 85
ማስታወሻዎች .................................................................. 86
ዋቢ መጻሕፍት ................................................................ 87

ምሥጋና

እንዳስጀመረ አስጨርሶ ለዚህ ፍጻሜ ያበቃኝ የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ስሙ የተረከ ይሁን::

ከጥናቱ መነሻ እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለመሰልቸትና ትርፍ ጊዜያቸውን ሳይቆጥቡ ረቂቅ ሥራዬን ደጋግመው በማንበብና ተገቢውን መልክ በማስያዝ ከፍተኛ ድጋፍ ሳደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ ይልማ ከበደ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሥርዓተ - ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዶክተር ማረው ዘውዴ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ - ጽሑፍ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት አቶ ሰለሞን ተሰማ፣ በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት አቶ ጌታቸው እንዳላማው ጥናቱን ከዳር ለማድረስ ሳደረጉልኝ እገዛና ትብብር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

በትምህርት ላይ በቀየሁበትቸው አራት ዓመታት ቤተሰብ የማስተዳደርን፣ በተለይም ልጆች የማሣደግን ከባድ ኃላፊነት ከመሸከም በተጨማሪ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፏ ፈጽሞ ሳልተለየኝ ውድ ባለቤቶ ለወይዘሮ መዓዛ ከበደ የተለየ ምስጋና አቀርባለሁ::

ትምህርቴን ስከታተል ዘወትር የሞራል ድጋፍ ያደረጉልኝ ልጆቼ ሰመሀር ዩሴፍ እና እዩኤል ዩሴፍ፣ እንዲሁም የማቴሪያልና የሞራል ድጋፋቸው ያልተለየኝ መምህር ንጉሴ ወርቁ እና መምህርት ከበቡሽ ደመቀ ከነቤተሰቦቻቸው፣ አቶ ኃይለማርያም ህሩይ፣ አቶ ንጋቱ ረታ፣ ወ/ሮ አያልነሽ ማሞ፣የድህረ ምረቃ አማርኛን የማስተማር ሥነ - ዘዴ ተማሪዎች፣ የእንጦጦ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ አስተዳደርና ስማቸው ያልተጠቀሰ ጓደኞቼ በሙሉ ባለውለታዬ ናቸው::

የዚህ ጥናት ውጤት አስተማማኝ እንዲሆን ጊዜያቸውን ሰውተው መጠይቶችን በመሙላትና ቃለ መጠይቆችን በመመለስ የተባበሩኝ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በሥርዓተ - ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎችን ከልብ አመሰግናለሁ::

ዩሴፍ ደመቀ ውበት

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የታለመው በ1984 ዓ.ም. ታትሞ ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት የአላማ አነዳደፍና የይዘት አደረጃጀት ብቃት ለመገምገም ነው:: ግምገማውንም ለማካሄድ በአዲስ አበባ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ10ኛ ክፍል ለያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቆች የተበተኑ ሲሆን፣ በሥርአተ ትምዓርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ደግሞ ቃለ መጠይቅ ቀርቧል:: ከነዚህም ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ባሻገር ቫሌትና ሪኒ (19.72) የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችንና ሙከራዎችን ለማደራጀት የተጠቀሙበት ያጠሠራር ሥልት በሥራ ላይ ውሏል::

ከላይ ከተመለከቱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኘውን ውጤት በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር ዓላማዎች የአላማ አነዳደፍ መርሆዎችን ተከትለው አለመነደፋቸውን አመልክቷል:: ዝርዝር ዓላማዎቹ ግልጽነት የሚጐላቸው ከመሆኑ ባሻገር መግለጫ መንገዳቸውን የያዙ አይደሉም:: በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተም አቀራረብ የላቸውም::

በሌላ በኩል ደግሞ የይዘቶቹን አደረጃጀት ብቃት በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ የይዘቶቹ አደረጃጀት ችግር ያለበት መሆኑን አመልክቷል:: ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከአጠቃላይ ወደተናጠል ወዘተ... የሚያስኬደውን ያደረጃጀት ስልት ተከተለው አለመደራጀታቸውን ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል::

# የሠንጠረዥ ዝርዝር


ሠንጠረዥ ገጽ

1. ስለ መምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ.................. 39
2. ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.................... 40
3. ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ................................... 41
4. ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.................. 43
5. ዓላማቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.................... 44
6. ዓላማቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.................................. 45
7. ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ የተነደፉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ............................................................................ 46
8. በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎች አቀራረብና የሚያስነሱት ጥያቄ መግለጫ...................................................................... 47
9. ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.................................. 48
10. በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን አደረጃጀት የሚያሳይ መግለጫ ........ 49
11. በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን አደረጃጀት የሚያሳይ ግራፍ............ 51
12. ዓላማቹ የሚያሳዩትን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ........................................................................... 52

13. ዓላማዎቹ ተማሪዎችእንዲያሳዩ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ መጻፋቸውን ወይም አለመፋቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.......................................................................... 53
14. ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ መልስ መግለጫ.................................... 55
15. በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር ዓላማዎች ትኩረት የሚያሳይ መግለጫ.......... 56
16. በመርሀ - ትምህርት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ..................... 58
17. በመርሀ - ትምህርት ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ........................................................... 59
18. በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.......................................................................... 61
19. ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ............................................................ 62
20. በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የትምህርቱን ዝርዝር ዓላማዎች በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.................... 63
21. በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችን አደረጃጀት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ.............................................................................. 64
22. የይዘቶች አደረጃጀት ተከታታይነት የተጠበቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ......... 69
23. የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት መጠበቅ ወይም አለመጠበቁን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ...................................... 70
24. የይዘቶቹን ቅደም ተከተል ለዋውጠው ቢያስተምሩ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ

መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ
ምላሽ መግለጫ.................................................................. 71

25. የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መለዋወጥ በትምህርት ሂደት
ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር የማችልበትን
ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ............ 72

26. ይዘቶቹን የሚያስተምሯቸው እንዴት እንደሆነ ለመለየት
ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ................................... 73

27. መምህራን በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ የራሳቸውን ቅደም
ተከተል በማውጣት ይዘቶቹን ለማስተማር የወሰኑበትን ምክንያት
እንዲገልጹ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ...................... 74

28. ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ካሉ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር
መደጋገፋቸውንና አለመደጋገፋቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ
የተሰጠ ምላሽ መግለጫ............................................................ 75

29. ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚሰጡ ከየትኛቹ የትምህርት
ዓይነቶች ጋር መደጋገፍን እንደሚያሳዩ ለይቶ በማመልከት
የተሰጠ ምላሽ መግለጫ............................................................ 76

# ምዕራፍ አንድ

# መ ግ ቢ ያ

## 1.1 የጥናቱ መነሻ ችግር

የመጀመሪያው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከተዘጋጀ ከ1947-48 ጀምሮ /ቤንደር 1975:372/ አማርኛ በትምህርት ዓይነትነትም ሆነ በማስተማሪያ ቋንቋነት ሲሰጥና ሲያገለግል ቢቆይም ዝግጅቱ ብቃት ይጎድለው እነደነበር ጥናቶች ያመለክታሉ:: ለምሣሌ በ1959 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትንና የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተናን ለመገምገም የተሰበሰበው ጉባዔ ያስተላለፈው ውሣኔ እንደሚያመለክተው፣ ጉባዔው እስከተካሄደበት ጊዜ ድረስ የነበረው የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከመርሀ-ትምህርትነት ይልቅ ወደ መምህራን መምሪያነት ያዘነበለ፣ የማስተማሪያ መጽሐፍቱና መርሀ-ትምህርቱ የማይገናኙ ከመሆናቸው ባሻገር በተለይ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተዘረዘሩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀታቸው የተዛባ ነው:: ተስፋዬ ሸዋዬ «የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን የማስተማሪያ ዓላማዎች ትንታኔ» በሚል ርዕስ በ1982 ዓ.ም. ባቀረቡት ጽሑፍ እንዳመለከቱት እስከ 1970 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት ውስጥ የነበሩት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርቶች ባግባቡ ያልተነደፉና በግልጽ የተቀመጠ ዓላማም የሌላቸው ናቸው::

በሌላ በኩል ደግሞ አያሌው አስፋው (1986) የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ይዘቶች በማጥናት፣ ይዘቶቹ የብቃት ማነስና የአደረጃጀት ጉድለት እንደሚታይባቸው ያመለከቱ ሲሆን አንተነህ አወቀም (1974) በበኩላቸው የሥነ-ጽሑፍ ይዘት በሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የተሰጠውን ትኩረት በመመርመር ለሥነ-ጽሑፍ ትምህርት አነስተኛ ትኩረት መስጠቱን፣ የይዘት አደረጃጀት ችግርና የብቃት ጉለቶች መኖሩን ገልጸዋል:: ጌታቸው አዱኛም (1985) ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ምንባቦችን የብቃት ደረጃ ለመለካት ባደረገት ጥናት ምንባቦቹ ተነባቢነት የሌላቸውና ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸው ቀረቤታ መካከለኛ መሆኑን ያመለከቱ ከመሆኑ ባሻገር በተለይ ይህ ጥናት የተመሰረተበትን መርሀ-ትምህርት ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያለውን ግንኙነት በመለካት የደረሱበት ውጤት ሁለቱ ዝግጅቶች ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ያሳያል::

ቀደም ሲል ካየናቸው ጥናቶች የተገኙ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ከ1984 ዓ.ም. በፊት የነበሩት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርቶችም ሆኑ በ1984 ዓ.ም. ታትሞ በ1985 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለው የአሥረኛ ክፍል የአማር ኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከመማሪያ መጽሐፍቱ ጋር ስምረት የሌላቸው፣ የአላማ አነዳደፍ ጉድለትና የይዘት ብቃት ማነስ የሚታይባቸው ናቸው::

ከላይ እንደተጠቀሰው ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት በአዲስ መርሀ-ትምህርት በመመራት ላይ ይገኛል:: ከእነዚህም መርሀ-ትምህርቶች አንዱ የሆነው የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት በክፍሉ ደረጃ በሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካኝነት ከዳር ይደርሳሉ ተብለው የቀረቡ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን፣ ዓላማዎቹንም ከዳር ለማድረስ የተመረጡ ይዘቶችን፣ የክፍል ውስጥ የማስተማር መማር ሥራ ተግባራትንና ግምገማዎችን ይዟል:: ሆኖም ዝርዝር ዓላማዎቹ የአነዳደፍ ጉድለት፣ ይዘቶቹ ደግሞ የአደረጃጀት ብቃት ችግር እንደሚታይባቸው የዚህ ጥናት አቅራቢ አሥረኛ ክፍል ሲያስተምርና ጥናቱንም ለማካሄድ የሙከራ ጥናት ሲያደርግ የችግሩን መኖር ተገንዝቧል:: ቀደም ሲል የዚህን ችግር መኖር ለማወቅም ሆነ መፍትሄ ለመሻት የተደረገ ጥናት ባለመኖሩ የችግሩን ዓይነትና ችግሩም ሊከሰት የቻለበትን ምክንያት ለይቶ ለማመልከትና መፍትሄውንም ለመጠቆም ይህን ጥናት ማካሄዱ አስፈልጓል::

### 1.2 የጥናቱ ዓላማ

መርሀ-ትምህርት ለቋንቋ ማስተማር - መማር ሂደት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: መርሀ-ትምህርት ለይዘት ምርጫና አደረጃጀት፣ ለዓላማዎች ተግባራዊነት፣ ለትምህርት ቁሳቁሶች ዝግጅትና ለግምገማ መሠረት በመሆን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል::

አንድ መርሀ-ትምህርት ከሚይዛቸው ክፍሎች ውስጥ ዓላማና ይዘት ዋነኞቹ በመሆናቸው ተግባራዊ ለመሆን የሚችሉ ዓላማዎችን መንደፍና በዓላማዎቹም መሠረት ይዘቶችን መርጦ የታሰበውን ግብ ከዳር ለማድረስ እንዲያስችሉ ከይዘት አደረጃጀት መርሆዎች አኳያ ማደራጀት ተገቢ ነው:: ከዚህ አንጻር በ1984 ዓ.ም. ታትሞ በ1985 ዓ.ም. በሥራ ላይ የዋለው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ያቀፋቸው ዝርዝር ዓላማዎች ሲነደፉና ይዘቶቹም ተመርጠው ሲደራጁ ምን ያህል ጥንቃቄ እንደተደረገና ብቃታቸውም እንደተጠበቀ መመርመሩ አስፈላጊ ነው:: የዚህም ጥናት ዋና ዓላማ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር

ዓላማዎችና ይዘቶች ከዓላማ አነዳደፍና ከይዘት አደረጃጀት መርሆዎች አኳያ በመመርመር ችግሮቹን ለይቶ ማመልከትና የበኩሉን የመፍትሔ ሃሣብ መጠቆም ነው:: ጥናቱም በሂደት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል::

1. በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር ዓላማዎች ከዓላማ አነዳደፍ መርሆዎች አኳያ የተቀረጹ ናቸው?

   1.1 ዝርዝር ዓላማዎቹ የክፍል ደረጃውን በመመጠን ተማሪች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታና በተመደበው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ?

   1.2 ዝርዝር ዓላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትና መገለጫ መንገዱን የያዙ ናቸው?

   1.3 ዝርዝር ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አነዳደፍ አላቸው?

   1.4 ዝርዝር ዓላማዎቹ ግልጽ ሆነው ቀርበዋል?

2. በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የአደረጃጀት ብቃት ይታይባቸዋል?

   2.1 የይዘቶቹ አደረጃጀት ምን ይመስላል?

   2.2 የይዘቶቹ ተከታታይነት ተጠብቋል?

   2.3 የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል?

   2.4 የይዘቶቹ ውህደት ተጠብቋል?

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

በቋንቋ ማስተማር መማር ሂደት የመርሀ-ትምህርት አስፈላጊነት አጠያያቂ ባለመሆኑ ለበለጠ ጥራትና መሻሻል በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ሊተች፣ ሊተነተንና ሊመዘን ይገባል:: ይህም የማስተማር - መማሩን ሂደት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም ይህ ጥናት በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን

አነዳደፍና ይዘቶችን አደረጃጀት ችግር፣ የችግሩንም ምክንያቶች ለይቶ በማመልከትና የመፍትሄ ሀሣቦችን በመጠቆም ረገድ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል::

1. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለሚያዘጋጁ የትምህርት ባለሙያዎች የበኩሉን ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፤
2. የትምህርት መሣሪያዎቹን ለሚጠቀሙባቸው መምህራን ጠቃሚ ሃሣብ ይሰጣል፤
3. ለተቀሩት የክፍል ደረጃዎች የተዘጋጁትን የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርቶች ለማጥናት መነሻ ሊሆን ይችላል፤
4. ወደፊት በዚህ መስክ በስፋት ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ አካሎች የበኩሉን መነሻ መረጃ በመስጠት ሊያገለግል ይችላል::

### 1.4 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች በመተንተን ላይ የተመሠረተ ነው:: በጥናቱ ውስጥ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች የዓላማ አነዳደፍና የይዘት አደረጃጀት ብቃት ናቸው:: ጥናቱ በዝርዝር ዓላማዎቹና ይዘቶቹ አስፈላጊነት፣ ብቃትና ደረጃ መጣኝነት ላይ አያተኩርም:: በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች ከዓላማ አነዳደፍና ከይዘት አደረጃጀት መርሆዎች አኳያ መነደፋቸውንና መደራጀታቸውን መመርመር የጥናቱ አብይ የትኩረት ነጥብ ነው::

**1.5** ለጥናቱ የመረጃ ምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ ከተመረጡት ውስጥ በሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት መርሀ-ትምህርቱን ያዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ይገኙበታል:: ይሁንና ግን መርሀ-ትምህርቱን ካዘጋጁትም ሆነ በማሻሻል እገዛ ካደረገት መካከል በጡረታና በሌላ ምክንያት ሥራቸውን የለቀቁ የትምህርት ባለሞያዎች በተለያዩ ምክንያቶች ለጥናቱ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው በጥናቱ ሂደት የታየ ችግር ነበር::

### 1.6 የሙያ ቃላት ተግባራዊ ማብራሪያ

በዚህ ንዑስ ክፍል በጥናቱ ውስጥ ተደጋግመው በሥራ ላይ የዋሉት ቁልፍ ቃላትና ሐረጋት በጥናቱ ውስጥ ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንጻር ማብራሪያ ይሰጣል::

<u>መርሀ-ትምህርት</u> - ከትምህርት ክንውን በኋላ ተማሪዎች ያሳያሉ ተብሎ የታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት፣ ለባሕሪ ለውጡ ምክንያት የሆነውን የትምህርት ይዘት፣ በክፍል ውስጥ መከናወን ያለበትን የተግባር ዓይነትና ቅደም ተከተሉን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ቁሳቁሶችን፣ እንዲሁም የመመዘኛ መንገዶችን የሚገልጽ ሰነድ ነው::

<u>የትምህርት ግቦች</u> - ለተግባራዊነታቸው ረጅም ጊዜን የሚጠይቁ የትምህርት ዕቅዶች አጠቃላይ መግለጫ ናቸው::

<u>የትምህርት ዓላማዎች</u> - ለተግባራዊነታቸው አጭር ጊዜን የሚሹና ተማሪዎች ባስተሳሰባቸው፣ በስሜታቸውና በተግባራቸው የሚያሳዩትን ለውጥ የሚያመለክቱ ውሱን መግለጫዎች ናቸው::

<u>ይ ዘ ት</u> - ተማሪዎች እንዲማሩ የሚፈለገውን የቋንቋ እውቀት፣ ክሂል፣ አመለካከትና እሴት ያሳያል::

<u>ተከታታይነት</u> - አንድ ይዘት በተከታታይ ጊዜያት ውስጥ በመከሰት በልምምድ ላይ ሊውል የሚችልበትን ቀጥተኛ ሁኔታ ያመለክታል::

<u>ተለጣጣቂነት</u> - እያንዳንዱ ተከታታይ ትምህርት በቀዳሚው ላይ ተመሥርቶና ስፋትና ጥልቀትአግኝቶ በመደራጀት በመስኩ የዳበረ እውቀት ለማስጨበጥ የሚችልበት መንገድ እንዲመቻች በመጠየቅ ይዘቶች ከቅርብ ወደሩቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጠል የሚጓዙበትን አቅጣጫ የሚቀይስ ያደረጃጀት ሥልት ነው::

<u>ውህደት</u> - በአንድ የትምህርት መስክ የተገኘ እውነትና መመሪያ በሌላ የትምህርት መስክ ካለው እውነትና መመሪያ ጋር ተዛማጅነትና ተደጋጋፊነት እንዲኖረው ማድረግን የሚጠይቅ የአደረጃጀት ሥልት ነው::

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1 የቋንቋ መርሀ ትምህርት ምንነት

ስለ መርሀ - ትምህርት ምንነት ማብራሪያ ለመስጠት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከመርሀ - ትምህርት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮች መግለጽ ያስፈልጋል:: የመርሀ - ትምህርትን ዝግጅትና አገልግሎት በተመለከተ በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ሥርአተ-ትምህርትን የሚመለከቱ ጉዳዮች መነሳታቸው የማይቀር በመሆኑና በእነዚህም አጋጣሚዎች ሁለቱን በመለዋወጥ የሚጠቀሙ በመኖራቸው በቅድሚያ የሁለቱን ልዩነት ማሳየት ተገቢ ነው::

ሥርአተ - ትምህርት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ምንነቱን በማስመልከት ከተለያዩ ፀሐፍት የቀረቡ ብያኔዎችን አንድ በአንድ መመልከቱ ይጠቅማል:: ሥርዓተ - ትምህርት ወደ ሕፃናት፣ ወደ ወላጆቻቸው፣ ወደ መምህሮቻቸው ሕይወት ዘልቆ የሚገባ ከመሆኑም በሻገር ሕይወታቸውንም ከከበበው ማንኛውም ነገር የተዋቀረ ነው በማለት የሰው ልጅ የኑሮ ገጠመኝ ነፀብራቅ መሆኑን የሚገልጹልን ካስዌልና ሌሎች ናቸው /1950:173/:: ካስዌልና ሌሎች ሥርዓተ - ትምህርት በእንቅስቃሴ ውስጥ ያለ አካባቢ ነው በማለት ተለዋዋጭነቱንም ያስረዳሉ:: ይህም ሥርዓተ - ትምህርት በአንድ አካባቢ ውስጥ የሚካሄድ ማንኛውም ነገር ነው ወደሚል መደምደሚያ ያደርሰናል:: ጠቅለል ባለ መልኩ የነካስዌል ማብራሪያ ሥርዓተ - ትምህርት የትምህርት ዓይነቶች ስብስብ ወይም በተወሰነ ተከታታይነት የተደራጀ የጥናት መስክ ነው በማለት ሥርዓተ - ትምህርትን በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ዓይነቶች ድምር በማድረግ እስትሬች፣ ክራቨስኪና ለርነር፣ ድሪስልና ማርኩስ የሰጡትን ገለጻ አበበ በቀለ /1986: 40/ በመጥቀስ ካቀረቡት ሃሣብ ጋር የሚስማማ አይደለም:

አለን /1984:61/፣ ዱቢንና ኦልስቲን/ 1986:34-35/ ኑናን /1988:3/ በበኩላቸው ሥርዓተ - ትምህርት የትምህርት ፕሮግራም ለመንደፍ ጠቀሜታ ያላቸውን ፍልስፍናዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ አስተዳደራዊና ብሔራዊ ሁኔታዎችን የሚመለከት፣ ስለአጠቃላዩ የትምህርት ግብ ሰፊ ትንተና ያካተተ አጠቃላይ ጽንሰ ሃሣብ መሆኑን ያስረዳሉ:: በነሱም ገለጻ መሠረት ሥርዓተ - ትምህርት የአንድ ሀገር የትምህርት

ፍልስፍና የሚገለጽበት፣ ማኅበረሰባዊ ፍላጎት የሚንፀባረቅበትና አገር አቀፍ ትምህርታዊ ጉዳዮች የሚካተቱበት ያጠቃላይ ግቦች መግለጫ መዝገብ ነው::

በአጠቃላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከሚሰነዘሩ የሥርዓተ-ትምህርት ብያኔዎች ለመረዳት የሚቻለው የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ስራ ተግባራትን መድረሻው ያደረገ፣ በጥናትና በዝግጅት ላይ የተመሠረተ የትምህርት ኘሮግራም ምሥረታን የሚመለከት መሆኑን ነው:: የትምህርት ፕሮግራም ምስረታም የትምህርት መሣሪያዎችን ዝግጅትና የአፈጻጸም ውሣኔን እንደሚመለከት ሒርስት /1980:9-18/ ያስረዳሉ:: ከትምህርት መሣሪያዎች ዝግጅት ውስጥ አንዱ ደግሞ የመርሀ-ትምህርት ዝግጅት ነው:: ታዲያ መርሀ-ትምህርት ምንድነው?

መርሀ-ትምህርት የሥርዓተ - ትምህርት አነስተኛ ክፍል ሆኖ በሥርዓተ - ትምህርት ውስጥ የተጠቃለሉትን የትምህርት ፍልስፍናዎች ውሱን ዓላማ ባላቸው ትምህርቶች ውስጥ የሚተረጉም፣ ጥልቀት ያለውና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የማስተማር - መማር ክንውን ማመልከቻና ከሥርዓተ - ትምህርቱ ውስጥ የሚወጣ ነው በሚለው ውሣኔ ብዙዎች ይስማማሉ /ውልኪንስ 1981: ያልደን 1983: ስተርን 1983 ዱቢንና ኦልስቲን 1986/::

በሌላ በኩል ደግሞ ብሬን /1984:47/: ካንድሊን/1984: 30-31/፣ ፕራብሁ /1987:89/ እንደሚያስረዱት መርሀ - ትምህርት የይዘት ውሣኔንና አደረጃጀትን የሚመለከት፣ በግቦች ተግባራዊነት ላይ የሚያተኩር፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ለማዘጋጀት መርህ ሆኖ የሚያገለግል፣ ባጠቃላይም በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ትምህርት ለማገዝ የተደራጀ የትምህርት መሣሪያ ነው:: በእነሱም አገላለጽ መርሀ - ትምህርት ይዘቶች ተመርጠው ባግባቡ የሚደራጁበት፣ በክፍል ወስጥ እንዲከናወን በተፈለገው ተግባር ላይ የሚያተኩርና የትምህርቱን ሂደት አቅጣጫ በማመልከት የሚመራ መዝገብ ነው::

መርሀ - ትምህርትን በይዘት ነጋሪነት በመመደብ ሀቺንስንና ዋተርስ /1987:80/፣ ካኒንግዎርዝ /1984:22/ በበኩላቸው ተማሪች ስለሚማሩት ነገር የሚነግር የትምህርት ይዘቶች ሥርዓታዊ መግለጫ መዝገብ ነው በማለት ያስረዳሉ:: ከእነሱም ገለጻ እንደምንረዳው መርሀ - ትምህርት ይዘቶችን በመምረጥ መጥኖ፣ አመቻችቶና አስማምቶ የሚይዝ የትምህርት መሣሪያ ነው::

በአጠቃላይ መርሀ - ትምህርት ከትምህርት ክንውን በኋላ ተማሪች ያሳያሉ ተብሎ የሚታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት፣ ለባሕሪ ለውጡ ምክንያት የሆነውን የትምህርት ይዘት፣ በክፍል ውስጥ መከናወን ያለበትን የተግባር ዓይነትና ቅደም ተከተሉን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ቁሳቁሶችን፣ እንዲሁም የመመዘኛ መንገዶችን የሚገልጽ ትምህርታዊ ሰነድ ነው ማለት ይቻላል::

ከፍ ሲል ለማመልከት እንደተሞከረው መርሀ - ትምህርትን በሚመለከት በተለያዩ ጸሐፍት የተሰጡት ትንታኔዎች ያቀራረብ እንጂ የመሠረተ ሃሣብ ልዩነት አይታይባቸውም:: ልዩነት የሚያሣዩት መርሀ-ትምህርት ሲያካትታቸው በሚገባው ክፍሎች ላይ ነው:: ስተርን /1984/ የእንግሊዝኛን ቋንቋ አጠቃላይ መርሀ-ትምህርት በተመለከተ በተካሄደው ስንፖዚየም ላይ ይህ ልዩነት እንደተንፀባረቀ ይገልጻሉ:: ከሲንፖዚየሙም ተሣታፊዎች ውስጥ ዊዶውስንና ብሩምፊት ሥነ-ዘዴ የመርሀ-ትምህርት አካል መሆን የለበትም የሚል አቋም የነበራቸው ሲሆን፣ ጋንድሊንና ብሬን ደግሞ ከይዘትና ዓላማ በተጨማሪ የትምህርት ልምድንና ግምገማን መያዝ አለበት የሚል እምነት ሲያራምዱ እንደነበር ስተርን ያስረዳሉ:: በሌላም በኩል ሻው ግምገማ ስለ መርሀ-ትምህርት ያለን ግንዛቤ አካል መሆን የለበትም የሚል አቋም እንዳላቸው ማረው /1992:3/ ይገልጻሉ:: የዚህም ምርምር ጽሑፍ ዋነኛ የትኩረት ነጥብ የዓላማ አነዳደፍና የይዘት አደረጃጀት ብቃት ሲሆን በዚሁ ላይ ትኩረት ይሰጣል::

## 2.2 የመርሀ - ትምህርት አዘገጃጀት

መርሀ - ትምህርት ስናዘጋጅ መሠረት በመሆን የሚያገለግሉ መመሪያዎች እንዳሉ በመጀመሪያ ያሳወቁት ታይለር /1950/ ሲሆኑ በኋላም ታባ /1962/ በማስፋፋት ተጠቅመውበታል:: በሳቸውም ገለጻ መሠረት ፍላጎትን ማሰስ፣ አላማን መመሥረት፣ ይዘትንና የትምህርት ልምዶችን መርጦ ማደራጀት፣ የሚገመገመውን መለየት መርሀ - ትምህርትን ስናዘጋጅ መሠረት ሆነው የሚያገለግሉን መመሪዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ:: ከጥናቱም የትኩረት አቅጣጫ አኳያ ቀጥሎ ፍላጎትን ማሰስ፣ አላማን መመሥረትና ይዘትን መርጦ ማደራጀት በሚሉት የመርሀ - ትምህርት ዝግጅት መሥረቶች ላይ ትንታኔ ይሰጣል::

### 2.2.1 የፍላጎት አሰሳ

የፍላጎት አሰሳ ለመርሀ - ትምህርት ዝግጅት አስፈላጊ የሆነ ተቀዳሚ ዝግጅት ከመሆኑ ባሻገር ትምህርታዊ ዓላማንም ለመመሥረት የመሠረት ድንጋይ በመሆን ያገለግላል::

ኦሊቫ /1988:242/ እንደሚያስረዱት፣ ምንም እንኳ በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ቢችልም ሰፋ አድርገን ካየነው የፍላጎት አሰሳ የሥርዓተ - ትምህርት ባለሞያዎች የአንድን ትምህርታዊ ፕሮግራም ተፈላጊነት ለመለየት የሚጠቀሙበት የአሠራር ዘዴ ነው::

በሌላም በኩል ሪችትሪች /1972:72/ እንደሚያስረዱት የፍላጎት አሰሳ የተማሪችን የመማር አቋም በመለየት ከተፈጥሯዊ (physical) አእምሮአዊና (intellectual) ስሜታዊ (emotional) ሁኔታዎቻቸው ጋር ለማጣጣም፣ ሥነ-ትምህርታዊ ዓላማዎችን ለመመሥረትና ተገቢ የሆኑ የማስተማሪያ መጽሐፍትን ለማዘጋጀት የሚያስችል ጠቃሚ መረጃን ያስገኛል:: ዱቢንና አልስቲን /1986:5/ በፍላጎት አሰሳ የሚሰበሰበው መረጃ ለቀጣዮቹ ጥያቄዎች መልስ በመሻት የመርሀ-ትምህርትን ዝግጅት ሂደት እንደሚመራ ያስረዳሉ:: ጥያቄዎቹም ተማሪዎቹ እነማን ናቸው? ፕሮግራሙ ለምን አስፈለገ? ተግባራዊ የሚሆነውስ የትና እንዴት ነው? የሚሉት ሲሆኑ ለጥያቄዎቹም የሚሰጠው መልስ ትምህርታዊ ፖሊሲንና ዓላማን ለመንደፍ እንደሚያገለግል ይገልጻሉ::

«ተማሪው እንግሊዝኛን መማር ለምን ፈለገ?» የሚለው ጥያቄ ለመርሀ - ትምህርት ዝግጅት መነሻ መሆን ያለበት ሲሆን ይህም ጥያቄ በፍላጎት አሰሳ አማካኝነት መልስ ሊያስኝ ይገባል በማለት በመርሀ - ትምህርት ዝግጅት ወቅት የፍላጎት አሰሳን ቀዳሚነትና አስፈላጊነት ሀቺንሰንና ዋተርስ /1987:53/ ይገልጻሉ::

ታባም በበኩላቸው /1962:347/ የፍላጎት አሰሳ ዓላማ አዲስ ትኩረትንና ሃሣብን ማፍለቅ ሲሆን ይህም ሂደት ቀደም ሲል የነበረውን መረጃ በአሰሳ ከተገኘው ጋር በማገናኘት ለተፈለገው ተግባር ለመጠቀም መቻልን እንደሚመለከት ያስረዳሉ:: በፍላጎት አሰሳ መረጃን መሰብሰብ ያለብን ተማሪው ቋንቋውን ለምን ሊማረው እንደፈለገ የሚመለከተውን ብቻ መሆን እንደሌለበት ጥናቶች ይጠቁማሉ:: ይህንንም

በተመለከተ ኑናን /1988:14/ እንደሚያስረዱት፣ ማኅበረሰቡ ስለቋንቋው ትምህርት ያለውን ግምት፣ መርሀ - ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ ያሉ እንቅፋቶችን፣ ለመርሀ - ትምህርቱ ተግባራዊነት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መኖርና አለመኖራቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎችም ሊሰበሰቡ ይገባል::

በሌላም በኩል የመርሀ - ትምህርትን ዝግጅት በፍላጎት አሰሳ የመጀመርን አስፈላጊነት የሚቃወሙ መኖራቸውን ኑናን /1988:20-21/ ይገልጻሉ:: እንደሳቸውም ገለጻ ከተቃዋሚዎቹ ውስጥ አንዳንዶቹ የፍላጎት አሰሳ፣ መምህራን በክፍል ውስጥ ያላቸውን የወሳኝነት ሚና የሚነጥቅ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ የመርሀ - ትምህርት ውሣኔ የሚካሄደው በመስኩ ሙያተኞች እንጂ በተማሪዎች አይደለም በማለት ተቃውሟቸውን ያሰማሉ:: ተማሪዎችም በበኩላቸው አንድ መምህር ወይም የትምህርት ተቋም ትምህርትን አስመልክቶ የተማሪውን አስተያየት ከጠየቀ ምን እንደሚሰራ እንደማያውቅ ያሳያል በማለት የፍላጎት አሰሳን ጠቃሚነት እንደሚያጣጥሉት ኑናን ያስረዳሉ::

ይሁንና ግን የፍላጎት አሰሳ በአንድ የትምህርት ሂደት ውስጥ የሚታቀፉ ተማሪዎችን በተመለከተ መረጃ በማስገኘት፣ የዝግጅቱን አስፈላጊነትና ለዝግጅቱም ማኅበረሰቡ ያለውን ግምት በመጠቆም፣ ዝግጅቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዱ እንቅፋቶችና ለዝግጅቱ ተግባራዊነት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መኖርና አለመኖር በመለየት ተጨባጭና ተግባራዊ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የመርሀ - ትምህርትን ዝግጅት በፍላጎት አሰሳ የመጀመሩ አስፈላጊነት የሚጠየይቅ አይመስልም::

### 2.2.2 የትምህርት ዓላማዎች አመሠራረት

ቀደም ሲል እንደተመለከተው መረጃዎች በፍላጎት አሰሳ አማካኝነት ከተሰበሰቡ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የትምህርቱን ዓላማ መመሥረት ይሆናል:: ይህንንም በተመለከተ ዱቢንና ኦልስቲን /1986:23/ እንደሚያስረዱት በፍላጎት አሰሳ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የፕሮግራም ነዳፊው ተግባር የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን የትምህርቱን ዓላማ መንደፍ ነው::

ስለ ትምህርት ዓላማዎች ምንነት፣ ጠቀሜታም ሆነ አመሠራረት ትንታኔ ለመስጠት ከትምህርት ዓላማዎች ጋር ተዛማጅነትና መመሳሰል ስላላቸው አንዳንድ ነጥቦች ማብራሪያ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል::

የተለያዩ ሰዎች አንድ የትምህርት ተቋም በሥራው ሊደርስበት የሚፈልገውን ውጤት የተለያየ ስያሜ ሲሰጡት ይታያሉ:: አንዳንድ ፀሐፊዎች እቅድ (aims)፣ መድረሻ (ends)፣ ውጤት (out come)፣ ግብ (goals)፣ ተልዕኮ (purpose) ዓላማ (objective) ይሉታል:: ሌሎች ደግሞ ግብ፣ ተልዕኮና እቅድ ለሚሉት ተመሳሳይ ፍቺ በመስጠት ሰፋት ያለውን ጠቀሜታ ለመግለጽ ሲጠቀሙበት ዓላማን ደግሞ በጣም ውሱን የሆነ የባሕሪ ዓይነትን ለማመልከት ሲያውሉት ይታያሉ:: አበበ በቀለ /1974:25-26/ ብሉም፣ ግላሰር፣ ፖፋም፣ ሜጀር፣ ታይለር፣ ጋኝ የመሳሰሉትን ፀሐፊዎች በመጥቀስ ስያሜዎቹን በመለዋወጥ አንዱን ከሌላው ሳያበላልጡ የሚጠቀሙባቸው መሆኑን ያስረዳሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ ጉድላድንና አምንስ ግብ ወይም ተልእኮ የሚለውን ግባቸው ሩቅ የሆነ ትምህርታዊ መድረሻዎችን ለማመልከት ሲጠቀሙ፣ ዓላማ የሚለውን ደግሞ ተማሪው በሚቀርብለት ትምህርት አማካኝነት የሚያሳየውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመሰየም እንደሚገለገሉበት ይገልጻሉ::

ባጠቃላይ ትምህርታዊ እቅዶች (aims) ለመምራት፣ ለማዘዝና ውሣኔ ለመስጠት፣ አቅጣጫን ለማስተካከልና ለማመልከት የሚያገለግሉ፣ ለተግባራዊነታቸው ሰፊ ጊዜን የሚጠይቁ አጠቃላይ መግለጫዎች ሲሆኑ ትምህርታዊ ዓላማዎች (objective) ደግሞ ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ተግባራትን የያዙ፣ ግልጽነት ያላቸው፣ ተግባራዊ ሊሆኑና ሊመዘኑ የሚችሉ፣ ለተግባራዊነታቸውም አጭር ጊዜን የሚሹ ውሱን መግለጫዎች ናቸው::

የትምህርት ዓላማ በአንድ የትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ለውጥ ያሳያሉ ተብሎ የሚገመትበትን መንገድ ወይም ሁኔታ የሚያሳይ መሆኑን ብሉም /1956:26ን ይገልጻሉ:: በብሉም አገላለጽ ዓላማ ተማሪዎች ባስተሳሰባቸው፣ በስሜታቸውና በተግባራቸው ያሳያሉ ተብሎ የሚገመተውን ለውጥ የሚያሳይ መግለጫ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ኦሊቫ /1988:378/ የማስተማር - መማር ዓላማ ከማስተማር - መማር ግብ የሚመነጭ፣ ሊመዘንና ሊታይ በሚችል መልኩ የተቀረፀ፣ እያንዳንዱ ተማሪ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሊያደርገው የሚገባው ክንውን መግለጫ ነው በማለት ያስረዳሉ::

ፔይኔ /1974:11/ በበኩላቸው የትምህርትን ዓላማ እንደሚከተለው ሊገልጹ ይሞክራሉ::

> ሰፋ አድርገን ከተመለከትነው ትምህርታዊ ዓላማ ተማሪዎች እንዲያሳዩ የሚፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት የሚያሳይ መግለጫ ነው:: ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ዓላማ የእሴት ግምገማን የሚወክል፣ የትምህርት ምክንያታዊነትን የሚያመለክት ነው:: በሌላም በኩል ዓላማ ሞዴል የሚሆን ሃሣብ የያዘ፣ ማንኛውም ተማሪ ተግባራዊ ሊያደርገው የሚገባ ነው::

በዓላማ ምንነትና አጠቃቀም ላይ በመስኩ ባለሞያዎች መካከል አንድ ዓይነት ግንዛቤ ባለመኖሩ ሁሉንም የሚያረካ ብያኔ መስጠቱ ያስቸግራል:: ይሁንና ግን ታይለር /1949:5-6/ ስለ ትምህርት በሰጡት ገለጻ ላይ በመመሥረት ትምህርታዊ ዓላማን እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል::

> አንድ ኅብረተሰብ ልጆቹ ስለ ጥሩ ሕይወት ከተገነዘቡት የሚመነጨውን እሴት ለመረዳትና ለመምረጥ ይችሉ ዘንድ በትምህርት ቤት አማካኝነት እንዲለምዱ የሚፈለ ገውን የባሕሪ ዓይነት የሚመለከት መግለጫ ነው::

ከላይ ከቀረበው ገለጻ በመነሳት የትምህርት ዓላማዎች ጠቀሜታ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢነት አለው::

### 2.2.2.1 የትምህርት ዓላማዎች ጠቀሜታ

በማስተማር - መማር ሂደት ውስጥ ዓላማ ዋነኛውና የመጀመሪያው ነጥብ ነው:: ዓላማ ወደምንፈልገው ግብ ለመድረስ እንችል ዘንድ አቅጣጫን በማመልከት የመሪነት ተግባር ያከናውናል::

ታባ /1962:197-199/ ትምህርታዊ ዓላማዎች የሚከተሉት ጥቅሞች እንዳሏቸው ያስረዳሉ::

1. የትምህርት ዓላማ የትምህርት ልምድን ለመምረጥ፣ ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንዳለብን ለመወሰን መስፈርት ሆኖ ያገለግላል፤

2. የትምህርት ዓላማ እንዲዳብር የተፈለገውንም የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ይገልጻል፤
3. የትምህርት ዓላማ በትምህርት ክፍሎች መሀል ያለውን መደጋገፍ ያጎለብታል፤
4. የትምህርት ዓላማ ከትምህርት በኋላ ይገኛል ተብሎ የታሰበው ውጤት መገኘትና አለመገኘቱን ለመገምገም ያስችላል::

በሌላ በኩል ደግሞ ፔይኔና /1974:70/ አሊሻ /1988:378/ እንደሚያስረዱት አንድ መምህር ዓላማን በመመሥረት ለማስተማር ከቻለ:

1. በክፍል ውስጥ ምን ዓይነት ባሕሪን ሊያሳድግ እንደሚሞክር ያውቃል፣
2. ለተማሪዎች ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ በግልጽ ለመንገር ይችላል፣
3. ምን ማስተማር፣ እንዴት ማስተማርና መገምገም እንዳለበት በቀላሉ ይረዳል::

ጌጅ /1979:36/ ታይለርን ጠቅሰው አንድን የትምህርት ሂደት በዓላማ መሪነት ለማከናወን አለመቻል በትምህርቱ እንቅስቃሴ ላይ የሚያስከትለውን ችግር በማመልከት የዓላማን ጥቅም እንደሚያስረዱት፣ መምህራን ዓላማን ካልመሰረቱ ተማሪዎች በሚማሩት ይዘት ሊሰሩ በሚገባቸው ነገር ላይ ትተው በይዘቱ ላይ ብቻ ማተኮር ይጀምራሉ:: ምንድነው የምንሰራው? የሚለው አብይ ነጥብ ከተዘነጋ ደግሞ ተማሪዎች ለትምህርት የቀረቡላቸውን ይዘቶች መሸምደድ ከነሱ የሚጠበቅ ተግባር አድርገው መገመት ይጀምራሉ:: መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት በዓላማ አማካኝነት ካልመሩ ተማሪዎች መምህሮቻቸው ስለሚያስተምሯቸው ነገርና ከእነሱም ስለሚጠበቀው ተግባር የተሳሳተ ግንዛቤ ይኖራቸዋል::

ባጠቃላይ የትምህርት ዓላማ ይዘትንና የትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተልን ለመምረጥ፣ የማስተማር መማሩን ሂደት ውጤማነት ለመገምገምና ተማሪዎች የማስተማር መማሩን ሂደት እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ይችሉ ዘንድ እንቅስቃሴያቸውን ለማቀናጀት የሚያስችል መሠረት በመሆን ከፍተኛ ጠቀሜታን የሚሰጥ ከመሆኑ ባሻገር የማስተማር መማሩን ሂደት ለማሻሻልም ያግዛል::

### 2.2.2.2. ዓላማን በመንደፍ ሂደት የሚጋጥሙ ችግሮች

አንድን ትምህርታዊ ተግባር በተፈለገው መንገድና ሁኔታ ከዳር ለማድረስ እቅድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የዓላማ በግልጽና በማያሻማ መንገድ ሊቀመጥ መቻል ለውጤታማ ተግባራዊነቱ ወሳኝነት አለው:: ይህንንም በማስመልከት ሜጀር /1984:5-6/ እንደሚያስረዱት በግልጽ የተቀመጠ ዓላማ ከሌለ ለማስተማር - መማሩ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን፣ ይዘቶችንና ሥነ-ዘዴን ለመምረጥ ወይም ለማዘጋጀት የሚያስችል መሠረት አይኖርም:: በሌላም በኩል አንድ የተፈለገ ትምህርታዊ ውጤት መገኘት ወይም አለመገኘቱን ለመመዘን የሚያስችሉ ሙከራዎችን ለማዘጋጀት የሚቻለው የማስተማር - መማሩ ሂደት ውጤት በግልጽ ሊቀመጥ ሲችል ነው:: በግልጽ የተቀመጠ ዓላማ ተማሪዎች ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችላቸውን እንቅስቃሴ ለማቀናጀት የሚረዳም ዘዴ በማመልከት ጥቅም ይሰጣል:: በርካታ ልምዶች እንደሚያመለክቱት በግልጽ የተቀመጠ ዓላማን በአእምሯ ቸው የያዙ ተማሪዎች መድረስ የሚገባቸው ቦታ ለመድረስ ይችሉ ዘንድ በበኩላቸው ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ተግባር ለመወሰን ይቀላቸዋል::

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የማስተማሪያ መሣሪያዎች ምርጫና የይዘቶች አደረጃጀት የሚመራው፣ የማስተማር - መማሩን ሂደት ለመንደፍና ውጤቱን ለመገምገም የሚቻለው በዓላማ አማካኝነት በመሆኑ የዓላማ አነዳደፍ ልዩ ትኩረትን ይሻል:: ይሁንና ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው የዓላማ አነዳደፍ ችግሮች የሚታይበት ሂደት ነው::

ዓላማን በተመለከተ ዋነኛውና የመጀመሪያው ችግር የሚመነጨው በዓላማ አጠቃቀም በተለይም ደግሞ በባሕሪያዊ ዓላማዎች አስፈላጊነት ላይ ነው:: ባሕሪያዊ ዓላማዎች በርካታ የመስኩ ምሁራን /ቫሌትና ዲስክ 1972:17፣ ጌጅ 1979:38-39፣ ሜጀር 1984:21፣ ኦሊቫ 1988፣39/ እንደሚያስረዱት ከተማሪው የሚጠበቀውን ውስጉን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ፣ የጥራት ደረጃው የሚለካበትን መስፈርት በመያዝ ግልጽ በሆነ መንገድ ተነድፈው ይቀርባሉ::

ዝርዝር ባሕሪያዊ ዓላማዎችን በተመለከተ የሚነሳው አንዱ ችግር ግልጽነት በሚለው ነጥብ ላይ ነው:: ጌጅ እንደሚያስረዱት ዛሆሪክ፣ ድሬሴልና የመሳሰሉት

ፀሐፊዎች ዓላማዎች ግልጽ ሆነው መቅረብ አለባቸው በሚለው ነጥብ ላይ አይስማሙም:: እንደነሱም አቋም ውስብስብ ዓላማዎች ተማሪዎች በሕብረተሰቡ ወደተመረጠው ግብ ለመድረስ የሚረዳቸውን የራሳቸውን መንገድ እንዲሹ ያስችላቸዋል:: ይሁንና ጌጅ /1979:41/ አጠቃላይ ሁኔታን የሚያመለክቱ ቃላትን ውሱን ተግባርን በሚያመለክቱ ቃላት በመተካት ዓላማውን ጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ያስገነዝባሉ::

ባሕሪያዊ ዓላማዎችን በተመለከተ የቀረቡ ዝርዝር የተቃውሞ ኃሣቦችና ጌጅ /1979:50/ ለቀረበው የተቃውሞ ሃሣብ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ትችትና ምላሽ በሚል ርዕስ ቀርቧል::

| | |
|---|---|
| ትችት:- | ጥሩ መምህራን ባሕሪያዊ ዓላማዎችን አይጠቀሙም |
| ምላሽ:- | ጥሩ መምህራን ባሕሪያዊ ዓላማዎችን ቢጠቀሙ የበለጠ ጥሩ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩን ለማመን የሚያስችሉ ምክንያቶች አሉ:: |
| ትችት:- | አነስተኛ ጥቅም ያላቸው ዓላማዎች ብቻ ናቸው በባሕሪያዊ መንገድ ሊነደፉ የሚችሉት: |
| ምላሽ:- | አስፈላጊው ችሎታ ከታከለበት ጠቃሚ ዓላማዎች በባሕሪያዊ መንገድ ሊነደፉ ይችላሉ |
| ትችት:- | የተወሰኑ የይዘት ዓይነቶች ለባሕሪያዊ ዓላማዎች አመችነት የላቸውም |
| ምላሽ:- | በተግባር እንደታየው የመስኩ ባለሙያዎችና መምህራን በባሕሪያዊ መንገድ ሊገለጹ የሚችሉ መስፈርቶችን ይጠቀማሉ |
| ትችት:- | ባሕሪያዊ ዓላማዎች የሰውን ስብዕና የሚነኩ ከመሆናቸው ባሻገር ሜካኒካዊ ናቸው |
| ምላሽ:- | ተማሪዎች መማር ስለሚገባቸው ነገር ማሳወቅ ሰብአዊነት ነው |
| ትችት:- | በትምህርት ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ያልተገመቱ የባሕሪ ለውጥ ዓይነቶች የበለጠ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ |
| ምላሽ:- | ይህ የሚሆንበት ሁኔታ ከተፈጠረ የባሕሪያቱ መከሰት ጥሩ ነው፣ ይሁንና ግን ተማሪው ያሳያል ተብሎ የተገመተውን ሊመዘን የሚችል ባሕሪ ተፈላጊነት አይቀንሰውም:: |

በሌላ በኩል ደግሞ የዓላማ አነዳደፍ ችግር የሚመነጨው ዓላማዎች ሲገለጹ የሚችሉባቸው በርካታ መንገዶች መኖራቸው ነው፡፡ ሁሉም ያገላለጽ መንገድ የተፈለገውን ነገር እኩል ለማሳየት የሚችል አይሆንም፡፡ አንዳንድ ዓላማዎች ከመምህሩ አኳያ ተጽፈው ይታያሉ፡፡ ለምሣሌ «የአረፍተ ነገር አመሰራረትን ማስተማር» የሚለው የመምህሩን ተግባር የሚገልጽ ነው፡፡ የመምህሩ ተግባር ደግሞ የትምህርቱ ሂደት የሚያስገኘው ውጤት ሳይሆን ተማሪውን ወደተፈለገው ውጤት የሚያደርስ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሌሎች ዓላማዎች ደግሞ ከትምህርቱ ይዘት አኳያ ተነድፈው ያታያሉ፡፡ ለምሣሌ «የአማርኛ አናባቢዎች» የሚለው ከትምህርቱ ሂደት ውጤት አኳያ የተጻፈ አይደለም፡፡ እንደዚህ ያለውን በተመለከተ ብሉም /1971:22/ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ «ይዘት በራሱ ፍቺ አልባ ነው ... ስለይዘት የሚያወሱ አረፍተ ነገሮች ተማሪው ከትምህርቱ በኋላ ያሳያል ተብሎ የሚታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ለማሳየት የማይችሉ በመሆናቸው ለማስተማር - መማሩና ለግምገማው ሂደት ሙሉ ናሙናዎች በመሆን አያገለግሉም፡፡»

በዓላማ አነዳደፍ ሂደት ችግር የሚያስከትለው ሌላው ሁኔታ የቃላት አጠቃቀም ነው፡፡ ይህም ችግር የሚመጣው ደግሞ የአጠቃላይና የውሱን ዓላማዎችን ባሕሪያት ለይቶ ካለማወቅ ነው፡፡ አጠቃላይ ዓላማዎች በአንድ ጊዜ ብዙ ነገር የሚያመለክቱና ለተግባራዊነታቸውም በርካታ ክንውኖችን የሚጠይቁ ከመሆናቸው ባሻገር ብዙ ይዘትንና ባሕሪያትን በውስጣቸው የያዙ ሲሆን ውሱን ዓላማዎች ደግሞ በጥቂት ክንውኖች አማካኝነት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የተወሰኑ ባሕሪያትን ብቻ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ጋኝ /1969:241-242/ ዓላማን ስንመሰርት በቃላት አጠቃቀማችን ላይ ልናደርግ የሚገባንን ጥንቃቄ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> በርካታ ፀሐፊዎች የትምህርትን ዓላማ ሲታይ ከሚችል ተግባር አኳያ በመጻፍ ተገቢነት ላይ ተመሳሳይ አቋም ያሳያሉ . . . አንድ ተማሪ ከሚሰጠው ትምህርት በኋላ አንድ ነገር ያውቃል ወይም ይረዳል ወይም ያደንቃል የሚለው አቀራረብ የትምህርትን ሂደት ለማቀድ የሚያስችል መሠረት አይሆንም፡፡ በትምህርት ዓላማ ውስጥ አዘወትረው የሚከሰቱ እነዚህን መሰል ቃላት በዓላማ አነዳደፍ ወቅት ሊገጥመን ስለሚችል ችግር እንድናስብ መነሻ በመሆን ያገለግሉናል እንጂ የክፍል ውስጥ የማስተማር-መማርን ሂደት በሚመለከት ለሚወሰድ የውሣኔ ሃሣብ ጠቀሜታ የላቸውም፡፡

ኦሊቫም /1988:392/ በበኩላቸው ውስን ዓላማዎችን ስንመሰርት ሊመዘኑና ሊታዩ የሚችሉ ተግባራትን የሚያመለክቱ ግሶችን መጠቀም እንዳለብን ያስገነዝቡናል::

በሌላም በኩል ሜጀር /1984:20/ አንድን ዓላማ የሚያነቡ ሰዎች ዓላማው ስለሚለው ነገር የተለየ ግምት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ቃላት ስላሉ ውሱን ዓላማዎችን ስንነድፍ በቃላት አጠቃቀማችን ላይ ልናደርገው የሚገባንን ጥንቃቄ እንደሚከተለው በምሣሌ ያስረዳሉ:: ለምሣሌ «ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀምን ያውቃሉ» በሚለው ዓላማ ውስጥ የሚገኘው» . . . ያውቃሉ» የሚለው ቃል ማስታወስን፣ መፃፍን፣ ማንበብን ወይም ማድነቅን የሚያመለክት መሆኑን ወስኖ ለመናገር ያስቸግራል:: እንደነዚህ ዓይነት ቃላት ከውሱን ዓላማዎች ይልቅ አጠቃላይ ዓላማዎችን ለመንደፍ ነው የሚያገለግሉት::

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ምንም እንኳ የባሕሪያዊ ዓላማዎችን አስፈላጊነት በተመለከተ በሁሉም የመስኩ ምሁራን ዘንድ ስምምነት ባይኖርም ከሚያስገኙት ተግባራዊ ጠቀሜታ አኳያ ውሱን የባሕሪ ለውጥ በሚያመለክቱ ቃላት አማካኝነት ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት፣ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታና የጥራት ደረጃቸው የሚለካበትን መሰፈርት አካቶ ዓላማን በመንደፍ የማስተማር መማሩን እንቅስቃሴ ማከናወን ተመራጭነት አለው:: አንድን ትምህርታዊ እንቅስቃሴ ለመምራት የሚያገለግሉ ዓላማዎችን ለመንደፍ ስንነሳ ደግሞ ስለዓላማ አነዳደፍ መርሆዎች ማሰብ ይኖርብናል::

### 2.2.2.3 የዓላማ አነዳደፍ መርሆዎች

ዓላማን ለመንደፍ ወይም ለመወሰን ከመነሳታችን በፊት ዓላማውን ለመንደፍ ወይም ለመወሰን መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ መስፈርቶችን ማዘጋጀት ይገባል:: በዓላማ አነዳደፍ መርሆዎች በመመራት የሚነደፉ ዓላማዎች ሜጀር /1984:19/ እንደሚገልጹት ለአንባቢው ትምህርታዊ እቅድን ለመግለጽና ዓላማ ነዳፊው በአእምሮው የያዘውን የውጤታማ ተማሪ ምስል ለሌላው ለማሳየት ብቃት ያላቸው፣ ተማሪው ያሳያል ተብሎ የታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትና ያከናውናል ተብሎ የሚገመተውን ተግባር በግልጽ በማመልከት የተለያዩ ግምቶች እንዳይኖሩ የሚረዱ፣ ለተግባራዊነታቸውና ለግምገማው ሂደት ተገቢነት ያላቸውን በርካታ ውሣኔዎች ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው::

ዝርዝር ዓላማዎችን ስንነድፍ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነጥቦች አሟልተው እንዲገኙ ማድረግ እንደሚገባ ታባ /1962: 199-202/ ያስረዳሉ:: እነሱም:-

1. ዓላማዎቹ ተማሪው እንዲያሳየው የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትና ባሕሪውም በተግባር የሚገልጽበትን ይዘት ያካተቱ መሆን አለባቸው፤
2. ውስብስብ ዓላማዎች ተተንትነውና ተለይተው የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ሊያመለክቱ በሚችሉበት መንገድ ተጽፈው ሊቀርቡ ይገባል፤
3. ዓላማዎቹ የተለያዩ የባሕሪ ለውጦችን ሊያስገኙ የሚችሉ ይዘቶችን ለይተው ሊያመለክቱ በሚችሉበት መንገድ ሊቀረጹ ይገባል፤
4. ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አነዳደፍ ሊኖራቸው ይገባል፤
5. ዓላማዎቹ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆን አለባቸው::

በሌላ በኩል ደግሞ ትምህርታዊ ዓላማን ስንነድፍ መዘንጋት የሌለባቸው ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች መኖራቸውን ፔይኔ /1974:21-23/ ይገልጻሉ:: እነሱም ይዘትና (content) ቅርጽ (form) ናቸው:: በሳቸውም ገለጻ መሠረት ይዘት የምንነድፋቸው ዓላማዎች ከተማሪው ችሎታ ጋር የሚሄዱ፣ ክፍል ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ፣ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትና ለባሕሪ ለውጡ ምክንያት የሚሆኑትን ይዘቶች የያዙ፣ የተማሪውንና የማኅበረሰቡን ፍላጎት የሚያረኩ መሆን እንዳለባቸው የሚያመለክት ሲሆን ቅርጽ ደግሞ ዓላማዎቹ ከተማሪው የባሕሪ ለውጥ አኳያ ተግባርን በሚያሳዩ ቃላት፣ ግልጽ በሆነ መንገድ፣ የእድገት ተከታታይነታቸውን ጠብቀው፣ ውሱን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትን በመያዝ ሊጻፉ እንደሚገባ ያሳያል::

ትምህርታዊ ዓላማዎች በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አጻጻፍና አደረጃጀት ሊኖራቸው እንደሚገባ ብሉምና ሌሎች /1956:16/፣ ታባ /1962:202/፣ ቫሌትና ዲስክ /1972:29/ ፔይኔ /1974:23/ እንዲሁም ኦሊቫ /1988:381/ ይገልጻሉ:: እንደነሱም ገለጻ ማንኛውም የትምህርት ሂደት ተማሪውን ከቀላል የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ወደ ውስብስብ የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ሊያሸጋግረው የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን የትምህርቱን ሂደት በበላይነት የሚመሩትም ዓላማዎች ይህንኑ መርህ ተከትለው ሊነደፉና ሊደራጁ ይገባል::

ባሕሪያዊ ዓላማዎችን ስንነድፍ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት፣ የባሕሪ ለውጡ በተግባር ተገልጾ የሚታይበትን ሁኔታ፣ የባሕሪ ለውጡን የተቀባይነት ደረጃ የሚያሳይ መስፈርትን መያዝ እንደሚገባቸው በርካታ የመስኩ ምሁራን /ቫሌትና ዲስክ 1972/17፣ ጌጅ 1979:38-39፣ ሜጀር 1984፤21፤ አሊቫ 1988:391/ ያስረዳሉ:: ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ተማሪው ያሳያል ተብሎ የታሰበው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት በተግባር የሚገለጽበት ሁኔታ (condition) ተወስኖ በግልጽ ሊቀመጥ እንደሚገባው አሊቫ /1988:392/ እንደሚከተለው በምሣሌ ያስረዳሉ:: «ተማሪዎች የማኅበረሰቡ ፍላጎት በዝርዝር ተሰጥቷቸው ካላቸው ቅድሚያ አኳያ በቅደም ተከተል ያስቀምጧቸዋል::» በሚለው ዓላማ ውስጥ « . . . የማኅበረሰቡ ፍላጎት በዝርዝር ተሰጥቷቸው . . .» የሚለው ተማሪው ያሳያል ተብሎ የታሰበውን ባሕሪ ተግባራዊ የሚያደርግበት ሁኔታ መሆኑን አሊቫ ይገልጻሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ያከናውናሉ ተብሎ የተገመተውን ተግባር በምን ያህል የጥራት ደረጃ እንዲያከናውኑት እንደሚፈለግ የሚያመለክተው መስፈርት በሶስት መንገዶች እንደሚገለጽ ሜጀር /1984: 74-83/ ያስረዳሉ:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

1. <u>ፍጥነት</u>:- ይህ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር የሚያከናውኑበትን የጊዜ ገደብ ይመለከታል:: ምሣሌ «ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምንባብ በ10 ደቂቃ ውስጥ አንብበው መጨረስ ይችላሉ::»
2. <u>ትክክለኛነት</u>:- (accuracy) ይህ ተማሪዎቹ እንዲያከናውኑ፣ የተፈለገውን ተግባር የተቀባይነት ወይም የትክክለኛነት ደረጃ ያሳያል:: ምሣሌ «በተሰጣቸው ርእስ መሠረት ድርሰት መጻፍይችላሉ፣ ድርሰቱ ግን ከ 200 ቃላት ማነስም ሆነ ከ 250 ቃላት መብለጥ የበለትም::» በምሣሌው ውስጥ እንደተመለከተው?» . . . ድርሰቱ ግን ከ200 ቃላት ማነስም ሆነ ከ 250 ቃላት መብለጥ የለበትም::» የሚለው ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተፈለገውን ተግባር የተቀባይነት ወይም የትክክለኛነት ደረጃ የሚያሳይ መስፈርት ነው::
3. <u>ጥራት</u>:- እንደ ሜጀር /1984:83-84/ ገለጻ ፍጥነትም ሆነ ትክክለኛነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተፈለገውን ተግባር የተቀባይነት ወይም የትክክለኛነት ደረጃ ለማሳየት የሚችሉ ወሳኝ

መስፈርቶች አይደሉም። በዚህም በዓላማው ውስጥ የተገለጸው ተግባር ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ስለ ጥራት ደረጃው የሚገልጽ መግለጫ ሊኖረው ይገባዋል። ምሣሌ « . . . ተማሪዎች መደበኛና መደበኛ ስላልሆነው የትምህርት ሂደት በቃል ገለጻ መስጠት ይችላሉ። ገለጻቸው ሁለቱ የትምህርት ሂደቶች የሚለያዩበትን አምስት አበይት ባሕሪያት በመተንተን በ 10 ደቂቃ ውስጥ ይጠናቀቃል።» በምሣሌው ውስጥ እንደተገለጸው ንግግሩ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ሁለቱ የትምህርት ሂደቶች የሚለያዩበትን አምስት አበይት ባሕሪያት በመተንተን የጥራት ደረጃውን መጠበቅ አለበት።

ሜጀር /1984:43/ ትምህርታዊ ዓላማዎችን ስንመሰርት ስለ ውጫዊና (overt) ውስጣዊ (covert) ባሕሪያት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያሳስቡናል። በሳቸውም ገለጻ መሠረት ውጫዊ ባሕሪያት በቀጥታ በዓይን ሊታዩ ወይም በጆሮ ሊሰሙ የሚችሉ ሲሆን፣ ውስጣዊ ባሕሪያት ግን በቀጥታ በዓይን ሊታዩ ወይም በጆሮ ሊሰሙ የሚችሉ ባለመሆናቸው ተግባራዊነታቸውን ለመቆጣጠር የሚቻለው ተማሪው አንድ ነገር እንዲያከናውን በማድረግ ነው። በመሆኑም ውስጣዊ የባሕሪ ለውጦችን የሚመለከቱ ዓላማዎችን ስንነድፍ ተማሪው የታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ማሳየቱን ለመግለጽ የሚያስችለው ተግባር እንዲፈጽም ዓላማው የሚጠይቅ መሆን አለበት። ለምሣሌ « በጋዜጣ ላይ በትክክለኛ የሆሄያት ቅንብራቸው ያልተጻፉ ቃላትን ይለያል።» የሚለውን ዓላማ « በጋዜጣ ላይ በትክክለኛ የሆሄያት ቅንብራቸው ያልተጻፉ ቃላትን በመለየት ከሥራቸው አስምሮ ያሳያል።» በማለት ተማሪው ያሳያል ተብሎ የታሰበው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት የሚያሳይበትን መንገድ በማመልከት ዓላማውን ማስተካከል እንደሚገባ ሜጀር /1984፣43/ ያስገነዝባሉ።

ባጠቃላይ ዝርዝር ዓላማዎችን ስንነድፍ ተማሪው ያሳያል ተብሎ የሚታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት፣ ይህም የባሕሪ ለውጥ ዓይነት በተግባር ተገልጦ የሚታይበትን ሁኔታና የባሕሪ ለውጡን የተቀባይነት ደረጃ የሚያመለክት መስፈርት እንዲይዙ ማድረግ የሚገባ ከመሆኑ ባሻገር የተማሪውን እውቀትና ችሎታ በመመጠን ከሥርአተ - ትምህርቱ እቅድ (aim) ጋር ስምረት ኖሯቸው በእድገት ተከታታይነት ላይ ተመሥርተውና ለማስተማር በሚያመች መልኩ ተቀርጸው ሊቀርቡ ይገባል።

### 2.2.2.4. የትምህርት ዓላማ ምንጮች

የትምህርት ዓላማዎችን ለመወሰን ተማሪዎችን፣ ማኅበረሰቡን፣ የትምህርት ባለሙያዎችንና የትምህርት ፍልስፍናን በመጠቀሙ አስፈላጊነትና ተገቢነት ላይ በርካታ የመስኩ ምሁራን የሚስማሙ ሲሆን የእያንዳንዱንም የመረጃ ምንጭ ጠቀሜታ እንደሚከተለው ይገልጻሉ::

#### 2.2.2.4.1 ተማሪው እንደ መረጃ ምንጭ

ተማሪው ያለበት ተጨባጭ ደረጃ ተገቢውን ትምህርታዊ ዓላማ ለመንደፍ መሠረት ሆኖ እንደሚያገለግል ታይለር /1949:4-5/፣ ብሉምና ሌሎች /1956:26/፣ ፔይኔ /1974:65/፣ ታነርና ታነር /1980:142-186/፣ መክኔይል /1985:100-101/ ያስረዳሉ:: ተማሪው ቀደም ሲል ምን ተምሯል? ምንስ ለመማር ዝግጁ ነው? በትምህርታዊ እድገቱ የት ነው ያለው? ወደ ክፍል ምን ዓይነት ችሎታን ነው ይዞ የመጣው? ለሚሉት ጥያቄዎች የምንሰጠው ምላሽ ዓላማን ለመመሥረት ጥሩ የመረጃ ምንጭ ሆኖ እንደሚያገለግል ፔይኔ ይገልጻሉ::

በሌላም በኩል ታይለር እንደሚያስረዱት ትምህርት ማለት የተማሪው ባሕሪ የሚለወጥበት ሂደት ሲሆን፣ ትምህርታዊ ዓላማ ደግሞ አንድ የትምህርት ተቋም በተማሪው ውስጥ እንዲታይ የሚፈለገው የባሕሪ ለውጥ ነው:: ስለተማሪው የሚደረግ ጥናትም የትምህርት ተቋሙ በተማሪው ውስጥ እንዲታይ የሚፈለገውን ተፈላጊ ባሕሪያዊ ለውጥ ለይቶ ለማመልከት የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው:: ይህም ስለተማሪው የሚደረግ ጥናት ትምህርታዊ ዓላማን ለማስገኘት የሚችለው ተማሪውን በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ ተፈላጊነትና ተቀባይነት ካለው መለኪያ (Standard) ጋር ተነጻጽሮ ሲቀርብ ነው:: በዚህም የንጽጽር ሂደት ታይለር እንደሚገልጹት በተማሪው ወቅታዊ ሁኔታና ተቀባይነት ባለው መለኪያ መሀል ያለው ልዩነት ይለያል:: ይህም ልዩነት ወይም ክፍተት ፍላጎት ይባላል:: ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ይህን ክፍተት ለመለየት የሚደረግ ጥናት በትምህርት ቤት ውስጥ ተቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠውን ዓላማ ለመምረጥ የሚያስችል መሠረት ለመጣል እንደሚረዳ ታይለር ያስረዳሉ::

ተማሪዎችን ማጥናት ትምህርታዊ ዓላማዎችን ለመለየት የሚረዳ ጠቃሚ ሃሣብ የሚያስገኝ መሆኑን ታይለር /1976:63/ አንድ ዓላማ በውስጡ ትኩረት ሊሰጣቸው ስለሚገባው ነጥቦች በሰጡት ማብራሪያ እንደሚከተለው ያስረዳሉ::

> ትምህርታዊ ዓላማ በመጀመሪያ ተማሪው በዘመኑ ባለው ማኅበረሰብ ውስጥ ገንቢ የሆነ ሚና እንዲጫወት የሚረ ዱትንና ለራሱም ለተማሪው ጠቃሚነት ያላቸውን ነገሮች መያዝ አለበት:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለትምህርቱ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል:: በመጨረሻም ከትምህርት ተቋሙ የትምህርት ፍልስፍና ጋር ስምምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል::

ከላይ ታይለር እንዳመለከቱት ተማሪው በዘመኑ ባለው ማኀበረሰብ ውስጥ ገንቢ ሚና ለመጫወት እንዲችል የሚረዱትንና ለራሱም ጠቃሚነት ያላቸውን ነገሮች መለየት የሚቻለው ተማሪውን በማጥናት በመሆኑ ከተማሪው የሚገኝ የጥናት ውጤት ትምህርታዊ ዓላማን ለመንደፍ የሚያስችል መሠረት በመሆን እንደሚያገለግል የሚያጠያይቅ አይሆንም::

### 2.2.2.4.2 በዘመኑ ያለው ማኅበረሰብ እንደመረጃ ምንጭ

ትምህርት ቤቶች እንደሌሎቹ ማኅበረሰባዊ ተቋማት ሁሉ የሚገኙበት ኅብረተሰብ ውጤት በመሆናቸው በሚነድፏቸው ዓላማዎቻቸው ውስጥ የማኅበረሰቡን ፍላጎት፣ ምኞትና ምርጫ ማንጸባረቅ ይኖርባቸዋል:: በመሆኑም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ለማኅበረሰቡ ጠቀሜታ ይኖረው ዘንድ በዘመኑ ከትምህርት ቤት ውጭ ያለው ማኅበረሰባዊ ሕይወት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::

ታይለር /1949:17/ እንደሚያስረዱት ሕይወት በማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ትምህርታዊ ጥረቶችን ሁሉ ወሳኝ በሆነው በዚህ የሕይወት ገጽታና በጊዜው ጠቃሚነት ባላቸው ሌሎች መስኮች ላይ እንዲያተኩር በማድረግ በዘመኑ ማኅበረሰባዊ አገልግሎት ያለውን ነገር ለማስተማር ይቻል ዘንድ ማኅበረሰቡን ማጥናት ያስፈልጋል::

ብሉምና ሌሎችም /1956:26/ በበኩላቸው ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸውን ተግባራትና የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች፣ እራሳቸውን ለመግለጽ የሚያስችላቸውን እድልና የሚሰማሩበትን የሥራ መስክ

ለመለየት የሚቻለው ማኀበረሰቡን በማጥናት በመሆኑ ዓላማ ስንነድፍ በዘመኑ ያለውን ማኀነበረሰብ በመረጃ ምንጭነት መጠቀም ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ።

ባጠቃላይ በዘመኑ ያለውን ማኀበረሰባዊ ሕይወት ማጥናት ምን ማስተማር እንደሚገባን የሚጠቁመን ብቻ ሣይሆን ለተማሪዎቻችን የምናቀርበው ትምህርት ከተማሪውም ሆነ ከማኀበረሰቡ ጥቅም አኳያ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያመለክት በመሆኑ ትምህርታዊ ዓላማዎችን ለመንደፍ በዘመኑ ያለውን ማኀበረሰብ በመረጃ ምንጭነት መጠቀም ተገቢነት ይኖረዋል።

### 2.2.2.4.3 የትምህርት ባለሞያዎች እንደ መረጃ ምንጭ

የትምህርት ባለሞያዎች ሃሣብ (views) በትምህርት ዓለም ውስጥ ለብዙ ዘመናት ያለተቃዋሚ የትምህርት ዓላማን ለመወሰን ወሳኝነት ያለው የመረጃ ምንጭ በመሆን ሲሰራበት ቢኖርም ታይለር /1949: 26-27/ እንደሚያስረዱት የትምህርት ባለሞያዎች የሚነድፏቸው ዓላማዎች በጣም ቴክኒካዊ፡ ሙያዊ ወይም ከፍተኛቁጥር ላላቸው የትምህርት ቤት ተማሪዎች የማይመቹ ከመሆናቸው ባሻገር ውሱንነት ስለሌላቸው የትምህርት ባለሞያዎች ስለትምህርት መስኩ ያላቸውን ግንዛቤ በማሳየት ለአጠቃላይ ትምህርት በሚያገለግል መልኩ የሚዘጋጁ ናቸው።

ከትምህርት ባለሞያዎች የሚገኝ ሃሣብ ዓላማን ለመንደፍ ጠቃሚነት ይኖረው ዘንድ ለሚከተለው ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ እንደሚወስነው ታይለር /1949/ ያስረዳሉ። ጥያቄውም «ትምህርታችሁ በትምህርት ክፍላችሁ ባለሞያ ለመሆን የማይፈለጉ ወጣቶችን ለማስተማር ምን አስተዋጽኦ ያበረክታል?» የሚል ሲሆን እንደ ታይለር እምነት እነዚህ የትምህርት ባለሞያዎች ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ከቻሉ በሰለጠኑበት የትምህርት መስክ በቂ እውቀት ያላቸው በመሆኑና የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ለራሳቸውም ሆነ ለሥራ ባልደረቦቻቸው ያስገኘላቸውን ጥቅም ለማየት እድል የገጠማቸው በመሆኑ ዓላማን በመንደፍ ጠቃሚ የሆነ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

### 2.2.2.4.4 የትምህርት ፍልስፍና እንደ መረጃ ምንጭ

ታይለር /1949: 33-36/ እንደሚያስረዱት አንድ ትምህርት ቤት የተመሰረተበት ትምህርታዊና ማኀበራዊ ፍልስፍና ዓላማዎችን መርጦ ለማደራጀት መለያና ማጣሪያ በመሆን ያገለግላል። እንደሳቸውም ገለጻ ትምህርታዊ ፍልስፍና

የጥሩ ሕይወትና ማኅበረሰብ ተፈጥሮን የሚገልጽ ከመሆኑ ባሻገር ለተሳካና አመርቂ ለሆነ ሕይወት አስፈላጊ የሆኑ እሴቶችን በመለየት በዘመኑ ያለውን ኅብረተሰብ ቁሳዊ እሴትና ውጤት ስለሚመለከት የጥሩ ዓላማ መሠረት በመሆን ያገለግላል::

በሌላም በኩል ታይለር /1949:36/፣ ፔይኔ /1974:66/ እንደሚያስረዱት ትምህርት ቤት ከማኅበረሰቡ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እራሳቸውን በማመሳሰል ለመኖር የሚችሉ ወጣቶችን ነው ማሰልጠን ያለበት? ወይስ ማኅበረሰቡን ሊለውጡ የሚችሉ ወጣቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት ነው ያለበት? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ያለበት የሀገሪቱ የትምህርት ፍልስፍና በመሆኑና ለጥያቄዎቹም የሚሰጠው መልስ በሚነደፈው ዓላማ ላይ ተጽእኖ ስላለው የአንድ ሀገር የትምህርት ፍልስፍና ዓላማን ለመንደፍ መሠረት ሊሆን የሚችል መረጃን በመስጠት አገልግሎት ይሰጣል::

በአጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎችን ለመወሰን እነዚህን የመረጃ ምንጮች በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ ሂደቱ ትኩረትንና ጥንቃቄን የሚሻ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም:: በመርሀ - ትምህርት ዝግጅት ላይ የሚሳተፉ ሁሉ ለየትኛውም የመረጃ ምንጭ የበለጠ ትኩረት ሳይሰጡ ከአራቱም የመረጃ ምንጮች በቂ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሏቸውን ዘዴዎች ሊጠቀሙ ይገባል:: ታነር /1983:39/ አንደኛውም የመረጃ ምንጭ ከሌላው የሚያስበልጥ የትምህርት ዝግጅት ለውድቀት የተጋለጠ ነው በማለት አራቱንም የመረጃ ምንጮች እኩል የመጠቀምን አስፈላጊነት ያስረዳሉ::

በአንድ የትምህርት ፕሮግራም ዝግጅት ሂደት ዓላማ መንደፍ አንዱና ዋነኛው ተግባር ነው:: በትምህርት ፕሮግራሙ አማካኝነት ከዳር ይደርስ ዘንድ የተፈለገው ዓላማ ከተነደፈም በኋላ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ይዘቶችን መርጦ በይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች አማካኝነት ማደራጀቱ ቀጣዩ ተግባር ነው:: በሚቀጥለው ክፍል ለይዘቶች መምረጫነትና የተመረጡትንም ይዘቶች ለማደራጀት የሚያገለግሉ መስፈርቶችና የአሠራር ዘዴዎች ይቀርባሉ::

### 2.2.3 የይዘት አመራረጥ

መርሀ-ትምህርትን ስናዘጋጅ በፍላጎት አሰሳ አማካኝነት በሰበሰብነው መረጃ ላይ ተመስርተን የትምህርቱን ዓላማ ከመሰረትን በኋላ ቀጣዩ ተግባራችን ተማሪዎች የትምህርቱን ዓላማ ከዳር ለማድረስ የሚያስችሏቸውን ይዘቶች መርጦ ማደራጀት

ነው:: ኑናን /1988:10/ ይዘት ተማሪው እንዲማረው የሚፈለገውን የቋንቋ እውቀት፣ ክሂሎች፣ አመለካከትና እሴትን የሚመለከት ሲሆን አወሳሰኑም ስለቋንቋ ተፈጥሮና ስለ ቋንቋ መማር ባለን ንድፈ ሃሳባዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያስረዳሉ::

የአንድን ቋንቋ ልዩ ልዩ ዘርፎች ሁሉ በአንድ ጊዜ ለማስተማር የሚቻል ባለመሆኑ እንደ አስፈላጊነታቸው የተወሰኑትን መርጦ ማስተማር ተገቢነት አለው:: መርጦ በማስተማሩ ላይ መግባባት ያለ ቢሆንም የይዘት መመረጫ መስፈርቶችን በተመከለተ ግን በመስኩ ባለሙያዎች ዘንድ ወጥ የሆነ አሠራር አይታይም:: ለዚህም የመጀመሪያው ምክንያት ለቋንቋ ማስተማሪነት የሚዘጋጁ መርሀ-ትምህርቶች ዓይነትና ዓላማ መለያየት ነው:: አንዳንድ ምሁራን አንድ መርሀ-ትምህርት ሊይዘው የሚገባውን የይዘት ዓይነት የሚወስነው ቋንቋውን ለማስተማር የተዘጋጀው የመርሀ-ትምህርት ዓይነት ነው የሚለውን ሃሣብ ሲያቀርቡ ሌሎች የመስኩ ምሁራን /ስሚዝ 1950፣ ታባ 1962፣ ሜኪይ 1962: ሀሊዴይ 1964: ኋይት 1988/ ግን ቀደም ሲል በተገለጸው ሃሣብ ላይ ተቃውሞ ባይኖራቸውም የትኛውንም ዓይነት መርሀ-ትምህርት ለማዘጋጀት የሚደረግ የይዘት ምርጫ በተጨማሪ ሊከተለው የሚገባው መስፈርት መኖሩን ይገልጻሉ::

### 2.2.3.1 የይዘት መምረጫ መስፈርቶች

ስሚዝ /1950:132-137/ አስፈላጊነት፣ ዘላቂነት፣ ጠቃሚነት፣ አስደሣችነትና ወቅታዊነት የሚሉትን ነጥቦች ለይዘት መምረጫ በመስፈርትነት መጠቀም ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ:: በሳቸው ገለጻ መሠረት አስፈላጊነት የተመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲያውቀው የተፈለገውን ነገር ለመጨበጥ ያስችለዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ዘላቂነት ደግሞ ይዘቱ ረጅም እድሜ ሊያገለግል የሚችል መሆን አለበት የሚለውን ያመለክታል:: ጠቃሚነት ተዘውትረው በጥቅም ላይ የሚውሉትን የቋንቋ ክፍሎች የመምረጡን አስፈላጊነት ሲያመለክት፣ አስደሣችነት ደግሞ የተማሪውን ችግር በማቃለልና እቅዱንም በማሟላት ስሜቱን የሚስበውን ይዘት በመምረጥ አስፈላጊነት ላይ የተመሠረተ መስፈርት ነው:: ወቅታዊነት ተማሪው በማኅበረሰባዊ ተግባራትና ጉዳዮች ውስጥ ተሣታፊ የሚያደርገውን ይዘት በመምረጥ አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል::

በሌላ በኩል ደግሞ ሜኪይ /1962: 176-187/ እና ኋይት /1988: 48-49/ ተደጋጋሚነት (frequency)፣ ልቀት (rang)፣ ቅርብነት (avialability)፣ የፍቺ ስፋት (coverage) እና ለመማር ያለው አመቺነት (learnability) የሚሉት መስፈርቶች ለይዘት መምረጫነት እንደሚያገለግሉ ያስረዳሉ::

ተደጋጋሚነት በአንድ በተመረጠ ንግግር ወይም ጽሑፍ ውስጥ ተደጋግሞ የሚመጣውን የቋንቋ ክፍል በመምረጥ አስፈላጊነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ልቀት ደግሞ ተመርጠው በተዘጋጁ የተለያዩ ጽሑፎች ወይም ንግግሮች ውስጥ ተደጋግሞ በመምጣት ብልጫ ያሳየውን የቋንቋ ክፍል መርጦ ለትምህርት በማቅረብ ተገቢነት ላይ የተመሠረተ የይዘት መምረጫ መስፈርት ነው:: ሜኬይ ተደጋጋሚነትንም ሆነ ልቀትን በይዘት መምረጫ መስፈርትነት የመጠቀሙ አስፈላጊነት የተመሰረተው ተማሪዎች ተደጋግሞ የሚመጣውን የቋንቋ ክፍል ተደጋግሞ ከማይመጣው የቋንቋ ክፍል በቀላሉ ይረዱታል በሚል እምነት ላይ መሆኑን ይገልጻሉ::

ተደጋጋሚነትና ልቀት የመመሳሰል ባሕሪ የሚታይባቸው ቢሆንም ልዩነት እንዳላቸው መገንዘቡ ጠቃሚ ነው:: ተደጋጋሚነት የአንድን ተፈላጊ የቋንቋ ክፍል በአንድ ዝግጅት ውስጥ ብቻ ተደጋግሞ መከሰትን የሚመለከት ሲሆን፣ ልቀት ግን ተፈላጊው የቋንቋ ክፍል በአንድ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ዝግጅቶች ውስጥ ተደጋግሞ በመከሰት ከሌሎች የቋንቋ ክፍሎች ብልጫ ለማሳየት መቻሉን የሚመዝን መስፈርት ነው::

ቅርብነት የሚለው መስፈርት ደግሞ አንዳንድ የቋንቋ ክፍሎች ለተወሰኑ ሁኔታዎች ካላቸው ቅርብነት የተነሳ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ በአገልግሎት ላይ ስለሚውሉ ተደጋግመው በሚመጡባቸው ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ ባላቸው ድግግሞሽ ብልጫ የመምረጥ አስፈላጊነትን ያመለክታል:: የፍች ስፋት የሚለው ደግሞ አንድ የቋንቋ ክፍል በርካታ ሁኔታዎችን አሳክቶ ለመግለጽ ከቻለና ሌሎችንም በርካታ የቋንቋ ክፍሎች በመተካት ያልተጓደለና የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት ከቻለ የፍቺ ስፋት ያለው በመሆኑ ከሌሎች ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊመረጥ ይገባዋል በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ የቋንቋ ክፍል ለመማር አመቺነት አለው? የሚለውን መስፈርት አሟልቶ ለመመረጥ የሚችለው ተመሳሳይነት (similarity)፣ ግልጽነት(clarity)፣ ምጥንነት (brevity)፣ ቋሚነት (regularity)፣ እና የመማር

ጫና(learning load) የሚሉትን ነጥቦች አሟልቶ ሲገኝ መሆኑን ሜኬይ /1962:187/ ያስረዳሉ:: እንደሳቸው ገለፃ ተመሳሳይነት ሁለተኛ ቋንቋውን የሚማር ተማሪ ከራሱ ቋንቋ ጋር ተመሳሳይነት ባላቸው የቋንቋ ክፍሎች እንዲጀምር የማድረግን አስፈላጊነት የሚያመለክት ሲሆን፣ ግልጽነት ደግሞ የያዙትን መልእክት ለተማሪዎች በቀላሉ ለማቅረብ የማያስቸግሩ የቋንቋ ክፍሎች በቅድሚያ ተመርጠው ለትምህርት መቅረብ አለባቸው በሚለው መርህ ላይ የተመሠረተ መስፈርት ነው:: ምጥንነት፣ ከአንደበት አውጥቶ ለመናገርም ሆነ ለግንዛቤ የሚያመች አጭርና ቀላል አቀራረብ ያላቸው የቋንቋ ክፍሎች ይህ ባሕሪ ከማይታይባቸው ቀድመው የመመረጣቸውን ተገቢነት ሲገልጽ፣ ቋሚነት ደግሞ የቋንቋውን ቋሚ ሕግጋት ሳያፋልሱ የሚከተሉ የቋንቋ ክፍሎች ከሌሎቹ ቀድመው የመመረጣቸውን አስፈላጊነት ያመለክታል:: የመማር ጫና የሚለው መስፈርት ደግሞ ለትምህርት የቀረበው የቋንቋ ክፍል የሚሰጠው አገልግሎት ተማሪው የቋንቋውን ክፍል ለማወቅ ከሚያደርገው ጥረት በልጦ ሲገኝ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደሚመረጥ ያመለክታል::

ታባም /1962:267-289/ በበኩላቸው ተቀባይነት፣ አስፈላጊነት፣ ከማኅበረሰባዊው እውነታ ጋር ያለው ተስማሚነት፣ የጥልቀትና የስፋት ተመጣጣኝነት፣ በርካታ ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ ያለው ብቃት፣ ለመማር ያለው አመቺነት፣ ከተማሪው ልምድ ጋር ያለው ተዛማጅነትና ከተማሪው ስሜትና ፍላጎት ጋር ያለው ስምረት የሚሉት ነጥቦች ይዘትን ለመምረጥ በመስፈርትነት እንደሚያገለግሉ ይገልጻሉ::

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በተያለዩ ፀሐፊዎች የቀረቡት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች አንዱ ሌላውን የሚቃረኑ ሳይሆኑ ተደጋጋፊነት ነው የሚታይባቸው:: በአጠቃላይ ይዘቶችን ስንመርጥ ይዘቶቹ ከትምህርቱ ዓላማ፡ ከተማሪዎች ፍላጐትና ስሜት ጋር ያላቸውን ስምረት፣ ተግባራዊ ጠቀሜታቸውንና ለመማር ያላቸውን አመቺነት፣ ተግባራዊነታቸውንና ከተማሪው ልምድ ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ ተቀባይነታቸውንና ተገቢነታቸውን፣ የተመጣጠነ ስፋትና ጥልቀታቸውን መመርመር ያሻል::

### 2.2.3.2 የይዘት አደረጃጀት

ማደራጀት የሚለው ቃል የሚተባበሩ ወይም የሚተጋገዙ ተደጋጋፊ ክፍሎችን መፍጠር እንደሚመለከት ፓስነር /1992:126/ ይገልጻሉ:: በሳቸውም ገለጻ መሠረት ማደራጀት በነገሮች መሀል ኅብረትና መተሳሰር መፍጠር ነው::

ይዘቶች የተቀናጀ ውጤትና የተፈለገውንም የባሕሪ ለውጥ ያስገኙ ዘንድ እርስ በርስ ሊደጋገፉ በሚችሉበት ውጤታማ መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል:: ሜኬይ /1962:204/ በቋንቋ ማስተማር - መማር ክንውን ውስጥ አደረጃጀት በአውሮፓ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይሰራበት እንደነበር ያስረዳሉ:: ታይለርም /1949:83/ አደረጃጀት በማስተማር-መማር ሂደት ብቃትና ተማሪዎች እንዲያሳዩ በሚፈለገው የባሕሪ ለውጥ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው በመሆኑ የመስኩ ምሁራን የትኩረት ነጥብ ከሆነ መሰንበቱን ይገልጻሉ::

ባጠቃላይ አንድ መርሀ-ትምህርት የትምህርት መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ በውስጡ አቅፎ የያዛቸው ይዘቶች የትምህርቱን ዓለማ ከዳር ለማድረስ በሚያስችላቸው መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል:: በአንድ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች የቱንም ያህል ተገቢነት ያላቸው ቢሆኑ አደረጃጀታቸው ከተበላሸ የታለመውን ዓላማ ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ብቃት አይኖራቸውም:: ከዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ግን ዓላማውን ከዳር ለማድረስ ወደሚያስችል የአደረጃጀት ብቃት እንዴት መድረስ ይቻላል? የሚለው ነው::

አብዛኞዎቹ የትምህርት ባለሙያዎች ስለአደረጃጀት ሲነሳ ይዘቶች በጊዜና በቦታ ውስጥ ያላቸውን ዝምድና የማጥናት አስፈላጊነት ላይ ይስማማሉ:: በዚህም በይዘቶች መሐከል ቀጥተኛ ዝምድና ለማስገኘት በጊዜ መሀል በሚቀርበው ትምህርት ውስጥ ቀዳሚውን ይዘት ለተከታዩ መሠረት እንዲሆን በሚያስችል መልኩ ማደራጀት የማይታለፍ ይሆናል::

ፓስነር /1992:127/ እንደሚያስረዱት የሥርዓተ-ትምህርት ቀጥተኛ ቅንብር የቅድመ ሁኔታዎች መሟላትን፣ የይዘቶች ተከታታይነት የሚጠበቅበትን መንገድ ማመቻቸትን ያመለክታል:: እንደሳቸውም ገለጻ ተከታይ የትምህርት ክፍሎች

በቀዳሚዎቹ ላይ እንዲመሠረቱ ማድረግ፣ የክሂሎችንና የግንዛቤዎችን ተለጣጣቂነት መጠበቅ ቀጥተኛ ቅንብር የሚያተኩርባቸው ነጥቦች ናቸው::

በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የተለያዩ ትምህርቶች በያሏቸው ይዘቶች መሀል ያለውን ዝምድና ጎናዊ ቅንብር እንደሚባል ታይለርና /1949:84/ ፖስነር /1992:127/ ያስረዳሉ:: ጎናዊ ቅንብር በአንድ የክፍል ደረጃ የሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች እርስ በርሳቸው ምን ያህል ይደጋገፋሉ? የሚለውን ያመለክታል:: በጥቅሉም ጎናዊ ቅንብር በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች አንዱ ሌላውን ለማጎልበት፣ ለማጠንከር የሚጫወተውን ሚና የሚገልጽ የአደረጃጀት መሰፈርት ነው::

የአደረጃጀት ዓለማ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን መስተጋብራዊ ውጤት ከፍ ለማድረግ በመሆኑ የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት ይችሉ ዘንድ ባደረጃጀት መስፈርቶች እየተመሩ ተደራጅተው ሊቀርቡ ይገባል::

### 2.2.3.3 የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች

በግልጽ የተቀመጠ ያደረጃጀት መስፈርት ሳይኖር ይዘቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማደራጀት አይቻልም:: ይህንንም ያደረጃጀት ችግር ለመወጣት የሚያስችሉ ሦስት ዓይነት ያደረጃጀት መስፈርቶች ስለመኖራቸው በርካታ የመስኩ ሊቃውንት ይስማማሉ (ታይለር 1949:84-86፣ ታባ 1962:292-300፣ ዶል 1970:144-147፣ ሴይለር 1981: 21፣ ኦሊቫ 1988:503-510፣ ፖስነር 1992:127):: መስፈርቶቹም የሚከተሉት ናቸው::

2.2.3.3.1 ተከታታይነት:- የመስኩ ምሁራን እንደሚያስረዱት ተከታታይነት አንድ ይዘት በተከታታይ ጊዜያት ውስጥ ሊከሰት የሚችልበትን ቀጥተኛ ሁኔታ ያመለክታል:: በሌላም አባባል ተከታታይነት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ አንድ የእውቀት ዓይነት ወይም ክሂል ተደጋግሞ የሚመጣበትንና በልምምድ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይገልጻል:: ታይለር /1949:85/ ተከታታይነት በትምህርት ክፍሎች መሀል ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት የሚገልጽ ሲሆን ይህም በአንድ የትምህርት ዓይነት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የአንድን ይዘት ተደጋግሞ መከሰት እንደሚያመለክት ያስረዳሉ:: ስትራቴሜየር /1957:12/ በበኩላቸው «ተከታታይነት

አንድን የትምህርት ክፍል የሚያግዙና የሚያጎለብቱ የጠቃሚ ነጥቦችንና ክሂሎችን ተደጋግሞ መምጣት ያመለክታል» በማለት ይገልጻሉ::

2.2.3.3.2 ተለጣጣቂነት:- እንደ ታይለር /1949:85/ ገለጻ ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር የተዛመደ ቢሆንም ተከታታይነትን አልፎ የሚሄድ ያደረጃጀት መስፈርት ነው:: ተለጣጣቂነት እንደ አደረጃጀት መስፈርት እያንዳንዱ ተከታታይ ይዘት በቀዳሚው ላይ ተመሥርቶ ስፋትና ጥልቀት በማግኘት ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጠል በመጓዝ በመስኩ የዳበረ እውቀት ለማስጨበጥ በሚያስችል መልኩ ተደራጅተው የሚቀርቡበትን መንገድ የሚያመለክት የአደረጃጀት መስፈርት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ታባ /1962:293/ ተለጣጣቂነት ይዘትንና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ቅደም ተከተል ባለው አቀማመጥ ለማደራጀት የምንጠቀምበት መስፈርት ነው በማለት ሲገልጹ ሀሊደይም /1964:210/ በበኩላቸው ተለጣጣቂነት መምህሩ አንድን ይዘት ከሌላው በማስቀደም ለማስተማር የሚወስንበት መስፈርት መሆኑን ያስረዳሉ::

ስትራቲሜየር /1957:12/ ተለጣጣቂነትን እንደሚከተለው ይገልጹታል::

> ተለጣጣቂነት ተማሪው የመረዳት ችሎታውን የሚያሳ ድግበትን፣ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ በሚገኙ ይዘቶች መካከል ያሉ ዝምድናዎችን ለማየት የሚችልበትንና በአንድ የእድገት ደረጃ ላይ ያገኘውን ማጠቃለያ በሚቀጥለው ደረጃ ላይ ለመጠቀም ወደሚችልበት እርከን ከፍ የሚልበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው::

እንደስትራቲሜየር ገለፃ ተለጣጣቂነት ተማሪው በሚማረው የትምህርት መስክ እድገትን ለማሳየት እንዲችል ይዘቶች በሥርዓት ተደራጅተው የመቅረባቸውን አስፈላጊነት የሚገልጽ ያደረጃጀት መስፈርት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ሊዮናርዶ በሚከተሉት ጥያቄዎች አማካኝነት ተለጣጣቂነትን እንዴት ሲገልጹት እንደሞከሩ ታባ /1962:292/ በመጥቀስ ያስረዳሉ:: «የትምህርት ቁሳቁሶች ቅደም ተከተል የሚወስነው እንዴት ነው? ምን ምንን ተከትሎ ይደራጃል? ይኸስ ለምን ይሆናል? ምን መቼ ይቀርባል?» ሊዮናርዶ በእነዚህ

ጥያቄዎች አማካኝነት ሊገልጹልን የሞከሩት፣ የትምህርት መሣሪያዎችን ቅደም ተከተል የሚወስን መስፈርት ከጣልን፣ የትኛው የትምህርት ክፍል ቀድሞ የትኛው እንደሚከተልና ይህም ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ቀድመን ከተረዳን፣ ተማሪዎች የትኛውን የትምህርት ክፍል በየትኛው ጊዜ ቢማሩ ሊቀላቸው እንደሚችል ከለየን የተለጣጣቂነትን ጥያቄ ለመመለስ መቻላችንን ነው::

ባጠቃላይ ከተነደፈው ዓላማ አኳያ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችል ተለጣጣቂነት በይዘቶች መሐል ለመገንባት ይቻል ዘንድ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ የሚያስኬዱ ያደረጃጀት ሥርዓቶች ብቻቸውን በቂ አይሆኑም:: ታባ /1962:294/ እንደሚያስረዱት ልጥጥቅ ብቃቱ የተጠበቀ ይሆን ዘንድ ተለጣጥቀው ሊደራጁ የቀረቡት የትምህርት ክፍሎች ከተማሪው ያስተሳሰብ መልክና የግንዛቤ ደረጃ ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገው ሊለወጡ ይገባል:: በሌላም አባባል የተማሪውን የእድገት ደረጃ የጠበቁ እንዲሆኑ ያሻል::

2.2.3.3.3 ውህደት:- በአንድ የትምህርት መስክ የተገኘውን እውነትና መመሪያ በሌላ የትምህርት መስክ ካለው ጋር ተዛማጅነትና ተደጋጋፊነት እንዲኖረው ማድረግን የሚጠይቅ ያደረጃጀት መስፈርት ነው:: የዚህ መስፈርት ተግባራዊነት የትምህርት መስኮችን መተጋገዝና መገነባባት ያስገኛል::

ውህደት እንደአደረጃጀት መርህ በተለያዩ መንገዶች እንደሚታይ ታባ /1962:299/ ይገልጻሉ:: በሳቸውም ገለጻ መሠረት ታይለር /1950/ ውህደትን የሥርዓተ-ትምህርት የተለያዩ ክፍሎች ጎናዊ ቅንብር አድርገው የሚመለከቱት ሲሆን ድሬሲል /1958/ ብሉም /1958/ ደግሞ ውህደት በአንድ ግለሰብ ውስጥ የሚካሄድ ለውጥ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ያስረዳሉ:: ድሬሲል ውህደት አንድ ሰው አስቀድሞ የማይገናኙ የሚመስሉ እውቀቶችንና ልምዶችን ፍች ባለው መንገድ ለማደራጀት የሚጠቀምበትን ሂደት እንደሚያመለክት ሲያስረዱ ብሉም ደግሞ የድሬሴልን ሃሣብ በማጠናከር፣ ውህደት በአንድ በኩል የራስን ልምድና እውቀት ማደራጀትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በራስ ልምድና እውቀት መካከል ዝምድናን መሻትን እንደሚመለከት ይገልጻሉ:: ከብሉም ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ውህደት አንድ ተማሪ ከእያንዳንዱ የትምህርት መስክ በሚያገኘው እውቀት የራሱን ልምድና እውቀት ማዳበሩን የሚመለከት ከመሆኑም ባሻገር የተማሪውንም ልምድና እውቀት የበለጠ ለማሣደግ ይችል ዘንድ በካበቱትና በተደራጁት ልምዶችና እውቀቶች መካከል መስተጋብራዊ አንድነት የመፍጠርንም አስፈላጊነት የሚጠይቅ ያደረጃጀት መስፈርት ነው::

ባጠቃላይ ውህደት የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ጎናዊ ዝምድና የሚመለከት፣ ተማሪው የተዋሀደ እውቀትና ልምድ እንዲያገኝ የሚያስችል፣ በሚቀርቡለት ይዘቶች እየታገዘ ባሕሪውን እንዲያዋህድ የሚረዳ ያደረጃጀት መልክ ነው፡፡

በመሠረቱ የይዘት አደረጃጀት ብቃት ማጣት ከትምህርት መስኩ ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀውን ውጤት እንዳይገኝ ሊያደርግ የሚችል በመሆኑ ለተማሪች የሚቀርቡ ይዘቶች የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ እንዲያስገኙ ከተፈለገ እነዚህ ያደረጃጀት መስፈርቶች ባግባቡ በሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

አንድን የትምህርት ፕሮግራም በሥራ ላይ ለማዋል ሲታቀድ የትምህርት ፕሮግራሙ የተነሳበትን ዓላማ መንደፍ ያስፈልጋል፡፡ ከዓላማው ቀረጻ በኋላ ዓላማውን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይዘቶች ተመርጠው በይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች አማካኝነት በመደራጀት ለትምህርት ይቀርባሉ፡፡ ይህንንም የዝግጅት ሂደት በአግባቡ ለማከናወን አለመቻል በትምህርት ፕሮግራሙ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሲከሰቱ ለመፍታትም ሆነ የትምህርት ፕሮግራሙን ወደ በለጠ የጥራት ደረጃ ለማሸጋገር ይቻል ዘንድ የትምህርት ፕሮግራሙ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሊጠና፣ ሊገመገምና ሊመዘን ይገባል፡፡ አንድን ጥናት ለማካሄድ ደግሞ ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዱ ዘዴዎች ያስፈልጋሉ፡፡ በቀጣዩም ክፍል ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት የሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይቀርባሉ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት፣ በ1984 ዓ.ም. ታትሞ ከ1985 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት የዓላማ አነዳደፍና የይዘት አደረጃጀት ብቃት እንዳለው ወይም እንደሌለው ለመመርመር የተደረገ ነው:: ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚጠቀም ሲሆን በዚህም ምዕራፍ የጥናቱን የመረጃ ምንጮች፣ የናሙና አወሳሰድ፣ የመረጃ አተናተን አሰባሰብ ዘዴዎች፣ የመጠይቆችና የቃለ መጠይቆች አዘገጃጀትና የመረጃ ዘዴ ይቀርባሉ::

### 3.1 የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው::

1. ይህ ጥናት በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የቀረቡ ዝርዝር ዓላማዎችን አነዳደፍና ይዘቶችን አደረጃጀት ብቃት ለመመርመር የተካሄደ በመሆኑ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት በመረጃ ምንጭነት አገልግሏል::

2. በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ 46 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሌላው የመረጃ ምንጭ ናቸው:: የአሥረኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመረጃ ምንጭነት መውሰዱ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት የዓላማዎቹ አነዳደፍና የይዘቶቹ አደረጃጀት መስመርም ሆነ ብቃት ማጣት ከማስተማር መማሩ ሂደት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ይህ ስምረትም ሆነ የብቃት ችግር በማስተማር-መማሩ ሂደት ላይ የሚኖረውን ገንቢም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ በተግባር የማየት እድል ስላላቸው ተጨባጭ መረጃ ለመስጠት እንደሚችሉ በማመን ነው::

3. በሥርዓተ-ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች መርሀ-ትምህርቱን በማዘጋጀት ሂደት ቀጥተኛ

ተሳትፎ ያደረጉ የዓላማዎችን አነዳደፍና የይዘቶቹን አደረጃጀት ብቃት በተመለከተ ሌላው የመረጃ ምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ ተደርጓል:: በዚህም ጥናት የተጠቃለሉት አራቱም የቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ናቸው::

### 3.2 የናሙና አወሳሰድ

ይህ ጥናት ያመቺነት ንሙና የሚባለውን የናሙና አወሳሰድ ሥልት ተጠቅሟል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ከክልል 14 ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ሲሆን መምህራኑም በሙሉ ተወስደዋል:: የግልና የሚሲዩን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው በጥናቱ ውስጥ አልታቀፉም::

በሌላም በኩል በሥርዓተ-ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የሚሰሩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የትምህርት ባለሞያቹን እንዳሉ መወሰድ አስፈላጊ ሆኗል::

ይሁንና 10ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጁት መጠይቆች በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተበተኑ ቢሆንም በመድኃኒዓለም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መርሀ-ትምህርቱ ስላልደረሳቸው መጠይቁን ሳይሞሉ ባዶውን በመመለሳቸው በጥናቱ ሳይታቀፉ ቀርተዋል:: ከዚህም ሌላ ከተሰበሰቡት 52 መጠይቆች ውስጥ 6 መምህራን መርሀ-ትምህርቱን እንደማይገለገሉበት በመግለጻቸው መጠይቃቸው ከትንተናው ውጭ እንዲሆን ተደርጓል::

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ቀጥሎ በተዘረዘሩት ዘዴዎች አማካኝነት ተሰብስበዋል::

1. የ10ኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ_ትምህርት ቫሌትና ዲስክ /1972/ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ደረጃቸው ለመከፋፈል የተገለገሉበትን ያሠራር ስልት በመጠቀም ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ ብሉምና ሌሎች /1956/ የሰውነት ማጎልመሻና የኅብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት ዓላማዎችን በእድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል ያዘጋጁትን ስልት ቫሌትና ዲስክ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችንና ሙከራዎችን ለመከፋፈል በሚያመች መልኩ በማዘጋጀት የተጠቀሙበት በመሆኑ በዚህም ጥናት በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን አነዳደፍና ይዘቶችን አደረጃጀት ለመተንተን በአብይ መሣሪያነት በሥራ ላይ ውሏል፡፡ ምንም እንኳ ቫሌትና ዲስክ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል ያዘጋጁት ሞዴል ለሁለተኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ቢሆንም በተለይ ለቋንቋ ትምህርት በሚያመች መልኩ በመዘጋጀቱ በዚህ ጥናት የዓላማዎችንና የይዘቶችን አደረጃጀት ብቃት ለመተንተን እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡ በሌላም በኩል ቫሌትና ዲስክ የሁለተኛቋንቋ ዓላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል የተጠቀሙበትን ያሠራር ስልት ወደ አማርኛ በመመለስና ለዚህም የምርምር ሥራ በሚያመች መንገድ በማዘጋጀት ሞዴሉ ጥናቱን ለማካሄድ ያለውን ብቃት ከመጀመሪያ ድግሪ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው 3 የትምህርት ባለሞያች እንዲገመግሙት ተደርጎ በሰጡት የማሻሻያ ሃሣብ መሠረት እንደገና ተሰርቶ በሙከራ ጥናት ላይ ከታየ በኋላ ጥሩ ውጤት በማስገኘቱ ለዋናው ጥናት እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር ዓለማዎችና ተማሪች ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካኝነት እንዲያከናውኑ የተፈለጉትን ተግባራት በቫሌትና ዲስክ ሞዴል መሠረት ለመከፋፈል ከተሞከረ በኋላ ከመጀመሪያ ድግሪ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው 3 የትምህርት ባለሞያዎች እንዲያዩት ተደርጎ የክፍፍሉን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የይዘቶችን አደረጃጀት ለመለካት የሞከረው ተማሪች ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካኝነት እንዲያከናውኑ የተፈለጉትን ተግባራት በመጠቀም ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ብሉም /1971:22/ እንደሚያስረዱት ይዘት በራሱ ፍቺ አልባ በመሆኑና ስለይዘትም የሚናገሩ ዓረፍተ ነገሮች ተማሪው ከትምህርቱ በኋላ

ያሳያል ተብሎ የሚታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለማሳየት የማይችሉ በመሆናቸው ከመገለጫ መንገዳቸው ውጭ ባሉበት ሁኔታ አደረጃጀታቸውን ለመመዘን አመቺነት ስለሌለው ነው::

ቫሌትና ዲስክ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል የተጠቀሙበትን ያሠራር ስልት ሜካኒካዊ ክሂል፣ እውቀት፣ ሽግግር፣ ተግባቦትና ትችት በሚሉ አምስት ዓብይ የትምህርት ክፍሎች የከፈሉት ሲሆን የመጀመሪዎቹንም 4 የትምህርት ክፍሎች በሁለት በሁለት ንዑሳን የትምህርት ክፍሎች ከፍለዋቸዋል:: የመጨረሻውና ትችት የሚለውን የትምህርት ክፍል ደግሞ በ3 ንዑሳን የትምህርት ክፍሎች የከፈሉት ሲሆን በእያንዳንዱም አብይ የትምህርት ደረጃ ተማሪው በአራቱ የቋንቋ ክሂሎችና በሥነ-ጽሑፍ እውቀት ዘርፍ ሊያሳይ ይገባዋል ብለው ያመኑበትን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትና ሙከራ በሚል ርእስ የዓላማዎቹን ተግባራዊነት ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው፣ በየደረጃው ተማሪው ሊያከናውናቸው ይገባል ብለው የወሰኗቸውን ተግባራት አመልክተዋል:: የዚህንም ዝርዝር መግለጫ በአባሪ «ረ» ላይ ይመልከቷል::

2. በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ10ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቆችን አዘጋጅቶ በመበተን መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል::

3. በሥርዓተ-ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባለሞያዎች ቃለ መጠይቅን አዘጋጅቶ በማቅረብ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል::

### 3.4 የመጠይቆችና የቃለ መጠይቆች አዘገጃጀት

በጥናቱ እንዲሳተፉ ለተመረጡት በአዲስ አበባ ከፍተኛሁለተኛ ደረጃ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጀው መጠይቅ በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው:: የመጀመሪው ክፍል ከመምህራን የሚፈለጉ አጠቃላይ መረጃዎችን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር ዓላማዎች አነዳደፍ ብቃት ለመመርመር የተዘጋጁ ጥያቄዎችን የያዘ ነው::

የመጨረሻውና ሦስተኛው ክፍል በአሥረኛ ክ፤ፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ይዘቶች አደረጃጀት ብቃት ለመለካት የተዘጋጁ ጥያቄዎች የሚገኙበት ክፍል ነው።

በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች አማራጭ መልሶችን የያዙና በጽሑፍ የሚመለሱ ጥቄዎችን ያካተቱ ሲሆን ብዛታቸውም አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቁትን ሳይጨምር 27 ናቸው። ጥያቄዎቹ የጥናቱን ዓላማ ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማስገኘት እንዲረዱ ከክለሳ ድርሳናትና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን በማስተማር ላይ ከሚገኙ መምህራን በናሙና ጥናት በተገኙ መረጃዎች ላይ በመንተራስ ተዘጋጅተው በባለሞያዎች እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ በተገኙት የእርምት ሀሣቦች አማካኝነት ተሻሽለው በጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። የመጠይቁ መላሾች በምርጫ መልክ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ የሚስማሙበት መልስ ከሌለ ጥያቄውን ከመመለስ እንዳይታቀቡ የራሳቸውን ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉበት ክፍት ቦታ ተትቶላቸዋል። ጥያቄዎቹም ሲዘጋጁ እያንዳንዱ ተጠያቂ ለጥናቱ ወሳኝ መረጃን ለሚያስገኙ ጥያቄዎች የሚሰጠውን ምላሽ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሌሎች ጥያቄዎች ተካተው እንዲያቀርቡ ተደርጓል።

በሌላ በኩል ደግሞ በሥርዓተ-ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች የተዘጋጀው ቃለ መጠይቅ በአሥረኛ ክፍል ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንደተዘጋጀው መጠይቅ ሁሉ ከክለሳ ድርሳናትና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን በማስተማር ላይ ከሚገኙ መምህራን በተገኙ መረጃዎች ላይ በመንተራስ ተዘጋጅተው በባለሞያች እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ በተገኙት የእርምት ሃሣቦች አማካኝነት እንዲሻሻሉ በማድረግ የተፈለገውን መረጃ ለማሰባሰብ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

### 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን አነዳደፍና ይዘቶችን አደረጃጀት ብቃት ለመለካት የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ሦስት የመረጃ ምንጮችን የተጠቀመ ሲሆን ከእነዚህም የመረጃ ምንጮች የተሰበሰበው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል።

1. ሻሌትና ዲስክ /1972/ የሁለተኛቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል የተጠቀሙበትን ያሠራር ስልት በመጠቀም ተማሪዎች ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካይነት እንዲያከናውኑ የተፈለጉትን ተግባራት በእድገት ተከታታይነታቸው ለመከፋፈል ተሞክሯል፡፡ በዚህም ያሠራር ስልት የተገኘውን ውጤት ከመጀመሪያ ድግሪ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው የትምህርት ባለሞያች እንዲገመግሙት ተደርጎ ያከፋፈሉን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛቋንቋ መምህራን በተበተኑ መጠይቆች አማካይነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚከተለው ሁኔታ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በመጠይቁ ውስጥ ለተካተቱት ጥያቄዎች የቀረቡትን ምርጫዎች በመምረጥ የተሰጡ መልሶች በየፊደል ተራዎቹ ከተሰበሰቡና በቁጥርም ከተወከሉ በኋላ ወደ መቶኛ እንዲለወጡ የተደረገ ሲሆን ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ የሚስማሙበት ባለመኖሩ ከራሳቸው ምላሽ የሰጡም በዚሁ በመቶኛ ስሌት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምርጫ በሌላቸው ጥያቄዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችም እንዲሁ በጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን ለመምህራን በተበተኑ መጠይቆች አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ በሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጋር በመዋሃድ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

3. በሥርዓተ-ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎችም በቃለ መጠይቅ አማካይነት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ የትምህርቱ ባለሞዎች ባለባቸው የሥራ ጫና ምክንያት ሁሉንም አንድ ላይ በማገናኘት ቃለ መጠይቁን ለማድረግ ባለመቻሉ እያንዳንዱ የትምህርት ባለሞያ በተመቸው ጊዜ ቃለ መጠይቁ እንዲቀርብላቸው ተደርጓል፡፡ ለቃለ መጠይቁም የተሰጠውን ምላሽ ለመያዝ የተሞከረው በጽሑፍ ሲሆን ይህንንም በአባሪ « ሐ » ላይ ይመለከቷል፡፡ በቃለ መጠይቁ አማካኝነት በሥርዓተ-ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች የተሰበሰቡትንና ተመሳሳይ የሆኑትን መረጃዎች በማገናኘት፣ ልዩነት ያላቸውን ደግሞ እራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃና የጥናቱ ውጤት ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በተለያዩ የመርጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ይቀርባሉ፣ ከመረጃዎቹም የተገኙት ውጤቶች እየተተነተኑ ማብራሪያ ይሰጥባቸዋል።

### 4.1. የመረጃ ትንተና

#### 4.1.1 በቫሌትና ሪኒ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችና ሙከራዎች አከፋፈል ስልት፣ ከመምህራንና በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ክፍል በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ–ትምህርት ዉስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎችን አነዳደፍና ይዘቶችን አድርጃጀት ብቃት ለመገምገም ይቻል ዘንድ ቫሌትና ሪኒ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ተከታታይነታቸዉ ለመከፋፈል የተገለገሉበትን ያሰራር ስልት በመጠቀም፣ በመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ ለአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በታደለ መጠይቅና በስርኣተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ይተነተናሉ።

##### 4.1.1.1 በክፍል አንድ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማግኘት ለመምህራን ከቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ መርጃዎች ትንተና

ሰንጠረዥ 1 ስለ መምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ

| ጾታ | | የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት | | | | | የትምህርት ደረጃ | | የአገልግሎት ዘመን በአማካይ | 10ኛ ክፍል ያስተማሩበት ዘመን በአማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አብይ | | | ንዑስ | | ዲግሪ | ዲፕሎማ | | |
| ወ | ሴ | አማርኛ | እንግሊዘኛ | ፔዳጎጂ | አማርኛ | እንግሊዘኛ | | | | |
| 38 | 8 | 40 | - | 6 | 6 | 4 | 24 | 22 | 18.3 | 8.6 |

በመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ ለአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከታደሉ 60 መጠይቆች ዉስጥ ሀምሳ ሁለቱ ተሞልተዉ ሲመለሱ 8 መጠይቆች ግን ሳይሞሉ ባዷቸዉን ተመልሰዋል። ተሞልተዉ ከተመለሱት ሀምሳ ሁለት መጠይቆች ዉስጥ ደግሞ ስድስቱ በመርሀ–ትምህርቱ እንደማይገለገሉ በማመልከታቸዉ

መጠይቃቸዉ ከትንታኔዉ ዉስጥ እንዲወጣ ተደርጓል። ከመጠይቁ ተሰብስበዉ ከላይ በቀረበዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የሰፈሩት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት 38 ወንዶችና 8 ሴቶች በጥናቱ ዉስጥ ተካተዋል። መምህራኑም በሙሉ አማርኛን የማስተማር ስልጠና ያገኙ ሲሆን ሠያ አራቱ የድግሪና ሀያ ሁለቱ ደግሞ የዲፕሎማ ትምህርት ደረጃ ያላቸዉ መሆኑን ከቀረበዉ መረጃ መረዳት ይቻላል። መረጃዉ እንደሚያረጋግጥው አርባ መምህራን አማርኛን፤ ስድስት መምህራን ደግሞ ፔዳጎጂክስን አብይ የትምህርት መስክ በማድረግ የሰለጠኑ ሲሆን ከአብይ የትምህርት መስክ በተጨማሪ ያጠኑት ንዑስ የትምህርት መስክ መኖሩን በማመልከት አስር ተጠያቂዎች ብቻ መልስ ሰጥተዋል። በተገኘውም መረጃ መሠረት አማርኛን በንዑስ ትምህርት መስክ ያጠኑ ስድስት መምህራን ሲሆኑ እንግሊዝኛን በንዑስ ትምህርት መስክ ያጠኑ ደግሞ አራት መምህራን ናቸው። የመምህራኑም የአገልግሎት ዘመን በአማካይ 18.3 ሲሆን በ10ኛ ክፍል ያገለገሉበት ዘመን በአማካይ 8.6 ነው። ከዚህም የመረጃ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ ግማሽ የአገልግሎት ዘመናቸውን ያሳለፉት አማርኛን አስረኛ ክፍል በማስተማር ነው።

4.1.1.2 በክፍል ሁለት በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎችን አነዳደፍ ብቃት ለመለካት የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና፤

ሰንጠረዥ 2 አላማዎቹ በክፍል ደርጃው ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፤

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ናቸው | 24 | 52.2 |
| ለ | አይደሉም | 22 | 47.8 |
| ድምር | | 46 | 100 |

ዝርዝር አላማዎቹ በተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውንም ሆነ አለመሆናቸውን በማመልከት ምላሽ የሰጡ ተጠያቂዎች ብዛት በጣም ተቀራራቢ መሆኑ የትኛውንም መልስ በአስተማማኝ መረጃ ሰጭነት ለመቀበል ያስቸግራል። በስርዐተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች በበኩላቸው የሰጡት ምላሽ እንዲሁ የዓላማዎቹን የተተግባሪነት ደረጃ ለይቶ ለማመልከት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም።

ከላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለዉ 24 (52.2%) መላሾች አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያመለክቱ 22 (47.85) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ ገልፀዋል:: ምንም እንኳ ከፍተኛዉን ቁጥር የያዙት መላሾች አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማመልከት ምላሽ ቢሰጡም አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ በማመልከት ምላሽ የሰጡ ተጠያቂዎች ቁጥር ከቀዳሚዎቹ ጋር እጅግ ተቀራራቢ መሆኑ፤ ከዚህ ምላሽ የተገኘዉ የመረጃ ዉጤት ዝርዝር አላማዎቹ በተግባራዊነት ብቃታቸዉ ችግር ያለባቸዉ መሆኑን በማመልከት ፍንጭ ሊሰጥ እንደሚችል የዚህ ጥናት አቅራቢ እምነት ነዉ::

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ – ትምህርት ዉስጥ የታቀፉትን ዝርዝር አላማዎች ተተግባሪነት አስመልክቶ ለቀረበላቸዉ ቃለ መጠይቅ ሁለት የቋንቋዉ ትምህርትክፍል ባለሙያዎች ዝርዝር አላማዎቹ የተማሪዉን የክፍል ደረጃ እንዲመጥኑ ተደርገዉ የተቀረፀ በመሆናቸው ያለ ችግር በክፍል ደረጃዉ በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል:: ቀሪዎቹ ሁለት የቋንቋዉ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች ደግሞ ዝርዝር አላማዎቹ የአነዳደፍ ግልፅነት ስለሚጎላቸዉ አሁን ባሉበት አቀራረብ ሙሉ ለሙሉ በተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ ብለዉ ለመናገር እንደሚቸገሩ በማመልከት መልሰዋል::

ሰንጠረዥ 3 አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበዉ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አላማዎቹ በዉስጣቸዉ የያዟቸዉ የባህሪ ለውጥ አይነቶች የክፍል ደረጃዉን የሚመጥኑ አለመሆናቸዉ | 2 | 9.1 |
| ለ | አላማዎቹ እንዲ[illegible]ያመለክቱ የተፈለገዉ የባህሪ ለዉጥ አይነት በግልፅ የተቀመጠ አለመሆኑ | 12 | 54.6 |
| ሐ | አላማዎቹ ለተግባራዊነታቸ የሚጠይቋቸዉ ይዘቶች በክፍል ደረጃዉ ያሉ ተማሪዎች ሊረዱትዉ የሚችሉ አለመሆናቸዉ | 3 | 13.6 |
| መ | አላማዎቹ ለተግባራዊነታቸዉ የሚጠይቋቸዉ ይዘቶች በመርሀ–ትምህርት ዉስጥ የተካተቱላቸዉ ባለመሆኑ | 4 | 18.2 |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | 1 | 4.5 |
| | ድምር | 22 | 100 |

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዉስጥ ያታቀፉ ዝርዝር አላማዎች በክፍል ደረጃዉ በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ መሆናቸዉን ያመለከቱ ተጠያቂዎች ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት እንዲገልፁ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ 12(54.6%) መላሾች አላማዎቹ እንዲያመለክቱ የተፈለገዉ የባህሪ ለዉጥ አይነት በግልፅ የተቀመጠ አለመሆኑ በተግባራዊነታቸዉ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑን ሲገልፁ 4(18.2%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ለተግባራዊነታቸዉ የሚጠይቋቸዉ ይዘቶች በመርሀ-ትምህርቱ ዉስጥ የተካተቱላቸዉ ባለመሆኑ በክፍል ደረጃዉ የሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊያደርጓቸዉ እንደማይችሉ አመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 3( 13.6%) መላሾች አላማዎቹ ለተግባራዊነታቸዉ የሚጠይቋቸዉ ይዘቶች በክፍል ደረጃዉ ያሉ ተማሪዎች ሊረዱቸዉ የሚችሉ አለመሆናቸዉ በተማሪዎችተግባራዊ ከመሆን እንደገደባቸዉ ሲያመለክቱ 2(9.1%) መላሾች በበኩላቸዉ አላማዎቹ በዉስጣቸዉ የያዟቸዉ የባህሪ ለዉጥ አይነቶች የክፍል ደረጃዉን የሚመጥኑ አለመሆናቸዉ በክፍል ደረጃዉ የሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ እንዳያደርጓቸዉ መሰናክል ሊሆን እንደሚችል በማመልከት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀሪዉ 1(4.5%) መላሽ ደግሞ ተማሪዎች ቀደም ሲል ከ1ኛ - 8ኛ ባሉት ክፍሎች ዉስጥ አጠናቀዉ መምጣት ሲገባቸዉ ያላጠናቀቁት ስላለ አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም በማለት ምላሻቸዉን በፅሁፍ ሰጥተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸዉን ወይም አለመሆናቸዉን ለመለየት ለቀረበዉ ቃለ መጠይቅ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ሁለት የአመርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች አላማዎቹ በክፍል ደረጃዉ በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ በማመልከት በሰጡት ምክንያታዊ መልስ ላይ ለመግለፅ እንደሞከሩት አላማዎቹ ግልፅ ሆነዉ አለመነደፋቸዉ በተግባራዊነታቸዉ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡

ከላይ አስራ ሁለቱ መላሾች እንዳመለከቱትም ሆነ ቀደም ባለዉ የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ዉስጥ እንደተገለፀዉ የአላማዎች ተተግባሪነት ከግልፅነታቸዉ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለዉ በመሆኑ ባፃፃፋቸዉ ተተንትነዉና ተለይተዉ የተፈለገዉን የባህሪ ለዉጥ አይነት በማያሻማ መልኩ ሊያመለክቱ በሚችሉበት መንገድ ተፅፈዉ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለአላማዎች ግልፅነት ማጣት በተቀዳሚ ምክንያትነት የሚጠቀሱት አላማዎችን ለመንደፍ የምንጠቀምባቸዉ ቃላት በመሆናቸዉ አንድን አላማ የሚያነቡ ሰዎች አላማዉ ስለሚለዉ ነገር የተለያየ ግምት እንዲኖራቸዉ በሚያደርጉ ቃላት አለመጠቀም ይመረጣል፡፡ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዉስጥ የታቀፉት የአብዛኛዎቹ ዝርዝር አላማዎች ችግርም ይሄዉ ነዉ፡፡ የችግሩም ዋና መንስኤ ዝርዝር አላማዎቹ በአንድ ጊዜ ብዙ ነገር ለማለት በሚችሉ ቃላት ተቀርፀዉ መቅረባቸዉ ሲሆን ይህም አይነቱ አቀራረብ ደግሞ ከተማሪዉ የሚጠበቀዉን የባህሪ ለዉጥ አይነት በእርግጠኝነት ለይቶ ለማመልከት የማያስችል ከመሆኑ ባሻገር አላማዎቹን ያነበበ ሁሉ በተረዳዉ መንገድ ተግባራዊ እንዲያደርጋቸዉ በመጋበዝ ለተዘበራረቀ አሰራርና የባህሪ ለዉጥ አይነት ያጋልጣል፡፡

ሰንጠረዥ 4 አላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ዉስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸዉን ወይም አለመሆናቸዉን ለመለየት ለቀረበዉ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | መቶኛ |
| ሀ | ይችላሉ | 33 | 71.7 |
| ለ | አይችሉም | 13 | 28.3 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ክላይ በቀረበዉ መረጃ መሰረት 33 (71.7%) መላሾች ዝርዝር አላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ዉስጥ ተግበራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸዉን በማመልከት ምላሽ ሲሰጡ 13 (28.3%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ዉስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ መሆናቸዉን ገልፀዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቱት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዉስጥ የሚገኙ ዝርዝር አላማዎች ሲነደፉ ተማሪዉ ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ ለማገናዘብ ምን ያህል እንደተሞከረ እንዲገልፁ ለቀረበላቸዉ ቃለ መጠይቅ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ሁኔታን የሚያመለክቱ ምላሽ ሰጥተዋል። እንደ ትምህርት ባለሙያዎቹም ገለፃ መርሀ-ትምህርቱ የተዘጋጀዉ በመስክ ጉብኝት በመላ ሀገሪቱ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ በመሆኑ ዝርዝር አላማዎቹም ተማሪዎች የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ እንዲሆኑ ጥረት መደረጉን ገልፀዋል።

በመሰረቱ የትምህርት አላማዎች ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ዉስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ዉስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ አላማዎች ደግሞ ከተማሪዎች ህይወት ጋር በመቆራኘት ተግባራዊ ጠቀሜታን የሚያስገኙ አይሁኑም። ታባም ( 1962:199-202) የምንነድፋቸዉ አላማዎች በክፍሉ ደረጃ በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉበትም እዉነተኛ ሁኔታዎች ያሏቸዉ ሊሆኑ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ሰንጠረዥ 5 አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ::

| ተ.ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ይችላሉ | 20 | 43.5 |
| ለ | አይችሉም | 26 | 56.5 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ከላይ እንደተመለከተው 26 (56.5%) መላሾች አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ አይደሉም በማለት መልስ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 20 (43.5፤) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን በመልሳቸው አመልክተዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለመሆን የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፥ ይህን ጥያቄ መመለስ የሚገባቸው በክፍል ደረጃው የሚያስተምሩ መምህራን መሆናቸውን በመጥቀስ እንደ ትምህርት ባለሞያነታቸው የቋንቋውን ማስተማሪያ መሳሪያዎች ለማሻሻል በሚያደርጉት ጥረት መረጃዎችን የሚያገኙት ቋንቋውን ከሚያስተምሩ መምህራን መሆኑን አስታውሰው የማስተማሪያ መጽሀፍቱንና መርሀ - ትምህርቱን ለማሻሻል በየጊዜው በሚያደርጉት የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ላይ እስከ አሁን አላማዎቹን በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ተስኖናል የሚል አስተያየት እንዳላስተዋሉ ያመለከቱ ሲሆን ይህም ሲባል ግን አላማዎቹ በዚህ ረገድ ፈጽሞ ችግር የለባቸውም ማለት አለመሆኑን ገልፀዋል::

ቀደም ሲል የአላማዎቹን ተተግባሪነት አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ 24 (52.2%) መላሾች አላማዎቹ በክፍል ደረጃው ባሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማመልከት ምላሽ ቢሰጡም ከላይ ለማየት እንደሚቻለው አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን በማመልከት ምላሽ የሰጡ ግን 20 (43.5%) ተጠያቂዎች ብቻ መሆናቸው የአላማዎቹን ተተግባሪነት አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን የአዎንታ ምላሽ አጠራጣሪ አድርጎታል:: የአላማዎች ተተግባሪነት መታየት ያለበት አንድም በተወሰነው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ባላቸው ተተግባሪነት ጭምር በመሆኑ የአላማዎቹን ተተግባሪነት ከጊዜ ለይቶ በመበየን የተሰጠው ምላሽ ችግር እንዳለበት ማስተዋል ይቻላል::

ትምህርታዊ አላማዎች በታቀደላቸው የትምህርት ዘመን ውስጥ ተግባራዊ ለመሆን የመቻላቸው አስፈላጊነት ከጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። አላማዎች በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ ካልቻሉ ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ያሳያሉ ተብሎ የተገመተውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለማሳየት መቻልና አለመቻላቸውን በመመዘን የትምህርቱን ሂደት ስኬታማነት ለመለየት የማይቻል ከመሆኑ ባሻገር ከግምገማውም ተግባራዊ ምላሽ በመነሳት የትምህርቱን ፕሮግራም ለማሻሻልም ሆነ ቀጣዩን ፕሮግራም ለመንደፍ የሚያስችል እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚሞከር አይሆንም።

ሰንጠረዥ 6 አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ።

| ተ.ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አላማዎቹ የክፍሉን ደረጃ የማይመጥኑ በመሆናቸው | 2 | 7.7 |
| ለ | አላአማዎቹ ከተማሪዎች ምን እንደሚጠበቅ ለይቶ በማመልከት ተማሪዎቹ ለአላማዎቹ ተግባራዊነት የድርሻቸውን እንዲወጡ ስለማያስችሏቸው | 16 | 61.6 |
| ሐ | ለተግባራዊነታቸው የሚጠይቁት ጊዜ ረጅም በመሆኑ | 6 | 23 |
| መ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጠቀሱ | 2 | 7.7 |
| | ድምር | 26 | 100 |

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ በማመልከት ምላሽ የሰጡ ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት እንዲያሳውቁ ለቀረበላቸው ጥያቄ 16 (61.6%) መላሾች አላማዎቹ ከተማሪዎች ምን እንደሚጠበቅ ለይቶ በማመልከት ተማሪዎች ለአላማዎቹ ተግባራዊነት የድርሻቸውን እንዲወጡ ስለማያስችሏቸው መሆኑን በማመልከት ምላሽ ሲሰጡ 6 (23%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ለተግባራዊነታቸው ረጅም ጊዜን የሚጠይቁ መሆናቸው በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለመሆን አላስቻላቸውም በማለት መልሰዋል። 2(7.7%) መላሾች በበኩላቸው አላማዎቹ የክፍሉን ደረጃ የማይመጥኑ መሆናቸው በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ እንዳይሆኑ መሰናክል እንደሆነባቸው በማመልከት ምላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 2(7.7%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ተማሪዎቹን የበለጠ በቋንቋው ተጠቃሚ በሚያደርጋቸው ነጥብ ላይ የሚያተኩሩ ባለመሆናቸው ምክንያት ተማሪውን ስለማይስቡት በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ለመሆን የመቻላቸው ሁኔታ ያጠራጥራል በማለት ምላሻቸውን በጽሁፍ ሰጥተዋል።

ቀደም ሲል በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረውም ሆነ አስራ ስድስቱ ተጠያቂዎች በሰጡት ምላሽ እንዳመለከቱት ተማሪዎች በተነደፈው አላማ ውስጥ ያሳያሉ ተብሎ የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት በማያሻማ መንገድ ለመረዳት ካልቻሉ ለአላማው ተግባራዊነት ከነሱ የሚጠበቀውን ድርሻ ለመወጣት የማይችሉ ከመሆኑ ባሻገር እያንዳንዱም መምህር በተረዳቸው መንገድ ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው በር በመክፈት ለተለያየና ለተዘበራረቀ አሰራር ያጋልጣል:: ይህም ደግሞ በበኩሉ የግምገማውን ሂደት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ይታመናል:: ባጠቃላይም ዝርዝር አላማዎች ከተማሪዎች ምን እንደሚጠበቅ ለይተው ሊያመለክቱ በሚችሉበት መንገድ ሲቀረጹ ነው ለቀና ተግባራዊነታቸው ማሟላት ከሚገባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱንና ዋነኛውን አሟልተዋል ለማለት የሚቻለው::

ሰንጠረዥ 7 ተማሪዎች አላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ የተነደፉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አዎ | 13 | 28.3 |
| ለ | አይደለም | 33 | 71.7 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት 33(71.7%) መላሾች ተማሪዎች አላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ የተፃፉ አለመሆናቸውን ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ 13(28.3%) መላሾች ደግሞ ተማሪዎች አላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ተጽፈዋል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል::

በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎችም በበኩላቸው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአሰሳ ጥናት ያገኙት መረጃ አላማዎቹ ተማሪዎች ከሚሰጣቸው ትምህርት በኋላ ያሳያሉ ተብሎ የሚገመተውን የባህሪ ለውጥ አይነት ማሳየታቸውን በተግባር ለመግለጽ ማድረግ ያለባቸውን በማመልከት አለመነደፋቸውን እንደሚያመለክት ገልፀዋል::

አላማዎች ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ብቻ ሳይሆን መገለጫ መንገዳቸውንም በመያዝ መፃፍ እንዳለባቸው በርካታ የመስኩ ምሁራን (ታይለር 1949÷ ታባ 1962÷ ቫሌትና ሪኒ 1972÷ ሚጀር 1984÷ አሊቫ 1988) ይገልፃሉ:: አላማዎች በተግባር ውለው ሊታዩ የሚገባቸው እቅዶች በመሆናቸው የእነዚህን እቅዶች መገለጫ መንገድ ለመወሰን አለመቻል ተማሪዎች ወደ አልተፈለገ ውጤት ቢያመሩ ለመቆጣጠርም ሆነ እቅዶቹ መተግበራቸውን ለመከታተል ወይም ለመገምገም አስቸጋሪ በመሆኑ አላማዎችን መገለጫ መንገዳቸውን እንዲይዙ በማድረግ መንደፍ አስፈላጊ ነው::

በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች መገለጫ መንገዳቸውን በመያዝ የተነደፉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ይቻል ዘንድ መርሀ - ትምህርቱን ለመመርመር ተሞክሯል:: መርሀ - ትምህርቱንም በመመርመር የተገኘው ውጤት የአላማዎቹን አቀራረጽ አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ አብዛኞቹ መላሾች ከሰጡት መልስ ጋር የሚስማማ ሆኖ የተገኘ ሲሆን ይህንንም ቀጥሎ ከቀረበው መግለጫ መረዳት ይቻላል::

ሰንጠረዥ 8 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች አቀራረብና የሚያስነሱት ጥያቄ መግለጫ

| መገለጫ መንገዳቸውን ያልያዙ ዝርዝር አላማዎች | የዝርዝር አላማዎቹ መገለጫ መንገዳቸውን አለመያዝ የሚያስነሳው ጥያቄ |
|---|---|
| - የቋንቋ መሰረተ ሀሳቦችን ያውቃሉ<br>- ምዕላዶችን ያውቃሉ<br>- የቋንቋውን አሰካክ ያውቃሉ<br>- የልቦለድ አፃፃፍን ያውቃሉ<br>- የግጥም አፃፃፍን ያውቃሉ<br>- የኢልቦለድ አፃፃፍን ያውቃሉ | - ማወቅ የሚለው ቃል ምን ማድረግን ያመለክታል?<br>- ተማሪዎች እንዲያውቁ የተፈለገውን ነገር ማወቃቸውን በምን መንገድ ነው የሚገልፁት? |
| - ተጠያቂያዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ<br>- የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳባቸውን ያዳብራሉ<br>- ድርሰት የመፃፍ ችሎታን ያዳብራሉ<br>- የቃላት ችሎታን ያዳብራሉ | - ተማሪዎች ተጠያቂያዊ አስተሳሰብን÷ ሀሳባቸውን÷ ድርሰት የመፃፍና የቃላት ችሎታቸውን ማዳበራቸውን የሚገልፁት በምን መንገድ ነው?<br>- ተማሪዎች እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ማሳየታቸውን እንዴት መረዳት ይቻላል? |
| - የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳቦችን ይገነዘባሉ | - ተማሪዎች የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳቦችን መገንዘባቸውን የሚገልፁት በምን መንገድ ነው? |
| - ፍሬ ሀሳቦችን ከዝርዝር ሀሳቦች አንብቦ መለየት ይችላሉ<br>- ድርሰት መፃፍ ይችላሉ | - ተማሪዎች ፍሬ ሀሳቦችን ከዝርዝር ሀሳቦች ለመለየትም ሆነ ድርሰት ለመፃፍ መቻላቸውን በምን መንገድ ነው የሚገልፁት? |

ከላይ እንደተገለፀው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች ተማሪዎች አላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ አልተፃፉም:: ባቀራረባቸው የተወሰነ የባህሪ ለውጥ አይነትን የሚያመለክቱ ቃላትን በመጠቀም የተቀረፁ ባለመሆናቸው ከዝርዝርነት ይልቅ የአጠቃላይነት ባህሪ ጎልቶ የሚታይባቸው በመሆኑ አላማዎቹን የሚያነቡ የተለያዩ ሰዎች ተማሪው እንዲያሳየው ስለተፈለገው የባህሪ ለውጥ አይነት የተለያየ ግምት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ::

አላማዎች ውሱን ሆነው የመቅረባቸውን አስፈላጊነት በማስመልከት ሜጀር (1984.20) እንደሚያስረዱት አንድን አላማ የሚያነቡ የተለያዩ ሰዎች አላማው ስለሚለው ነገር የተለያየ ግምት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ቃላት ስላሉ በነዚህ ቃላት ተጠቅሞ አላማዎችን አለመንደፍ ተማሪው ከትምህርቱ በኋላ እንዲያሳይ የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለይቶ በማመልከት ተማሪው ለአላማው ተግባራዊነት ከእሱ ምን እንደሚጠበቅ በግልጽ አውቆ የድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ ያስችላል:

ሰንጠረዥ 9 አላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሰረተ አደረጃጀት ያላቸው መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አላቸው | 15 | 32.6 |
| ለ | የላቸውም | 31 | 67.4 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት 31 (67.4%) መላሾች አላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሰረተ አደረጃጀት የሌላቸው መሆኑን ሲያመለክቱ 15 (32.6%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሰረተ አደረጃጀት ያላቸው መሆኑን ገልፀዋል::

በስርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች የአላማዎቹን አደረጃጀት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አላማዎቹ ከቀላል ወደ ከባድ በሚያስኬድ መንገድ የተደራጁ መሆናቸውን አመልክተዋል::

የአላማዎችን አደረጃጀት በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የማድረጉ አስፈላጊነት ከጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ የእድገት ተከታታይነትን ተከትለው ያልተደራጁ አላማዎች በይዘቶችም አደረጃጀት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ይታመናል፡፡ የአላማዎቹ አደረጃጀት ተማሪው ከትምህርቱ በኋላ እንዲያሳየው የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት እድገት እያሳየ እንዲሄድ የሚያስችል ካልሆነ አላማዎቹንም ተከትለው የሚደራጁት ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ፥ ከቅርብ ወደ ሩቅ ወዘተ. የሚያስኬድ አደረጃጀት ሊኖራቸው አይችልም፡፡

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር አላማዎች አደረጃጀት ለመለየት ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ውጤት፥ ቫሌትና ሪኒ (1972) የቋንቋ ትምህርት አላማዎችንና ሙከራዎችን በተለያዩ ክፍሎች ለማደራጀት የተጠቀሙበትን ያከፋፈል ሂደት በመጠቀም አደረጃጀታቸውን ለመተንተን ተሞክሮ ከተገኘው ውጤት ጋር የሚስማማና አላማዎቹ ያደረጃጀት ችግር ያለባቸው መሆኑን ያመለከተ ሲሆን ይህንንም ቀጥሎ ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡


ሰንጠረዥ 10 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎችን አደረጃጀት የሚያሳይ መግለጫ

| አብይ የትምህርት ርዕሶች | ዝርዝር አላማዎች | ዝርዝር አላማዎቹ የተመደቡበት ክፍል |
|---|---|---|
| ስነ - ልሳን | ፃቋንቋ መሰረተ ሀሳቦችን ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| መፃፍ | ድርሰት መፃፍ ይችላሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| ስነ - ልሳን | የቃላት ችሎታን ያዳብራሉ<br>ምዕላዶችን ያውቃሉ<br>የቋንቋውን አሰካክ ያውቃሉ | ሽግግር-በስራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ማንበብ | የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳቦችን ይገነዘባሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| ማዳመጥና መናገር | ተጠያቂያዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ | ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| ማንበብ | የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳባቸውን ያዳብራሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| መፃፍ | ድርሰት የመፃፍ ችሎታን ያዳብራሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| ስነ ልሳን | የቋንቋውን አሰካክ ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| ማንበብ | ፍሬ ሀሳቦችን ከዝርዝር ሀሳቦች አንብቦ መለየት ይችላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| መፃፍ | ድርሰት የመፃፍ ችሎታን ያዳብራሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| ስነ - ጽሁፍ | የልቦለድ አፃፃፍን ያውቃሉ<br>የግጥም አፃፃፍን ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ማንበብ | የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሃሳቦችን ይገነዘባሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| ማዳመጥና መናገር | የተወሰነ ሀሳብን በራስ አባባል የማቅረብ ዘዴን ያዳብራል | ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| መፃፍ | ድርሰት የመፃፍ ችሎታን ያዳብራል<br>የኢልቦለድ አፃፃፍን ያውቃሉ | ትችት - ማዋሀድ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ልቦለድ | የልቦለድ አፃፃፍ ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያሳዩ የተፈለገው የባህሪ ለውጥ አይነት ቫሌትና ሪኒ (1972 : 32) ዝቀተኛ ብለው በሚጠሩት የትምህርት ክፍል ይጀምራል። ተማሪዎች የቋንቋ መሰረተ ሀሳቦችን እንዲያውቁ በሚጠይቀው የባህሪ ለውጥ አይነት የጀመረው የትምህርት ሂደት ተማሪዎች ድርሰት መፃፍ የሚያስችላቸውን ትምህርት ወደ ሚያገኙበት ከፍተኛ የትምህርት ክፍል ከተሸጋገረ በኋላ በደረጃው ከቀዳሚው ዝቅ ወደሚለው የትምህርት ክፍል በመመለስ ተማሪዎች የቃላት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ወደሚጠይቀውና "ሽግግር" ወደተባለው የባህሪ ለውጥ አይነት የሚያመራ ከመሆኑ ባሻገር ምዕላዶችንና የቋንቋውን አስካክ በማወቅ በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኝ የባህሪ አይነት እንዲያሳዩ ይጠይቃል። ከዚህም በኋላ የትምህርቱ እንቅስቃሴ ተማሪዎች የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳቦችን እንዲገነዘቡ፥ ተጠያቂያዊ አስተሳሰቦችን እንዲሁም የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ሀሳባቸውን እንዲያዳብሩ ወደሚያስችላቸው " ተግባቦት" ወደተባለው የትምህርት ክፍል በማምራት በመጠኑም ቢሆን የእድገት ሂደቱን ጠብቆ "ትችት" ወደተባለው የትምህርት ክፍል ሲሸጋገር ይታያል። ከዚህም ከፍተኛ የትምህርት ክፍል የትምህርቱ ሂደት በመነሳት እውቀት ተብሎ ወደሚጠራው ዝቅተኛ የትምህርት ክፍል ያመራ ሲሆን በዚህም የትምህርት ደረጃ ተማሪዎች የቋንቋዉን አስካክ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ከቋንቋ አስካክ እዉቀት በኋላ ተማሪዎች እንዲሸጋገሩ የተደረገዉ ተግባቦት ወደሚባለዉ ከፍተኛ የትምህርት ክፍል ሲሆን በዚህም ደረጃ ፍሬ ሀሳቦች አንብበው መለየት ይችላሉ ተብሎ ይገመታል። ከዚህም በኋላ ተማሪዎች የተግባቦት ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ከሚያስችላቸዉ የትምህርት ክፍል እድገቱን በጠበቀ አካሄድ " ትችት" ወደሚለዉ የትምህርት ክፍል የተሸጋገሩ ሲሆን በዚህም ደረጃ ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸዉን እንደሚያዳብሩ ከአላማዉ መረዳት ይቻላል። " ትችት" ከሚለዉ ከፍተኛ የትህርት ክፍል ተማሪዎች እንዲያሳዩ የተፈለገዉ የባህሪ ለዉጥ አይነት ያመራዉ " እዉቀት" ወደሚለዉ ዝቅተኛ የትምህርት ክፍል ሲሆን በዚህም የትምህርት ደረጃ ተማሪዎች የልበወለድና የግጥም አፃፃፍን ያዉቃሉ ተብሎ የሚገመት ሲሆን ከዚህም በማስከተል የተለያዩ ፅሁፎችን አንብበዉ ሀሳቦችን ወደሚገነዘቡበት፥ የተወሰነ ሀሳብን በራሳቸዉ አባባል የማቅረብ ዘዴን ወደሚያዳብሩበት ከፍተኛ የትምህርት ክፍል እንዲሸጋገሩ ተደርጔል። ተማሪዎች ከዚህም " ተግባቦታዊ" ችሎታቸዉን ለማዳበር ከሚያስችላቸዉ የትምህርት ክፍል ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸዉን ለማዳበር ወደሚያስችላቸዉ የትምህርት ክፍል ደረጃዉን ጠብቀዉ ከተሸጋገሩ በኋላ የኢልቦለድና የልቦለድ አፃፃፍን ለማወቅ ወደሚያስችላቸዉና " እዉቀት " ወደተባለዉ የትምህርት ክፍል በመመለስ የአመቱን ትምህርት ያበቃሉ።

ከላይ ከቀረበዉ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለዉ የዝርዝር አላማዎቹ አደረጃጀት ችግር የሚታይበት ሲሆን ይህንንም ያደረጃጀት መዛባት የበለጠ መረዳት እንዲቻል እነደሚከተለዉ በግራፍ መልክ ቀርቧል፡

ሰንጠረዥ11፥ በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትህርት ዉስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች አደረጃጀት የሚያሳይ ግራፍ




ከላይ የቀረበዉ ግራፍ የያዘዉ መረጃ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዉስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች ያላቸዉን አደረጃጀት የሚያሳይ ነዉ። ከ1-19 የተጠቀሱት ተራ ቁጥሮች ለአሰራር ቅለት ሲባል ዝርዝር አላማዎቹን እንዲወክሉ የተደረገ ሲሆን ሙሉ መረጃዉንም በአባሪው ላይ ይመለከቷል።

ግራፉ የያዘዉ መረጃ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዉስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች ቫሌትና ሪኒ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችንና ሙከራዎችን የእድገት ተከታታይነታቸዉን ተከትለዉ ለመከፋፈል ከተጠቀሙበት ያሰራር ስልት ጋር የሚስማማ አደረጃጀት እንደሌላቸዉ ያሳያል። በነቫሌት እምነት የቋንቋ ትምህርት አላማዎችም ሆኑ ሙከራዎች ከቀላል የባህሪ ለዉጥ አይነት በመጀመር ወደ ከፍተኛና ዉስብስብ የባህሪ ለዉጥ አይነት የሚያስኬደዉን የአደረጃጀት ስልት ተከትለዉ ሊደራጁ የሚገባ ሲሆን በእድገት ተከታታይነት ላይ ተመስርተዉ ያልተደራጁ አላማዎች ደግሞ ተማሪዎች ከቀላል የባህሪ ለዉጥ አይነት ዉስብስብ ወደ ሆነ የባህሪ ለዉጥ አይነት የእድገት ሂደቱን ጠብቀዉ እንዲሸጋገሩ የማያስችሏቸዉ ከመሆኑ ባሻገር ቀላል የሆነ የባህሪ ለዉጥ አይነት እንዲያሳዩ የሚያስችላቸዉን ይዘት ከተማሩ በኋላ ወዲያው በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የባህሪ ለውጥ ዓይነት እንዲያሳዩ የሚያስችላቸውን ይዘት እንዲማሩ ሲደረግ ተማሪዎቹን በማደናገርና በራስ የመተማመን ችሎታቸዉን በማሳጣት በትምህርቱ ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸዉ ሊያደርግ ይችላል።

በሌላም በኩል የዝርዝር አላማዎቹ አደረጃጀት ብቃት ማጣት በይዘቶችም አደረጃጀት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይታመናል:: ይዘቶች የአላማዎች ማስፈፀምያ መሳሪያዎች በመሆናቸዉ በአላማዎች መስፈርትነት ተመርጠዉ ይደራጃሉ:: የሚደራጁት ደግሞ አላማዎቹን ተከትለዉ በመሆኑ አደረጃጀታቸዉ የተበላሸ አላማዎችን ተከትለዉ የተደራጁ ይዘቶች አደረጃጀታቸዉ እንደ አላማዎቹ ሁሉ ብቃት የሌለዉ እንደሚሆን ይታመናል::

ሰንጠረዥ 12 አላማዎቹ የሚያሳዩትን ለመለየት ለቀረበዉ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ከተማሪዉ የሚጠበቀዉ የባህሪ ለዉጥ | 24 | 52.2 |
| ለ | ተማሪዉ እንዲማረዉ የሚፈለገዉን የይዘት ዝርዝር | 8 | 17.4 |
| ሐ | ከተማሪዉ የሚጠበቀዉን የባህሪ ለዉጥ አይነትና ባህሪዉ የሚገለጥበትን ይዘት | 6 | 13 |
| መ | መምህሩ ማድረግ ያለበትን ተግባር | 7 | 15.2 |
| | | | |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | 1 | 2.2 |
| ድምር | | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት 24 ( 52.2% ) መላሾች አላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ብቻ እንደሚያሳዩ ሲገልፁ 8 (17.4% ) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ የይዘት ዝርዝር መሆናቸውን አመልክተዋል:: ሌሎች 7 (15.2%) መላሾች በበኩላቸው አላማዎቹ መምህሩ ማድረግ ያለበትን ተግባር እንደሚያመለክቱ ሲገልፁ 6 (13%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነትና ባህሪውም የሚገለጥበትን ይዘት እንደሚያሳዩ አመልክተዋል:: ቀሪው 1 (2.2%) መላሽ " አላማዎቹ የሚያሳዩትን ለመለየት ያስቸግራል" በማለት ምላሻቸውን በፅሁፍ ሰጥተዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትህርት ክፍል ባለሞያዎች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች ምንን እንደሚያመለክቱ እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አላማዎቹ ተማሪው ከትምህርቱ በኋላ ያሳያል ተብሎ የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት እንደሚያሳዩ ሲገልፁ ይህ አቀራረባቸው ግን ብቃት እንደሚጎድለው አንድ የትህርት ክፍሉ ባለሙያ ሊያመለክቱ ሞክረዋል::

በርካታ የመስኩ ምሁራን ( ታይለር 1949: 46-74÷- ታባ 1962:200÷ ቫሌትና ሪኒ 1972:17÷ ፔይኔ 1974: 7÷ ጌጅ 19 79:40÷ ሴለይር 1981:150÷ ሜጀር 1984:20÷ ኦሊቫ 1988:391) እንደሚያስረዱት የትምህርት አላማዎች ሁለት የማይነጣጠሉ ሁኔታዎችን የያዙ ናቸው:: እነርሱም ተማሪው ያሳያል ተብሎ የሚገመተው የባህሪ ለውጥ አይነትና ይህም የባህሪ ለውጥ ዓይነት የሚገለጥበትን መንገድ ናቸው:: በዚህም መሰረት ሀያ አራቱ መላሾች እንዳመለከቱት አላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ብቻ በመግለፅ ከተነደፉ የአላማዎቹን ተግባራዊነት ለመቆጣጠር የማያመች ሲሆን÷ ስምንቱ መላሾችም እንዳመለከቱት አላማዎቹ የይዘቶች ዝርዝር ከሆኑ ይዘቶችን በመዘርዘር የሚፃፉ አላማዎች ተማሪዎች በነዚህ ይዘቶች ምን እንደሚሰሩ የሚገልፁ ባለመሆናቸው አላማዎቹ በዚህም አቀራረባቸው ችግር ያልተለያቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል:: በሌላም በኩል ሰባቱ መላሾች እንደገለፁት አላማዎቹ መምህሩ ማድረግ ያለበትን በመግለፅ ተፅፈው ከሆነ÷ የአንድ ትምህርት ግብ መምህሩ አንዳንድ ተግባራትን እንዲፈፅም ማስቻል ባለመሆኑና በዚህም መንገድ የተፃፉ አላማዎች ተማሪዎች የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ማሳየታቸውን ወይም አለማሳየታቸውን ለመመዘን ስለማያስችሉ አላማዎቹ አሁንም ችግር ያልተለያቸዉ መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ባጠቃላይ ቀደም ሲል ዝርዝር አላማዎቹ መገለጫ መንገዳቸውን በመያዝ መነደፋቸውን ወይም አለመነደፋቸውን ለመለየት ይቻል ዘንድ መርሀ - ትምህርቱን በመመርመር የተገኘው ውጤት እንዳረጋገጠውም ሆነ ሀያ አራቱ ተጠያቂዎችና በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች በሰጡት ምላሽ እንዳመለከቱት አላማዎቹ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ብቻ አጠቃላይ በሆነ መልኩ እንዲያሳዩ ተደርገው የተነደፉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል::

ሰንጠረዥ 13 አላማዎቹ ተማሪዎች እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ መፃፋቸውን ወይም አለመፃፋቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አዎ | 13 | 28.3 |
| ለ | አይደሉም | 33 | 71.7 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ከላይ እንደተመለከተው 33 ( 71.7% ) መላሾች አላማዎች ተማሪዎቹ ከሚሰጣቸው

ትምህርት በኋላ ያሳያሉ ተብሎ የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለመረዳት በማያድግት መንገድ አለመፃፋቸውን በማመልከት የሰጡት ምላሽ አላማዎች ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር በማይሉበት አቀራረብ፥ ለመረዳት በማያስቸግርና ተማሪዎች እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት በግልፅ ለማመልከት በሚችሉበት መንገድ መፃፍ አለባቸው ከሚለው የመስኩ ምሁራን ( ታባ 1962፡199-202፥ ሜጀር 1962፡24፥ ሌይዛውት 1963፡53፥ አሊቫ 1988፡392) ገለፃ ጋር የሚስማማ አቀራረብ የሌላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ቀሪዎቹ 13 (28.3%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ተማሪዎቹ እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ መፃፋቸውን ገልፀዋል::

በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች የዝርዝር አላማዎቹን ግልፅነት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ አላማዎቹ በአንድ ጊዜ ብዙ ነገር ሊያመለክቱ በሚችሉ ቃላት የተነደፉ በመሆናቸው ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ወስኖ በግልፅ የማመልከት ሀይላቸው ደካማ መሆኑን ገልፀዋል:: ጋኝ ( 1969፡241-242) ዝርዝር አላማዎችን ስንነድፍ ሁሉም አይነት ቃላት ወይም ሀረጎች ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለመግለፅ እኩል ጠቀሜታ ስለሌላቸው በቃላት አጠቃቀማችን ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባን ያስገነዝባሉ:: በሳቸውም ገለፃ መሰረት አንድ ተማሪ ከሚማረው ትምህርት በኋላ አንድን ነገር ያውቃል ወይም ይረዳል ወይም ያደንቃል የሚለው አቀራረብ የአንድን ትምህርት ሂደት ለማቀድ የሚያስችል መሰረት ስለማይሆን ዝርዝር አላማዎችን ስንነድፍ ተግባር ገላጭ ቃላትን መጠቀም ተመራጭነት አለው:: በሌላም በኩል ሜጀር ( 1984፡20 ) እንደሚያስረዱት አንድን አላማ የሚያነቡ ሰዎች አላማው ስለሚለው ነገር የተለያየ ግምት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ቃላት ስላሉ ውሱን አላማዎችን ስንነድፍ በቃላት አጠቃቀማችን ላይ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል::

ቀደም ሲል ዝርዝር አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ አላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ በማመልከት ምላሽ የሰጡ ምክንያታቸውን እንዲያሳውቁ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት መላሾች የአላማዎቹ ግልፅ በሆነና በማያሻማ መንገድ አለመፃፍ በተግባራዊነታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩን በማመልከት የሰጡት ምላሽ ከላይ የአላማዎቹን ግልፅነት አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት መላሾች ከሰጡት መልስ ጋር መስመሩ በርግጥም አላማዎቹ የግልፅነት ችግር ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል::

በመሰረቱ አላማዎቹ አንድ የባህሪ ለውጥ አይነትን ብቻ ወስኖ ለማመልከት በሚያስችሉ ቃላት አለመነደፋቸው ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ያሳያሉ ተብሎ

የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ግልፅ በሆነና በማያሻማ መንገድ ለማሳየት የሚያስችል ብቃት እንዳይኖራቸው አድርጓል:: የአላማዎቹ ግልፅ አለመሆን ደግሞ አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይዘቶችን ለመምረጥም ሆነ የትምህርቱን እንቅስቃሴ ውጤታማነት ለመገምገም የሚያስችል ብቃት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል::

ሰንጠረዥ 14፥ አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ መልስ መግለጫ

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ይሰጣሉ | 30 | 65.2 |
| ለ | አይሰጡም | 16 | 34.8 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ከላይ እንደተገለፀው 30 ( 65.2%) መላሾች አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ 16(34.8%) መላሾች ደግሞ አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸውን ገልፀዋል፡

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች የአላማዎቹን የትኩረት አቅጣጫ እንዲለዩ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሶስቱ የትምህርት ባለሙያዎች አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን ሲያመለክቱ ቀሪው አንድ የትምህርት ክፍል ባለሞያ ግን የአላማዎቹ ትኩረት የተዛባና አንዱን የትምህርት ክፍል ከሌላው አስበልጦ የማየት ባህሪ እንደሚታይባቸው ገልፀዋል::

መርሀ-ትምህርቱን በመመርመር የተገኘው ውጤት ግን አብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣጣም አለመሆኑን ቀጥሎ ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል::

ሰንጠረዥ 15፣ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ዝርዝር አላማዎች ትኩረት የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | አቢይ የትምህርት ርዕሶች | የአላማዎች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ማዳመጥ | - | - |
| 2 | መናገር | 1 | 5.3 |
| 3 | ማንበብ | 4 | 21 |
| 4 | መፃፍ | 5 | 26. 3 |
| 5 | ስነ-ልሣን | 5 | 26. 3 |
| 6 | ስነ-ጽሁፍ | 3 | 15.8 |
| 7 | ልዩ ልዩ የትምህርት ርሰሶች | 1 | 5.3 |
| | ድምር | 19 | 100 |

ከላይ ከቀረበው መግለጫ መረዳት እንደሚቻለው ለመፃፍ ክሂልና ለስነ- ልሳን ዕውቀት ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን በሁለተኛነት ትኩረትን ያገኘው የማንበብ ክሂል ነው፡፡ ስነ- ፅሁፍ በሶስተኛ የትኩረት ደረጃ ላይ ሲገኝ የመናገር ክሂል ደግሞ የመጨረሻውን ግምት አግኝቷል፡፡ የማዳመጥ ክሂል ግን ጨርሶ ተዘንግቷል፡፡ ይህም የትኩረት ስርጭት መዛባት እንደሚያሳየው ዝርዝር ዓላማዎቹ ለሁሉም የቋንቋ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች እኩል ትኩረት አይሰጡም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይዘቶች የሚመረጡት ተማሪዎች በማማሩት የትምህርት መስክ እንዲያሳዩ የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት እንዲያሳዩ ለመርዳት ሲሆን አላማ ያልተነደፈለት የትምህርት ርዕስ ይዘት ይኖረዋል ለማለት ባያስደፍርም አላማ ሳይቀረጽለት ይዘት የተመረጠለት የትምህርት ርዕስ ቢገኝ ይህ ይዘት ምንን ከዳር ለማድረስና በምን መስፈርት ተመረጠ? ለሚለው ጥያቄ የተሟላ መልስ ማግኘትም ሆነ መስጠት የሚቻል አይመስልም፡፡ በመሠረቱ ተማሪዎች እንዲማሩ ለሚፈለገው አብይ የትምህርት ርዕስ አላማ አለመንደፍም ሆነ አላማ ሳይነደፍ ይዘት መምረጥ ትክክል አይደለም፡፡ ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በዝርዝር አላማዎች አቀራረፅ ረገድ ለተለያዩ አብይ የትምህርት ርዕሶች የተሰጠው የትኩረት አለመመጣጠን እንደለ ሆኖ ማዳመጥ ለሚለው አብይ የትምህርት ርዕስ አላማ እንዳልተነደፈለት ስናይ መርሀ- ትምህርቱ የቋንቋውን ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች በተሟላና በተመጣጠነ ሁኔታ ለማስተማር ያለው ብቃት አስተማማኝ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች የሰጡትን የትኩረት መጠን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ አላማዎቹ ለየትምህርት ክፍሎቹ የተመጣጠነ ትኩረት እንደማይሰጡ በማመልከት ምላሽ የሰጡ ለየትኛው የቋንቋ ክሂል ወይም የዕውቀት ዘርፍ የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ በመለየት በፅሑፍ እንዲገልፁ ለቀረበላቸው ጥያቄ 7(43.8%) መላሾች ለስነ- ልሳንና ለስነ --ፅሑፍ የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ ሲገልፁ 4(25%) መላሾች በበኩላቸው ዝርዝር አላማዎቹ ለማንበብ ክሂል ከፍተኛውን ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን አመልክተዋል ቀሪው 1(6.2%)መላሽ ደግሞ አላሞዎቹ የትኩረት አቅጣጫ እንደማይታወቅ በመግለፅ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ ምላሽ ግን መርሀ ትምህርቱን በመመርመር ከተገኘው መረጃ ጋር ብዙም የሚስምር አይደለም። ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት መላሾች ዝርዝር አላማዎቹ ከፍተኛውን ትኩረት የሚሰጡት ለስነ - ፅሁፍ ነው ይበሉ እንጂ ከመርሀ - ትምህርቱ የተገኘው መረጃ ግን ለመፃፍ ክሂልና ለስነ ልሳን ዕውቀት መሆኑን ያሳያል። ያም ሆነ ይህ የትኛውም የትኩረት ልዩነት የተማሪዎችን ሁለንተናዊ ተፅዕኖ የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር በሚ ደርገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይታመናል።

ባጠቃላይ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች የአላማ አነዳደፍ መርሆዎችን ተከትለው አለመነደፋቸውን ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል። ይህ ደግሞ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህን ከመሰለው ችግር ለመራቅ የምንነድፋቸው ዝርዝር አላማዎች በክፍል ደረጃው ያሉ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታና በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ፥ የክፍሉን ደረጃ የሚመጥኑ፥ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነትና መገለጫ መንገዳቸውን የያዙ፥ የእድገት ተከታታይነታቸውን የጠበቁ፥ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡና ግልፅ በሆነ መንገድ የቀረቡ መሆን ይገባቸዋል።

### 4.1.1.3 በክፍል ሶስት በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችን አደረጃጀት ብቃት ለመለካት የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና፡፡

በዚህ ክፍል ለአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን 15 ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በሥርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ደግሞ በቃል የሚመለሱ 8 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹም ሆኑ ከተዛማጅ ጽሑፎች የተወሰዱ መስፈርቶች በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ያላቸውን የአደረጃጀት ብቃት በመፈተሽ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 16 በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ይመጥናሉ | 13 | 28.2 |
| ለ | አይመጥኑም | 10 | 21.8 |
| ሐ | በከፊል ይመጥናሉ | 23 | 50 |
| | ድምር | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት 23 /50 በመቶ/ መላሾች የክፍል ደረጃውን የሚመጥኑ ይዘቶች ከፊሎቹ መሆናቸውን ሲያመለክቱ 13 /28.2 በመቶ/ መላሾች ደግሞ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ይዘቶት ባጠቃላይ የክፍሉን ደረጃ እንደሚመጥኑ ገልጸዋል፡፡ ቀሪዎቹ 10 /21.8 በመቶ/ መላሾች በበኩላቸው የክፍሉ ደረጃ የሚመጥኑ ይዘቶች አለመኖራቸውን አመልክተዋል፡፡

በሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያች ይዘቶቹ የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ መሆን

ወይም አለመሆናቸውን እንዲለዩ ለቀረበላቸው ጥያቄ አንድ የማስተማሪያ መሣሪያ ሲዘጋጅ አስቀድሞ መልስ ሊሻለት የሚገባው አብይ ጥያቄ የሚዘጋጀው የትምህርት መሣሪያ በውስጡ እንዲይዛቸው የተደረጉ ይዘቶች የተማሪውን የእድሜና የክፍል ደረጃ ይመጥናሉ ወይ ? የሚለው መሆኑን አመልክተው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትም ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች ሙሉ ለሙሉ ለማለት ባይቻልም ባመዛኙ ለዚህ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ የሚሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ቀደም ሲል በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ክፍል እንደተገለጸው አንድን የትምህርት ሂደት የታለመው ግብ ላይ ለማድረስ የሚያስችሉትን ይዘቶች ስንመርጥ ልናተኩርባቸው ከሚገቡን ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የተማሪው ብስለት በመሆኑ የትምህርት ይዘቶች መረጣ የተማሪውን የብስለት ደረጃ ያገናዘበ ሊሆን የሚገባው ከመሆኑ ባሻገር የመረጥናቸው ይዘቶችም በተማሪው ያስተሳሰብ መልክና የግንዛቤ ደረጃ ተለውጠው ሊቀርቡ ይገባል።

ከላይ እንደተመለከተው በመጠይቅ የተገኘው ውጤት ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን ይመጥናሉ ብሎ ለመናገር የሚያስችል አይደለም። ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት መላሾች ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን በከፊል እንደሚመጥኑ በማመልከት የሰጡት ምላሽ ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን በመመጠን ረገድ ችግር ያለባቸው መሆኑን ነው የሚያመለከተው ። በሌላም በኩል ደግሞ ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን ይመጥናሉ ወይም አይመጥኑም በማለት ምላሽ የሰጡ ተጠያቂዎች ቁጥር ተቀራራቢ መሆኑ የችግሩን መኖር የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ መስክ ጥናት ቢደረግ ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ውጤት ላይ ሊደረስ የሚቻል መሆኑን የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል።

ሰንጠረዥ 17 በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አላቸው | 15 | 32.6 |
| ለ | የላቸውም | 7 | 15.2 |
| ሐ | በከፊል አላቸው | 24 | 52.2 |
| | ድ ም ር | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ 24/52.2 በመቶ/ መላሾች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይዘቶች ከፊሎቹ መሆናቸውን ሲያመለክቱ፣ 15/32.6 በመቶ/ መላሾች ደግሞ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች በሙሉ በክፍል ደረጃው የሚሰጠውን የቋንቋ ትምህርት ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው መሆኑን ገልጸዋል:: ቀሪዎቹ 7/15.2 በመቶ/ መላሾች በበኩላቸው ይዘቶቹ ባጠቃላይ ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት እንደሌላቸው ገልጸዋል::

በሥርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ይዘቶቹ ቋንቋዎቹን ለማስተማር ያላቸውን ተገቢነት እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሶስቱ የትምህርት ባለሞያዎች የይዘት ምርጫና የተገቢነት ጥያቄ ተነጣጥለው የማይሄዱ መሆናቸውን ጠቅሰው ከትምህርቱ ሂደት በኋላ በሚገኘው የግምገማ ውጤት ሊሻሻሉና ሊዳበሩ ከሚችሉ አንዳንድ ይዘቶች በስተቀር ሁሉም በክፍል ደረጃው ሊሰጥ የሚገባውን የቋንቋ ትምህርት ለማስተማር ካላቸው ተገቢነት አኳያ ተመዝነውና ተለክተው የተመረጡ መሆናቸውን ሲያመለክቱ ቀሪው አንድ የትምህርት ባለሞያ ግን የይዘቶችን ተገቢነት በተመለከተ የአሥረኛ ክፍል ብቻ ሳይሆን የሌሎቹም ክፍሎች መርሀ ትምህርቶች ችግር እንዳለባቸው በመጠቆም ምላሽ ሰጥተዋል::

ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ተጠያቂዎች ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ ከታቀፉት መካከል ቢያንስ ከፊሉ ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት አጠያያቂ ነው::

ሰንጠረዥ 18 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል እንደሆነ ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ ፤

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ከፍተኛ | 14 | 30.4 |
| ለ | መካከለኛ | 23 | 50 |
| ሐ | ዝቅተኛ | 9 | 19.6 |
| ድ ም ር | | 46 | 100 |

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው 23 /50 % / መላሾች ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት መካከለኛ መሆኑን ሲያመለክቱ 14 /30.4 %/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል። ቀሪዎቹ 9/19.6 %/ መላሾች በበኩላቸው ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡትን የትኩረት ደረጃ እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሶስቱ የትምህርት ባለሞያዎች ይዘቶቹ በአጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት ከፍተኛውን ትኩረት እንደሚሰጡና የቅድሚያ ትኩረታቸውም የቋንቋውን ትምህርት በብቃት መስጠት መሆኑን ሲገልፁ ቀሪው አንድ የትምህርት ባለሞያ ግን ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ባመዛኙ ቋንቋውን ለማስተማር ካላቸው ተገቢነት ጋር ተለይቶ የማይታይ መሆኑን በማመልከት እንደተገቢነታቸው ሁሉ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡትም ትኩረት አመርቂ አለመሆኑን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ተጠያቂዎች የሰጡት መልስ እንደሚያመለክተው የይዘቶቹ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በቋንቋው ትምህርት ላይ ነው ለማለት እንደማያስደፍር መረዳት ይቻላል።

ሰንጠረዥ 19 ይዘቶቹ የትምህርቱን አላማዎች ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ያስችላሉ | 13 | 28.3 |
| ለ | አያስችሉም | 8 | 17.4 |
| ሐ | በከፊል ያስችላሉ | 25 | 54.3 |
| ድ ም ር | | 46 | 100 |

ከላይ እንደተመለከተው 25 /54.3 % / መላሾች በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የትምህርቱን አላማ በከፊል ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን ሲያመለክቱ 13/28.3 %/ መላሾች ደግሞ ሁሉም ይዘቶች አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ ጠቀሜታና ብቃት እንዳላቸው ገልጸዋል። ቀሪዎቹም 8/17.4 %/ መላሾች በበኩላቸው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች በሙሉ አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ አለመሆናቸውን አመልክተዋል።

በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የቋንቋውን ትምህርት አላማ ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ይዘቶቹ ሙሉ ለሙሉ ለማለት ባይቻልም ባመዛኙ አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ብቃት አላቸው ብሎ ለመናገር እንደሚያስደፍር ሶስቱ የትምህርት ባለሞያዎች ሲገልጹ ቀሪው አንድ የትምህርት ባለሞያ ግን ይዘቶቹ ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸው ተገቢነትና ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት አናሳ መሆን ለትምህርቱም አላማ የሚሰጡት ትኩረት ችግር ያጣል ብሎ ለመናገር እንደማያስደፍር ገለጸዋል።

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት አብዛኛዎቹ ተጠያቂዎች በሰጡት መልስ እንዳመለከቱት በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች ባጠቃላይ በክፍል ደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች እንዲያሳዩ የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለማስገኘት ያስችላሉ ብሎ ለመደምደም ያዳግታል። አላማዎች

ተመርጠው በተደራጁት ይዘቶች አግባብነት ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል የሚል የጋራ ስምምነት ያለ ቢሆንም አንዳንዴ ግን ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ውጤት ሊገኝ የሚችል መሆኑ ይታወቃል። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲከሰት ደግሞ የችግሩን መንስኤ በመለየት መፍትሄ መሻቱ ተገቢ በመሆኑ ቀጥሎ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ የትምህርቱን አላማዎች ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ ይቀርባል ።

ሰንጠረዥ 20 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የትምህርቱን ዝርዝር አላማዎች በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ ከዳር ለማድረስ የማያስችሉበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አላማዎቹና ይዘቶቹ ዝምድና የሌላቸው በመሆኑ | 7 | 21.2 |
| ለ | ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን የማይመጥኑ መሆናቸው | 10 | 30.3 |
| ሐ | ይዘቶቹ አላማዎቹ ን ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ያደረጃጀት ብቃት ስለሚያንሳቸው | 16 | 48.5 |
| መ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | --- | --- |
| ድ ም ር | | 33 | 100 |

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ ብቃት እንደሌላቸው በመግለጽ ምላሽ የሰጡ ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ለይተው እንዲያመለክቱ ለቀረበላቸው ጥያቄ 16/48.5 %/ መላሾች የይዘቶቹ ያደረጃጀት ጉድለት አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ብቃት እንዳሳጣቸው ሲገልጹ 10/30.3 %/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን የሚመጥኑ ባለመሆናቸው

አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ አያስችሉም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ቀሪዎቹ 7/21.2 ℅/ መላሾች በበኩላቸው የይዘቶቹና የአላማዎቹ ዝምድና ማጣት አላማዎቹን ከዳር ለማድረስ እንዳይችሉ ያደረጋቸው መሆኑን አመልክተዋል።

ይዘቶች እርስ በርስ ሊደጋገፉ በሚችሉበት ውጤታማ መንገድ ሊደራጁ ካልቻሉ አስራ ስድስቱ መላሾች እንዳመለከቱት የተቀናጀ ውጤትና የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችል ብቃት አይኖራቸውም። በሌላም በኩል አስሩ መላሾች እንደገለጹት የይዘቶች የክፍል ደረጃውን አለመመጠን ለአላማዎች ከግብ አለመድረስ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ አንደኛውና ግንባር ቀደሙ ነው። የክፍል ደረጃውን ባልጠበቀ ይዘት ከተማሪው ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ አይነት መጠበቅ የሚቻል አይመስልም። ሰባቱ መላሾች እንደገለጹት ደግሞ የአላማና የይዘት ስምረት መታጣት ለታለመው ግብ ስኬታማ አለመሆን ሌላው አብይ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። ይዘቶች ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው ትምህርት በኃላ ያሳያሉ ተብሎ የሚገመተውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለማሳየት እንዲችሉ በመሳሪያነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ ከተነደፈው አላማ ጋር ዝምድና የሌላቸውን ይዘቶች እንዲማሩ የተደረጉ ተማሪዎች ሊያሳዩ የሚችሉት የባህሪ ለውጥ አይነት ከተነደፈው አላማ የተለየ እንደሚሆን ይታወቃል። ይህ ደግሞ የትምህርቱን ሂደት ውጤታማነት ለመመዘንና ከምዘናውም ውጤት ተነስቶ የማሻሻያ እንቅስቃሴ ለማካሄድም ሆነ ቀጣዩን የትምህርት ፕሮግራም ለመንደፍ አመቺነት የለውም።

ሰንጠረዥ 21 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-
ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችን አደረጃጀት
ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ
መግለጫ ፣

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ከቀላል ወደ ከባድ የሚጓዝ ነው። | 3 | 6.5 |
| ለ | የደረጃ ልዩነት ሳያሳይ የሚጓዝ ነው። | 3 | 6.5 |
| ሐ | ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት እንዲሆን በሚያስችል መንገድ የተዋቀረ ነው። | --- | --- |
| መ | ከቀላል ወደ ከባድ የሚያስኬደውን ያደረጃጀት መርህ የተከተለ አይደለም። | 19 | 41.3 |
| ሠ | 'ሀ ' ና 'ሐ' ትክክል ናቸው። | 21 | 45.7 |
| ረ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | --- | --- |
| ድ ም ር | | 46 | 100 |

ከላይ እንደተመለከተው የይዘቶቹን አደረጃጀት አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ 21/45.7 %/ መላሾች ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ የሚጓዙ፣ ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት እንዲሆን በሚያስችል መንገድ የተዋቀሩ ናቸው በማለት ምላሽ የሰጡ ሲሆን 19/41.3 %/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ የሚያስኬደውን ያደረጃጀት መርህ ተከትለው አለመደራጀታቸውን ገልጸዋል። 3/6.5%/ መላሾች በበኩላቸው ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ የሚጓዝ አደረጃጀት እንደተከተሉ ሲያመለክቱ ሌሎች 3/6.5 %/ መላሾ ደግሞ ይዘቶቹ የደረጃ ልዩነት ሳያሳዩ የሚጓዙ መሆናቸውን በማመልከት ምላሽ ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች የይዘቶቹን አደረጃጀት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በቅርቡ ከዘጠነኛ ክፍል እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ለተዘጋጁት አማርኛቋንቋ ማስተማሪያ መጻህፍት የመምህሩን መምሪያ በማዘጋጀታቸው የይዘቶቹን አደረጃጀት ከስር መሠረቱ ለማየት የቻሉ መሆኑን በመግለጽ ይዘቶቹም ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጥል የሚያስኬደውን ያደረጃጀት መርህ ተከትለው መደራጀታቸውን እንዳስተዋሉ ሶስቱ የትምህርት ባለሞያዎች ሲገልጹ፣ ቀሪው አንድ የትምህርት ባለሞያ ግን ይዘቶቹ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም መጠነኛ የአደረጃጀት ችግር ሊኖርባቸው እንደሚችል አመልክተዋል።

ከላይ የቀረበው መረጃ ይዘቶቹ የይዘት አደረጃጀት መርህን ተከትለው የተደራጁ መሆንና አለመሆናቸውን ለመለየት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም ። ከመጠይቁ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ይዘቶቹ የይዘት አደረጃጀት መርህን ተከትለው የተደራጁ መሆናቸውን በማመልከት ምላሽ የሰጡ ሃያ አራት ተጠያቂዎች ሲሆኑ፣ ይዘቶቹ የደረጃ ልዩነት እንደማያሳዩና የይዘት አደረጃጀት መርህንም ተከትለው የተደራጁ አለመሆናቸውን በማመልከት ምላሽ የሰጡ ደግሞ ሀያ ሁለት መሆናቸው የትኛውንም መልስ በአምንታ ለመቀበል የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም።

ከመጠይቅና ከቃለ መጠይቅ ከተገኘው ውጤት በተጨማሪ ቫሌትና ሪኒ /1972/ የትምህርት አላማዎችንና ሙከራዎችን በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ከፋፍሎ ለማደራጀት የተጠቀሙበትን ያከፋፈል ስልት በመስፈርትነት በመጠቀም የይዘቶቹን አደረጃጀት ብቃት ለመመርመር ተሞክሯል። ብሎም /1971:22/ እንደሚያስረዱት ይዘቶች በራሳቸው ፍቼ አልባ ከመሆናቸው ባሻገር ተማሪው እንዲያሳየው የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለማሳየት የማይችሉ በመሆናቸው

በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በተቀመጡበት ሁኔታ ወስዶ የአደረጃጀታቸውን ብቃት ለመለካት አመቺ አይደለም። ተማሪዎች ለትምህርት በቀረቡ ይዘቶች አማካኝነት እንዲያከናውኑ የሚፈለገው ተግባር ይዘቶች ህይወት ዘርተው የሚታዩበትና ምንነታቸውም የሚገለጥበት መንገድ በመሆኑ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችን በተግባራዊ መገለጫቸው አማካኝነት የአደረጃጀታቸውን ብቃት ለመመዘን የተሞከረ ሲሆን ይህንንም በአባሪ "ሠ" ላይ ይመለከቷል።

በአባሪ "ሠ" ላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካኝነት 280 ተግባራትን እንዲያከናውኑ ተደርጓል። ከነዚህም ተግባራት ውስጥ አንድ መቶ አስራ ሁለቱ በዕውቀት፣ ሰባ አንዱ በሽግግር ፣ አርባ ዘጠኙ በተግባቦት፣ አርባ ስምንቱ ደግሞ በትችት የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው። ይህም የትንተና ውጤት ለየትምህርት ክፍሉ ሚዛናዊ ትኩረት አለመስጠቱን ያሳየ ከመሆኑ ባሻገር የይዘቶቹም አደረጃጀት ብቃት እንደሌለው አመልክቷል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ተማሪዎች ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካኝነት ከ280 ያላነሱ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ተደርጓል። የእነዚህንም ተግባራት አደረጃጀት ብቃት በሁለት መንገድ ለማየት ተሞክሯል። የመጀመሪያው በአጠቃላይ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያሉትን ተግባራት አደረጃጀት ብቃት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በያንዳንዱ ይዘት አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ በተፈለጉት ተግባራት መካከል ያለውን የአደረጃጀት ብቃት ነው ለመመርመር የተሞከረው። በዚህም መሠረት በአጠቃላይ ተግባራቱ መካከል የታየው አደረጃጀት ብቃት እንደሌለው ትንተናው አመልክቷል። ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ከቀላል፣ ቅርብና አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ተግባራት በመጀመር በሂደትም ወደ ከባድ፣ ሩቅና ተናጥል የቋንቋ ትምህርት ተግባራት የሚያደርሳቸውን ያደረጃጀት መርሀ ተከትለው አልተደራጁም። ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ተግባርን እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸውን ይዘት ከተማሩ በኃላ ወዲያው በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ተግባርን እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸውን ይዘት እንዲማሩም ተደርገዋል። ይህን መሰሉም አደረጃጀት በማስተማር መማሩ ሂደት ላይ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

በሌላም በኩል በእያንዳንዱ ይዘት አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ በተደረጉት ተግባራትም መካከል ያለው አደረጃጀት ችግር እንዳለበት የታየ ቢሆንም

በጣም ጥቂት በሆኑ ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ግን የይዘት አደረጃጀትን መርህ ተከትለው እንደተደራጁ ለመገንዘብ ተችሏል። ከእነዚህም ይዘቶች ውስጥ " ሰምና ወርቅ ፣ ህብር፣ ምርምር ቅኔ " በሚሉት ንዑሳን ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ቫሌትና ሪኒ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችና ሙከራዎች " እውቀት ሽግግር - ተግባቦት - ትችት " በሚለው ስልት መሠረት ሊደራጁ ይገባል በማለት ያስቀመጡትን ያደረጃጀት ስልት ተከትለው ተደራጅተዋል። ከዚህም በተጨማሪ " የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት " በሚለው ይዘት አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት " ተግባቦት" የሚለውን የትምህርት ክፍል በመዝለል " እውቀት - ሽግግር - ትችት " የሚለውን አካሄድ ተከትለው የተደራጁ ቢሆንም ከሌሎቹ ተግባራት የተሻለ አደረጃጀት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

"ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት ፣የቃል ፣የሐረግና የአረፍተ ነገር ልዩነት፣ የሆሄያትና የቃላት በስርአት መደርደር የትርጉም ለውጥ ማምጣት፣ የአያያዦች አጠቃቀም " በሚሉት ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተፈለጉት ተግባራት ከእውቀት የትምህርት ክፍል ወደ ሽግግር የትምህርት ክፍል የሚያስኬደውን ያደረጃጀት ስልት ተከትለው የተደራጁ ሲሆን " ከተጨማሪ ማብራሪያ /አፔንዴክስ/ የመረጃ ሐሳቦችን ማግኘት " በሚለው ይዘት አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ደግሞ ከተግባቦት የትምህርት ክፍል ወደ ትችት የትምህርት ክፍል የሚያስኬደውን ያደረጃጀት ስልት ተከትለው ተደራጅተዋል። ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አምስት ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት የእድገት ሂደታቸውን ጠብቀው ከዝቅተኛ የትምህርት ክፍል ተግባራት ወደ ከፍተኛ የትምህርት ክፍል ተግባራት በመሸጋገር ተደራጅተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ " በአሰሳ አነባበብ የሚፈለጉ ነጥቦችን ማግኘት፣ ከፎቶ ግራፍ የመረጃ ሃሳቦችን ማግኘት፣ ሪፖርት አቀራረብ፣ አንድን ርእስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ " በሚሉት ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ሽግግር የሚለውን የትምህርት ክፍል በመዝለል ከእውቀት የትምህርት ክፍል ወደ ተግባቦት የትምህርት ክፍል

የሚያስኬደውን ያደረጃጀት ስልት ተከትለው የተደራጁ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታም" ሁኔታዎችን ተመልከቶ ነው እያሉ መደምደም" በሚለው ይዘት አማካኝ ነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ተግባቦት የሚለውን የትምህርት ክፍል በመዝለል ከሽግግር የትምህርት ክፍል ወደ ትችት የትምህርት ክፍል የሚያስኬደውን ያደረጃጀት ስልት ተከትለው ተደራጅተዋል። ምንም እንኳ በነዚህ ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የተደረጉት ተግባራት ከመነሻው የትምህርት ክፍል ቀጥሎ የሚመጣውን የትምህርት ክፍል ዘለው ወደ ቀጣዩ የትምህርት ክፍል እንዲሸጋገሩ ተደርገው የተደራጁ ቢሆንም ከሌሎቹ የትምህርት ተግባራት አኳያ የተሻለ አደረጃጀት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

ባጠቃላይም ከላይ እንደተገለጸው ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ ለትምህርት በቀረቡላቸው ይዘቶች አማካኝነት እንዲያከናውኑ ከተደረጉት 280 ተግባራት ውስጥ በአርባ አምስቱ ተግባራት

መካከል ብቻ መጠነኛ ያደረጃጀት ብቃት መታየቱ የቱን ያህል ይዘቶቹ የአደረጃጀት ችግር እንዳለባቸው ያሳያል።

ሻሌትና ሪኒ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችንና ሙከራ በሚል ስያሜ የአላማዎቹን ተግባራዊነት ለመቆጣጠር እንዲችሉ ያስቀመጧቸውን ተግባራት በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ለመከፋፈል በተጠቀሙበት ስልት አማካኝነት ለማሳየት እንደሞከሩት ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርት ከተማሩ በኃላ ሊያሳዩ የሚገባቸውን የባህሪ ለውጥ አይነትም ሆነ የአላማዎቹን ተግባራዊነት ለማሳየት የሚያከናውኗቸው ተግባራት እንደ እድገት ደረጃቸው ተለይተውና ተወስነው ሊደራጁ ይገባል። ከነሱም ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው ሜካኒካዊ ክሂል፣ ዕውቀት፣ ሽግግር፣ ተግባቦትና ትችት የሚለው አከፋፈል ተማሪዎች እንዲያሳዩ የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት የእድገት ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ይህም አከፋፈል ተማሪዎች ከአንዱ የባህሪ ለውጥ አይነት ወደ ሌላው የባህሪ ለውጥ አይነት ሲሸጋገሩ እድገቱን በጠበቀ አካሄድ እንዴት መከናወን እንዳለበት ያሳያል። ይህም ማለት ለምሳሌ፣ ተማሪዎች በዕውቀት ደረጃ ላይ የሚገኝ የባህሪ ለውጥ አይትን እንዲያሳዩ የሚያስችላቸውን ይዘት ከተማሩ በኃላ እድገቱን በጠበቀ አካሄድ በሚቀጥለው የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ የባህሪ ለውጥ አይነት ለማሳየት የሚያስችላቸውን ይዘት ሊማሩ ይገባል። ይህን አይነቱም አቀራረብ በተማሪዎች ላይ መደናገር ከመፍጠር የሚያድን ከመሆኑ ባሻገር በራስ የመተማመን ስሜትን በማዳበር በትምህርቱ ሂደት ንቁተሳታፊ ያደርጋቸዋል።

ሰንጠረዥ 22 የይዘቶቹ አደረጃጀት ተከታታይነት የተጠበቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ.ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተጠብቋል | 6 | 13 |
| ለ | አልተጠበቀም | 19 | 41.3 |
| ሐ | በከፊል ተጠብቋል | 21 | 45.7 |
| | ድ ም ር | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት 21/45.7 ％/ መላሾች የይዘቶቹ ተከታታይነት በከፊል የተጠበቀ መሆኑን ሲያ መለከቱ 19/41.3 ％/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹ

ተከታታይነታቸው አለመጠበቁን ገልጸዋል። ቀሪዎቹ 6/13 ％/ መላሾች የይዘቶቹ ተከታታይነት ሙሉ ለሙሉ መጠበቁን አመልክተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች የይዘቶቹ ተከታታይነት መጠበቅ ወይም አለመጠበቁን እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሙሉ ለሙሉ ነው ለማለት ባይቻልም ይዘቶቹ ባመዛኙ ተከታታይነታቸው ተጠብቆ መደራጀታቸውን በማመልከት ምላሽ ሰጥተዋል።

ከተሰበሰቡት መረጃዎች ትንተና የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት መላሾችም ሆኑ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች እንዳመለከቱት የይዘቶቹ ተከታታይነት በከፊል የተጠበቀ መሆን ባደረጃጀታቸው በኩል ችግር እንዳለባቸው ያመለክታል።

ከላይ በተሰበሰበው መረጃ ለማመልከት እንደተሞከረው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች ተከታታይነት የተጠበቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የይዘቶቹ ተከታታይነት በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ መጠበቁን በማመልከት ምላሽ የሰጡ የይዘቶቹን ተከታታይነት መጠበቅ ሊያመለክቱ የሚችሉ ጥቂት ምሳሌዎች እንዲሰጡ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሊሰጥ የሞከረ አንድም ተጠያቂ አልነበረም።

ሠንጠረዥ 23 የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት መጠበቅ ወይም አለመጠበቁን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ.ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተጠብቋል | 6 | 13 |
| ለ | አልተጠበቀም | 24 | 52.2 |
| ሐ | በከፊል ተጠብቋል | 16 | 34.8 |
| | ድ ም ር | 46 | 100 |

ከላይ እንደተመለከተው የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት መጠበቅ ወይም አለመጠበቁን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ 24/52.2 በመቶ/ መላሾቹ የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት አለመጠበቁን ሲያመለክቱ 16/34.8 በመቶ/ መላሾች ደግሞ የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት በከፊል መጠበቁን ገልጸዋል:: ቀሪዎቹ 6/13 በመቶ/ መላሾች በበኩላቸው ይዘቶቹ ተለጣጣቂነታቸው ተጠብቆ መደራጀታቸውን አመልክተዋል::

በሌላ በኩል ደግሞ በሥርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች ተለጣጣቂነት ተጠብቆ መደራጀታቸውን ወይም አለመደራጀታቸውን እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሶስቱ የትምህርት ባለሞያዎች ይዘቶቹ ተለጣጣቂነታቸው ተጠብቆ መደራጀታቸውን ሲያመለክቱ ቀሪው የትምህርት ባለሞያ ግን ይዘቶቹ ተለጣጣቂነታቸው ሙሉ ለሙሉ ተጠብቆ ተደራጅተዋል ብለው ምላሽ ለመስጠት እንደሚቸገሩ በማመልከት ምላሽ ሰጥተዋል::

ከላይ የተገለጸው መረጃም ሆነ መርሀ ትምህርቱን በመተንተን የተገኘው ውጤት ይዘቶቹ ልጥጥቃቸው ተጠብቆ ያልተደራጁ መሆኑን አመልክቷል:: ቀደም ሲል የይዘቶቹን አደረጃጀት አስመልክቶ ለቀረበውጥያቄ ምላሽ ለመስጠት መርሀ-ትምህርቱ በተመረመረበት ወቅት የተገኘው ውጤት ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከአጠቃላይ ወደተናጥል ወዘተ... የሚያስኬደውን ያደረጃጀት መርሀ ተከትለው አለመደራጀታቸውን ያመለከተ ሲሆን በመጠይቁም አማካኝነት የተገኘው መረጃ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሆኖ ተገኝቷል::

ሰንጠረዥ 24 የይዘቶቹን ቅደም ተከተል ለዋውጠው ቢያስተምሩ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አለ | 17 | 37 |
| ለ | የለም | 29 | 63 |
| ድ ም ር | | 46 | 100 |

የይዘቶቹን ቅደም ተከተል በመለዋወጥ ለማስተማር ቢሞክሩ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ አለመኖሩን በማመልከት 29/63 %/ ተጠያቂዎች መልስ ሲሰጡ 17/37 %/ ተጠያቂዎች ደግሞ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መለዋወጥ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያስከትል ገልጸዋል።

የይዘቶቹን ቅደም ተከተል ለዋውጠ ለማስተማር ቢሞክር በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መለዋወጥ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ አለመኖሩን በማመልከት ምላሽ የሰጡ ተጠያቂዎች ብዛት ቀደም ሲል የይዘቶቹን ተለጣጣቂነት አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ ይዘቶቹ ልጥጥቃቸው አለመጠበቁን በማመልከት ምላሽ ከሰጡት ጋር መመሳሰል ሲገባው በአምስት መላሾች ልዩነት አሳይቷል። ይህ ደግሞ የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት አልተጠበቀም በማለት ምላሽ የሰጡትን ሃያ አራት ተጠያቂዎች በአምስት በማሳደግ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መፋለስ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ ችግር እንደማያስከትል በማስመልከት ምላሽ የሰጡትን ተጠያቂዎች

ሃያ ዘጠኝ እንዲሆኑ አድርጓል። ይህም መረጃ የይዘቶቹ ልጥጥቅ በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ መጠበቁን በማስመልከት ምላሽ የሰጡ አምስት ተጠያቂዎች የሐሳብ ለውጥ ማድረጋቸውን ያሳያል። በአንድ የማስተማሪያም ሆነ የመማሪያ መሳሪያ ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች በከፊልም ይሁን ሙሉ ለሙሉ የተጠበቀ የአደረጃጀት ብቃት ካላቸው ቅደም ተከተላቸውን ለዋውጦ ለማስተማር ቢሞክር በከፊልም እንኳ ቢሆን የተጠበቀው ተለጣጣቂነታቸው መፋለሱ የማይቀር በመሆኑ የይዘቶቹን ቅደም ተከተል

በመለዋወጥ ለማስተማር ቢሞከር በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል መሆኑን በማስመልከት አስራ ሰባት ሳይሆን ሃያ ሁለት ተጠያቂዎች ነበሩ ምላሽ መስጠት የሚገባቸው።

ሰንጠረዥ 25 የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መለዋወጥ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር የማይችልበትን ምክንያት ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ተማሪው የትኛውንም ይዘት አስቀድሞ ቢማር ለውጥ ስለሌለው ነው። | 2 | 6.9 |
| ለ | ይዘቶቹ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ነው። | 4 | 13.8 |
| ሐ | አንዱ ለሌላው መሠረት በመሆን ያልተደራጁ በመሆናቸው ነው። | 23 | 79.3 |
| መ | ሁሉም መልስ ናቸው። | -- | --- |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | | |
| ድ ም ር | | 29 | 100 |

በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ይዘቶች ቅደም ተከተል ለዋውጦ ለማስተማር ቢሞከር በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መለዋወጥ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ የለም በማለት መልስ የሰጡ የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መለዋወጥ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር የማይችልበትን ምክንያት እንዲያሳውቁ ለቀረበላቸው ጥያቄ 23/79.3 %/ መላሾች ይዘቶቹ አንዱ ለሌላው መሠረት በመሆን ያልተደራጁ በመሆናቸው የቅደም ተከተላቸው መፋለስ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ እንደሌለ ሲያመለክቱ 4/13.8%/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ የቅደም ተከተላቸው መፋለስ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ እንደማይኖር ገልጸዋል። ቀሪዎቹ 2/6.9%/ መላሾች

ተማሪው የትኛውንም ይዘት አስቀድሞ ቢማር ለውጥ ስለሌለው የይዘቶቹ ቅደም ተከተል መፋለስ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ አለመኖሩን አመልከተዋል።

የይዘት አደረጃጀት መርሆዎችን ተከትለው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ ፣ ከአጠቃላይ ወደተናጥል ወዘተ በሚያስኬድና ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት ለመሆን በሚያስችል መንገድ የተደራጁ ይዘቶች ቅደም ተከተል መፋለስ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ለያሳድር እንደሚችል ይታመናል።

ቀደም ሲል መርሀ-ትምህርቱን በመመርመር የተገኘው ውጤትም ሆነ ከላይ የተገኘው የመጠይቅ መረጃ እንደሚያሳየው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች የይዘት አደረጃጀት መርህን ተከትለው ባለመደ ራጀታቸው የቅደም ተከተላቸው መፋለስ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ እንዳይኖር አድርጓል።

ሰንጠረዥ 26 ይዘቶቹን የሚያስተምሯቸው እንዴት እንደሆነ ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | አደረጃጀታቸው ሳይለወጥ እንዳለ ነው። | 4 | 8.7 |
| ለ | የራሴንቅደም ተከተል በመስጠት ነው። | 26 | 56.5 |
| ሐ | የራሴን ይዘት በማዘጋጀት ነው። | --- | --- |
| መ | አንዳንዴ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ያላቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ አንዳንዴ ደግሞ የራሴን ቅደም ተከተል በመስጠት ነው። | 15 | 32.6 |
| ሠ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | 1 | 2.2 |
| | ድ ም ር | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት 26/56.5%/ መላሾች ይዘቶቹን የሚያስተምሯቸው የራሳቸውን ቅደም ተከተል በመስጠት መሆኑን ሲገልጹ 15/32.6%/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹን አንዳንዴ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ያላቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ አንዳንዴ ደግሞ የራሳቸውን ቅደም ተከተል በመስጠት

እንደሚያስተምሯቸው አመልክተዋል። 4/8.7%/ መላሾች በበኩላቸው ይዘቶቹን በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያላቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንደሚያስተምሯቸው ሲገልጹ ቀሪው 1/2.2 %/ ተጠያቂ ደግሞ ካለው በመንደርደርና የራሳቸውን አክለው በማስፋፋት እንደሚያስተምሩ በጽሁፍ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

ከላይ እንደተመለከተው ይዘቶቹን በከፊልም ይሁን ሙሉ ለሙሉ አደረጃጀታቸውን በመለወጥ እንደሚያስተምሩ በመግለጽ 41/89.1 %/ ተጠያቂዎች ምላሽ መስጠታቸው ይዘቶቹ የይዘት አደረጃጀት መርህን ተከትለው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጥል፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ ሊያስኬድና ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት ሊሆን በሚያስችል መልኩ አለመደራጀታቸውን ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 27 መምህራን በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ የራሳቸውን ቅደም ተከተል በማውጣት ይዘቶቹን ለማስተማር የወሰኑበትን ምክንያት እንዲገልፁ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ለማስተማር እንዲቀለኝ በማሰብ | 6 | 16.2 |
| ለ | ከቀላል ወደ ከባድ እንዲሄድ ለማድረግ | 30 | 81.1 |
| ሐ | ጠቃሚጠቃሚዎቹን ለመምረጥ | 1 | 2.7 |
| መ | ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ | | |
| | ድ ም ር | 37 | 100 |

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ይዘቶች እንዴት እንደሚያስተምሯቸው ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ በከፊልም ይሁን ሙሉ ለሙሉ የራሳቸውን ቅደም ተከተል በመስጠት እንደሚያስተምሩ በማመልከት ምላሽ የሰጡ አርባ አንድ ተጠያቂዎች ይዘቶቹ በመጽሃፉ ውስጥ ያላቸውን አደረጃጀት ትተው በከፊልም ይሁን ሙሉ ለሙሉ የራሳቸውን አደረጃጀት በመስጠት ለማስተማር

ለምን እንደወሰኑ ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ 30/81.1 %/ መላሾች ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ እንዲሄዱ ለማድረግ የሚለውን ምላሽ ሲሰጡ 6/16.2 %/ መላሾች ደግሞ ለማስተማር እንዲቀላቸው በማሰብ ያደረጉት መሆኑን አመልክተዋል። ቀሪው

1/2.7%/ ተጠያቂ በበኩላቸው ጠቃሚ ጠቃሚዎቹን ለመምረጥ ሲሉ የይዘቶቹን ቅደም ተከተል ለመለዋለጥ የተገደዱ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉትን ይዘቶች እንዴት እንደሚያስተምሩ ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ የነበራቸውን አደረጃጀት ሳይከተሉ እንደሚያስተምሩ በማመልከት ምላሽ የሰጡ 41/89.1 %/ ተጠያቂዎች ምክንያታቸውን እንዲገልጹ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ የሰጡ ሰላሳ ሰባት ብቻ ናቸው። ይህን የመሰለው የአሀዝ ልዩነት ቢታይም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ተጠያቂዎች የሰጡት ምላሽ የይዘቶቹ አደረጃጀት ችግር የሚታይበት መሆኑን ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 28 ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ካሉ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር መደጋገፍና አለመደጋገፋቸውን ለመለየት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | አማራጭ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ | ይደጋገፋሉ | 40 | 87 |
| ለ | አይደጋገፉም | 6 | 13 |
| ድ ም ር | | 46 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት 40/87 %/ መላሾች ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚገኙ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ይደጋገፋሉ በማለት የሰጡት ምላሽ በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ክፍል እንደተገለጸው፣ ውህደት የትምህርት መስኮችን መተጋገዝና መደጋገፍ የሚያጎለብት፣ ተማሪው በሚቀርብለት ትምህርታዊ መሠረታዊ ነገሮች እየተረዳ በተለያዩ የትምህርት መስኮች አማካኝነት የገነባውን ባህሪ እንዲያዋህድ የሚያግዝ ያደረጃጀት መስፈርት መሆኑን በማመልከት የመስኩምሁራን /ታይለር 1950: 299/ ከሰጡት ገለፃ ጋር ይዘቶቹ የሚስማማ አደረጃጀት እንዳላቸው

ያመለክታል። ቀሪዎቹ 6/13 %/ መላሾች ደግሞ ይዘቶቹ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር የማይደጋገፉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞዎች ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚገኙ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ጎናዊ ቅንብራቸው ተጠብቆ የተደራጁ መሆን ወይም አለመሆናቸውን እንዲለዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚገኙ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ውህደት እንዲኖራቸው ተደርጎ መደራጀታቸውን ሁለቱ የትምህርት ባለሞያዎች ሲገልጹ ቀሪዎቹ ሁለት የትምህርት ባለሞያዎች ግን የይዘቶቹ ጎናዊ ቅንብር ተጠብቋል ብለው እንደማያምኑ በማመልከት ምላሽ ሰጥተዋል።

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች በክፍል ደረጃው ከሚሰጡ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር እንደሚደጋገፉ በማመልከት ምላሽ የሰጡ መደጋገፉን የሚያሳዩት ከየትኛው የትምህርት አይነት ጋር እንደሆነ በጽሁፍ እንዲያመለክቱ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 29 ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚሰጡ ከየትኞቹ የትምህርት አይነቶች ጋር መደገገፍን እንደሚያሳዩ ለይቶ በማመልከት የተሰጠ ምላሽ መግለጫ፣

| ተ. ቁ. | የቀረቡ መልሶች | መላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ከተረትና ምሳሌ፣ ከቅኔ ጋር | 14 | 35 |
| 2 | ከስርአተ ቋንቋ አንፃር ነው | 1 | 2.5 |
| 3 | እርሻ፣ ሂሣብና የመዝገብ አያያዝ | 3 | 7.5 |
| 4 | ከሂሣብ፣ከእንግሊዘኛ፣ከሳይንስ፣ ከታሪክ ትምህርቶች | 8 | 20 |
| 5 | ትምህርቱ በጣም የሚገናኘው ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ነው | 9 | 22.5 |
| 6 | ግጥም፣ ስርአተ ነጥብ፣ ቁጥር ወዘተ | 4 | 10 |
| 7 | ከየትኛውም የትምህርት ዘርፍ ጋር | 1 | 2.5 |
| ድ ም ር | | 40 | 100 |

ከላይ በቀረበው መረጃ መሠረት በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች በክፍል ደረጃው ከሚገኙ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ጎናዊ ቅንብራቸው ተጠብቆ መደራጀታቸውን በማመልከት ምላሽ ከሰጡ

አርባ ተጠያቂዎች ውስጥ 21/52.2 %/ መላሾች ብቻ ከተጠየቀው ጥያቄ ጋር የሚሄድ መልስ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 19/47.5%/ መላሾች ግን በራሱ በቋንቋው ትምህርት ይዘቶች መካከል ያለውን ቀጥተኛ ትንብር ያመለኩቱ ከመሆኑ ባሻገር አንዳንዶቹም ከመርሀ-ትምህርቱ በመውጣት ከተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ለትምህርት የቀረቡ ይዘቶችን ጠቅሰዋል። ይህም የመረጃ ውጤት እንደሚያሳየው ከጥያቄው ጋር የሚሄድም ሆነ ጥያቄውን የማይመለከት ምላሽ የሰጡ ተጠያቂዎች ቁጥር መቀራረብ ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚሰጡ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ጎናዊ ትንብራቸው ተጠብቋል ለማለት የሚያስደፍር ሆኖ አልተገኘም።

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

### 4.2.1. በ10ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች አንዳደፍ ብቃት

በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች ከእያንዳንዱ የቋንቋው ትምህርት በኃላ ተማሪዎች ያሳያሉ ተብሎ የታሰበውን የባህሪ ለውጥ አይነት በግልጽ በማስቀመጥ ተማሪዎች ለአላማዎቹ ተግባራዊነት የድርሻቸውን እንዲወጡ በሚያስችል መልኩ ባለመነደፋቸው በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉና መገለጫ መንገዳቸውንም የያዙ ባለመሆናቸው ከተማሪው የሚጠበቀው የባህሪ ለውጥ አይነት መታየትና አለመታየቱን ለመገምገም የሚያስችል ብቃት እንደሌላቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። በምዕራፍ ሁለት የቀረበው የመስኩ ምሁራን ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ እንደሚያሳየው ዝርዝር አላማዎች የመግለጫ መንገዳቸውን ካልያዙ ተግባራዊነታቸውን ለመቆጣጠርም ሆነ የማስተማር መማሩን ሂደት ውጤታማነት ለመገምገም የማይቻል ከመሆኑ ባሻገር ከግምገማ ሂደት ከሚገኘው ውጤት በመነሳት የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል እድል እንዳይኖር ያደርጋል።

በሌላም በኩል ዝርዝር አላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሰረተ አንዳደፍ የሌላቸው በመሆኑ ተማሪች በሂደት ወደተሻለ የዕውቀት ደረጃ እንዲረማመዱ የሚያስችሉ አይደሉም። ይህም በበኩሉ በማስተማር-መማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ይታመናል። ይሄውም ማንኛውም ትምህርታዊ እንቅስቃሴ ባደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከአጠቃላይ ወደተናጥል የሚያስኬደውን መርህ ተከትሎ መጓዝ አለበት የሚለውን ስምምነት ያፈረሱ በመሆናቸውና ተማሪዎችም የእድገትሂደታቸውን ጠብቀው በተደራጁ አላማዎች መሪነት ስለማይማሩ የትምህርቱ ሂደት አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል የሚያጠያይቅ አይሆንም።

ዝርዝር አላማዎቹ ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው የቋንቋ ትምህርት በኃላ ያሳያሉ ተብሎ የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ ተጽፈው አለመቅረባቸውን የጥናቱ የመረጃ ውጤት ትንተና አሳይቷል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ዝርዝር አላማዎቹ በአንድ ጊዜ ብዙ ነገር ሊያሳዩ በሚችሉ ቃላት መነደፋቸው ነው። በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት የቀረበው ትንታኔ እንደሚያስረዳው፣

ሁሉም  አይነት ቃላት ወይም ሀረጎች ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው ትምህርት በኋላ እንዲያሳዩ  የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ አይነት እኩል የመግለጽ ሃይል የላቸውም። በ10ኛም ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች ተነድፈው የቀረቡባቸው ቃላት ያነበባቸው ሁሉ በተረዳቸው መንገድ እንዲተረጉማቸው በመጋበዝ በክፍል ደረጃው በሚያስተምሩ የተለያዩ መምህራን መካከል ወደተለያየ ግብ እስከ ማምራት የሚያደርስ ልዩነት ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ዝርዝር አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት እንደማይሰጡ መርሀ-ትምህርቱን በመተንተን የተገኘው ውጤት አመልክቷል። ዝርዝር አላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች የተዛባ ትኩረት የሚሰጡ ከመሆኑ ባሻገር አላማ ያልተቀረጸለትም አብይ የትምህርት ክፍል ተገኝቷል።

### 4.2.2 በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች አደረጃጀት ብቃት

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤት እንዳመለከተው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ በመመጠን፣ የቋንቋውን ትምህርት አላማ ከዳር በማድረስ፣ ለቋንቋው ትምህርት በሚሰጡት ትኩረትና ቋንቋውን ለማስተማር ባላቸው ተገቢነት ረገድ ያላቸው ብቃት በበቂ ደረጃ ላይ አይገኝም። ይህም ውጤት በዚህ መስክ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት ፍንጭ ሰጪ በመሆን ያገለግላል።

ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት መካከለኛ መሆኑንና አደረጃጀታቸው ደግሞ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣  ከአጠቃላይ ወደተናጠል በሚያስኬደው መርህ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። የይዘቶቹ አደረጃጀት ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት ለመሆን በሚያስችል መልኩ የተዋቀረ አለመሆኑ በይዘቶች መካከል የሚፈለገውን ያህል መደጋገፍ እንዳይኖር እንቅፋት  ሊሆን የሚችል ከመሆኑ ባሻገር ተማሪውም በይዘቶቹ መካከል ዝምድናን በመሻት ሊቸገር እንደሚችል ይታመናል። በሌላም በኩል ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው ይዘቶቹ ተከታታይነታቸውና ተለጣጣቂነታቸው ተጠብቆ

አልተደራጁም። ይዘቶቹ በዚህም የተበላሸ አደረጃጀታቸው ከቀላል ወደ ከባድ፣ እንደገና ተመልሰው ወደ ቀላል የመጓዝ ባህሪን የሚያሳዩ በመሆናቸውመምህራን ይህን ችግር ለመቋቋም የራሳቸውን ቅደም ተከተል በማውጣት ለማስተማር በሚወስዱት እርምጃ ለተዘበራረቀ አሠራር የሚዳርጋቸው ከመሆኑ ባሻገር በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ ከፍተኛ ችግር እንደሚያስከትል ይታመናል።

ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ከሚሰጠው ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ጎናዊ ዝምድና በበቂ ደረጃ ላይ እንደማይገኝ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

<ins>ምዕራፍ አምስት</ins>

<ins>ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳቦች</ins>

## 5.1 ማጠቃለያ

የማስተማሪያ መሳሪያዎች በጥንቃቄ ተዘጋጅተው በተግባር ላይ መዋል ይገባቸዋል። በተግባር ላይ ከዋሉም በኃላ በየጊዜው ሊገመገሙና ጠንካራ ጎናቸው የበለጠ እንዲጎለብት፣ ደካማ ጎናቸው ደግሞ እንዲሻሻል በየወቅቱ ሊጠኑ ይገባል።

አማርኛ በትምህርት አይነትነት መሰጠትና በማስተማሪያ ቋንቋነት ማገልገል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 1984 ዓ.ም. ድረስ የተለያዩ መርሀ ትምህርቶች የተዘጋጁ ቢሆንም ብቃት እንዳልነበራቸው መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሞያዎች ሲተቿቸው ቆይተዋል። በ1984 ዓ.ም. ደግሞ አዲስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች ተዘጋጅተው ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ ውለዋል።

በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎችን አነዳደፍና ይዘቶችን አደረጃጀት ብቃት ለመመርመር የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች ሁለት ሲሆኑ እያንዳንዳቸውም አራት አራት ንኡሳን ጥያቄዎችን ይዘዋል። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

1. በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች ከአላማ አነዳደፍ መርሆዎች አኳያ የተቀረጹ ናቸው ?
    1.1 ዝርዝር አላማዎቹ የክፍል ደረጃውን በመመጠን ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታና በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ ?
    1.2 ዝርዝር አላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነትና መገለጫ መንገዳቸውን የያዙ ናቸው ?
    1.3 ዝርዝር አላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሰረተ አነዳደፍ አላቸው ?
    1.4 ዝርዝር አላማዎቹ ግልጽ ሆነው ቀርበዋል ?

2. በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች የአደረጃጀት ብቃት ይታይባቸዋል ?
   2.1 የይዘቶቹ አደረጃጀት ምን ይመስላል ?
   2.2 የይዘቶቹ ተከታታይነት ተጠብቋል ?
   2.3 የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ?
   2.4 የይዘቶቹ ውህደት ተጠብቋል ?

በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች ከአላማ አነዳደፍ መርሆዎች አኳያ አለመነደፋቸውን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። አላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ብቻ አጠቃላይ በሆነ መልኩ የሚያቀርቡ መሆኑ ተስተውሏል። በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ክፍል እንደተገለጸው ዝርዝር አላማዎች ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት ብቻ ሳይሆን ተማሪው አላማዎቹን ተግባራዊ ለማድረግ መቻሉን ለማሳየት ማከናወን ያለበትን ተግባርና የተግባሩንም የተቀባይነት ደረጃ መለኪያ መስፈርት መያዝ አለባቸው። ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ግን በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ዝርዝር አላማዎች ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት እንኳ ግልጽ በሆነና በማያሻማ መንገድ አያመላክቱም። ለዚህም ዋናው ምክንያት ዝርዝር አላማዎቹ በአንድ ጊዜ ብዙ ነገር ሊሉ በሚችሉ ቃላት ተጽፈው መቅረባቸው ነው። በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ክፍል እንደተገለጸው ዝርዝር አላማዎችን ስንነድፍ በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ሊያስተላልፉ የሚችሉና ተግባር ገላጭ ቃላትን መጠቀም ያስፈልጋል።

በሌላም በኩል የዝርዝር አላማዎቹ አደረጃጀት የተዛባ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። በተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ክፍል ለመግለጽ እንደተሞከረው ለተማሪዎች የሚቀርቡ ትምህርታዊ ዝግጅቶች የእድገት ሂደታቸውን ጠብቀው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጠል የሚያስኬደውን ስልት ተከትለው በመደራጀት ለትምህርት ሊቀርቡ ይገባል። በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር አላማዎች ግን ከላይ ለመግለጽ የተሞከረውን የአደረጃጀት መርህ የተከተሉ ባለመሆናቸው አደረጃጀታቸው ብቃት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ችግር አላማዎቹን ተፈጻሚ ለማድረግ በተመረጡት ይዘቶች አደረጃጀት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የታቀፉት ይዘቶች እንደ ዝርዝር አላማዎቹ ሁሉ የአደረጃጀት ብቃት እንደሌላቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ፣ከአጠቃላይ ወደተናጠል፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ

የሚያስኬደውን ያደረጃጀት መርህ ተከተለው ባለመደራጀታቸው ተከታታይነታቸውም ሆነ ተለጣጣቂነታቸው አልተጠበቀም። በክፍል ደረጃው ከሚሰጡ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶችም ጋር ያላቸው ጎናዊ ዝምድና በበቂ ደረጃ ላይ እንደማይገኝ ከጥናቱ ውጤት ለመረዳት ተችሏል። ይህ ደግሞ በማስተማር መማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ይታመናል። ተማሪዎቹ አደረጃጀታቸው በተዛባ ይዘቶች እንዲማሩ የተደረጉ በመሆኑ በትምህርቱ አቀባበል ላይ ችግር ያስከትልባቸዋል።

## 5.2 የመፍትሄ ሐሳቦች

የ10ኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት አዘገጃጀት ወደተሻለ የጥራት ደረጃ በማሳደግ የማስተማር መማሩ ሂደት በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግና የትምህርቱንም ውጤታማነት ለማጎልበት ከጥናቱ ሙጤት በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰጥ ተዋል።

5.2.1 የአላማ አነዳደፍ መርሆችን ተከትለው ባልተነደፉና የእድገት ተከታታይነታቸውን ጠብቀው ባልተደራጁ ዝርዝር አላማዎች የቋንቋውን ትምህርት ሂደት በመምራት ወደ ውጤት ለመድረስ ስለማይቻል፣ ዝርዝር አላማዎቹ ከአላማ አነዳደፍ መርሆዎች አኳያ እንደገና ተነድፈውና የእድገት ተከታታይነታቸውን ጠብቀው በመደራጀት ሊቀርቡ ይገባል።

5.2.1.1 ዝርዝር አላማዎቹ ከተማሪው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ አይነት፣ በተግባር ተገልጠው የሚታዩበትን ሁኔታና የተቀባይነት ደረጃ መለኪያ መስፈርትን ይዘው እንደገና ሊነደፉ ይገባል።

5.2.1.2 ዝርዝር አላማዎቹ በማያሻማና ግልጽ በሆነ መንገድ፣ ተግባር ገላጭ በሆኑና በአንድ ጊዜ አንድ የባህሪ ለውጥ አይነትን ብቻ ሊያስተላልፉ በሚችሉ ቃላት እንደገና ተጽፈው ሊቀርቡ ይገባል።

5.2.1.3 ዝርዝር አላማዎቹ የእድገት ሂደታቸውን ጠብቀው ከቀላል ወደ ከባድ ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጥል የሚያስኬደውን የአደረጃጀት መርህ መሠረት በማድረግ እንደገና ተደራጅተው መቅረብ ይገባቸዋል።

5.2.2. በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶች የይዘት አደረጃጀት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ እንደገና ተደራጅተው ሊቀርቡ ይገባል።

5.2.2.1. ከተከታታይነት ያደረጃጀት መርህ አኳያ የይዘቶቹ ተከታታይነት ሊስተካከል ይገባዋል።

5.2.2.2. ከቫሌትና ሪኒ ያደረጃጀት ስልት አኳያ የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተስተካክሎ ቢቀርብ ከፍተኛ ጠቀሜታን ያስገኛል።

5.2.2.3 ከውህደት ያደረጃጀት መርህ አኳያ የይዘቶቹ ውህደት ወደሚገባው ደረጃ ከፍ ብሎ እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል።

## አምዶ ቃላት

Analysis ........................ ትንተና

Application ........................ በስራ ላይ ማዋል

Communication........................ ተግባቦት

Comprehension........................ አንብቦ መረዳት

Criticism ........................ ትችት

Evaluation ........................ ግምገማ

Knowledge ........................ ዕውቀት

Recall ........................ ማስታወስ

Reception ........................ መረዳት

Recognition ........................ መገንዘብ

Self-expression........................ እራስን ማግለፅ

Synthesis ........................ ማዋሀድ

Transfer ........................ ሽግግር

<u>ማስታወሻ</u>

1. ሻሱትና ሪኒ ዓሳማዎችንና ሙከራዎችን በተሰያዩ የትምህርት ክፍሎች በመመደብ ክፍሎቹን ለመሰየም የተጠቀሙባቸውን ቃላት ወደ አማርኛ ለመመለስ የተሞከረ ሲሆን የእነዚህም ቃላት የእንግሊዝኛ አቻቸው በአምደ ቃላት ሥር ቀርበዋል፡፡

2. ዓ.ም. የሚል ምህጻረ - ቃል ካልታከለባቸው በስተቀር በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙት ዓመታት ሁሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው፡፡

## <u>የአማርኛ መረጃ መጻሕፍት</u>


ተስፋዬ ሸዋዬ:: 1982:: *የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን የማስተማሪያ ዓላማዎች ትንታኔ::» አዲስ አበባ:: /ያልታተመ/

ትምህርት ሚኒስቴር:: 1984:: <u>የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ</u> /9-11ኛ ክፍል/:: አዲስ አበባ፤ በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት /ት.መ.ግ.ማ.ድ/::

አንተነህ አወቀ:: 1974:: «የሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ይዘት በሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የአማርኛ ቋንቋ ሥርአተ ትምህርት ከ1966 ዓ.ም. ወዲህ::» ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ::

አያሌው አስፋው:: 1986:: «ከ1933 - 1983 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ በአገልግሎት የዋሉ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪ መጻሕፍት ዝርዝር ዓይነትና የይዘት ግምገማ::» ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ጌታቸው አዱኛ:: 1985:: «ለአሥረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ::» ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት::

# BIBILOGRAPHY


Abebe Bekele. 1974 " Some Thought on Bases for Development of Educational Objectives" The Ethiopian Journal of Education. Vol, 7/1,pp25-38.

____________. 1986 " Insight into the Concepts of the Curriculum" The Ethiopian Journal of Education. Vol.10/1, pp.39-58

Allen, J.P.B. 1984. "General- Purpose Language Teaching: A variable Focus Approach" General Engilish Syllabus Design. ELT Document 118. Oxford: Pergamon Press. pp.61-74 .

Barrow, Robin. 1984. Giving Teaching Back to Teachers: A Critical Introduction to Curriculum Theory. London: The Althouse Press.

Bender, M.L. 1976 [et.al .]. Language in Ethiopia. London: Oxford University Press.

Bloom, B.S. 1956 [et.al.]. Taxonomy of Educational Objectives. Hand Book I . Cognitive Domain. New york: David Mckay.

____________. 1971 [ et. al]. Hand Book on Formative and Summative Evaluation of Student Learning. New york: Mc Graw-Hill Inc.

Breen, Michael p. 1984 " Process Syllabus for the Language Class room" General English Syllabus Design. ELT Document 118. Oxford: Pergamon Press, pp. 47-60

Brumfit, C. J. 1984. [ ed. ] General Engilish Syllabus Design. ELT Document 118 Oxford: Pergamon press.

Candlin, christopher N. 1984. " Syllabus Design as a Critical Process" General Engilsh Syllabus Design. ELT Document 118. Oxford: Pergamon Press, pp.29-46.

Caswell, HollisL. and Associates. 1950. Curriculum Improvement in Public School System. New york: Bureau of Publication.

Cunningsworth, Alan. 1984. Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford: Heine mann.

Doll, Ronald C. 1970. Curriculum Improvement: Decision Making and Process. 2nd. ed. U.S.A. : Allyn and Bacon, Inc.

Dubin, Fraida and Elite Olshtin. 1986. Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Gage, N.L. and David C. Berliner. 1979. Educational Psychology. 2nd. ed. Chicago: Rond Mcnally.

Gagne, Robert M. 1969. The Condition of Learning. New york: Hort, Rinchart and Winston.

Gronlund, Norman E. 1985. Measurment and Evaluation in Teaching. 5th.ed. New york: Mac Millan Publishing Company:

Haliday, M.A.K. and others. 1964. The Linguistic Science and Language Teaching. London: Longman.

Hirst, Paul. 1974. Knowledge and the Curriculum. London: Routledge and Kegan Roul, P.132. In Tanner and Tanner. 1980. Curriculum Development: Theory in to Practice. 2nd. ed. New york: Mac Millan.

Hutchinson, T. and Alan Waters. 1987. English for Specific Purposes: A Learning Centred Apparoach. London: Combridge University Press.

Lysought, J.P. and C.M.Williams.1963. AGuide to Programed Instruction. New york: Witey.

Mackey, W.F. 1962. Language Teaching Analysis. London: Langman.

Mager, Robert, F. 1962. Preparing Instructional Objectives. California: Fearon Publishers, Inc.

______________. 1984. Preparing Instructional Objectives. 2nd.ed. Belmont: Pitman Learning, Inc.

Marew Zewdie. 1992. " The Objectives and Content of the Ethiopian School English Syllabus; Its Adequacy, Relevance and Effectiveness" The Ethiopian Journal of Education. Vol 13/1, pp.1-40.

MicNiel, John D. 1985. Curriculum: A comprehensive Introduction. Losangeles: University of California, Little Brown and Company.

Ministry of Education. 1944. Secondary School Curriculum. Imperial Ethiopian Government, Ministry of Education and Fine Arts.

______________. 1959. Secondary School Curriculum Development and ESLCE Seminar Final Report. Ministry of Education and HSIU Facalty of Education.

Nunan, David. 1988. Syllabus Design. Oxford: Oxford University Press.

Oliva, Peter F. 1988. Developing the Curriculum. 2nd.ed. London: Scott, Foresman and Company.

Payne, A. Davide. 1974. Curriculum Evaluation: Comentaries on Purpose, Process, Product. London: D-C. Heath and Company.

Posner, George J. 1992. Analyzing the Curriculum. New york: Mc Grow - Hill, Inc.

Prabhu, N.S. 1987. Second Language Pedagogy. Oxford: Oxford University Press.

Richterich, R, 1972. A Model for the Definition of Language Needs of Adult Learning a Modern Language. Strashourag: Council of Europe.

Sylor, Alexander. 1981. [et.al.] Curriculum Planning for Better Teaching and Learing. 4th. ed. New york: HOlt, Rinchart and Winston.

Smith, B. Othanel and Others. 1950. Fundamentals of Curriculum Development. New york: Harcourt, Brace and world, Inc.

Stern, H.H. 1983. Fundamental Concept of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

_______________. 1984. " Review and Discussion" General English Syllabus Design. ELT Document 118. Oxford. Pergamon Press.pp. 5-12

Stratemeyor, Florence B. and Others. 1957. Developing a Curriculum for Modern Living. New york: Bureau of Publication.

Taba, Hilda. 1962. Curriculum Development : Theory and Practice. New york: Harcourt Brace Jovanovich, Inc.

Tanner, Daniel and Laurel N. Tanner. 1980. Curriculum Development. Theory into Practice. 2nd. ed. New york : Mac Millan Pulishing Co. Inc.

Tanner, Laurel N. 1983. " Curriculum History and Educational Leader Ship" Educational Leader ship. Vol. 40/8,pp. 38-43.

Tyler, Ralph.W 1949. Basic Principle of Curriculum and Instruction. Chicago: Chicago University Press.

_____________. 1950. Basic Principle of Curriculum and Instruction. Chicago : Chicago University Press.

_____________. 1976. " Two New Emphasis in Curriculum Development " Educational Leader Ship. Vol. 24/1, 61-77

Valette, Rebecca M. and Rence S. Disick. 1972. Modern Language Performance Objectives and Individualization. New york: Harcourt Brace Jovanovich, Inc.

White, Ronald V. 1988. The ELT Curriculum. Cambridge: Basil Black Wall, Inc.

Widdowson, H.G. 1984. " Educational and Pedagogical Factors in Syllabus Design" General English Syllabus Design. ELT Document 118. Oxford: Pergamon Press. pp. 23-27.

Wilkins, D.A. 1981. " National Syllabus Revisted" Applied Linguistics II, 1, pp. 83-89.

Yalden, Janice. 1983. The Communication Syllabus: Evaluation, Design, and Implementation. Oxford: Pergamon Press.

_____________ 1984. " Syllabus Design in General Education: Opitions for ELT" General English Syllabus Design: ELT Document 118: Oxford: Pergamon Press, pp. 13-21.

« አባሪ ሀ »

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
# የድህረ ምረቃ ት/ቤት
# በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን
# የሚመለስ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ አሁን በሥራ ላይ ያለው የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት የዓላማ አነዳደፍና የይዘት አደረጃጀት ብቃት እንዳለው ለማጥናት የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው::

የጥናቱ ውጤት ለአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዝግጅት የዓላማ አነዳደፍና የይዘት አደረጃጀት ብቃትን ለመጠበቅ በሚደረጉ ጥረቶች አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይገመታል:: በዚህም ጥናቱ የታለመለትን ውጤት ያስገኝ ዘንድ ተገቢና ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትእግስትና በጥሞና በማንበብ ትክክል ናቸው የሚሉዋቸውን መልሶች እንዲመልሱልኝ እየጠየቅሁ፣ ለሚያደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

ማሳሰቢያ:- በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም::

## ክፍል አንድ

1. ጾታ:- ________________
2. የትምህርት ደረጃ:- __________________________
3. አማርኛን ለማስተማር ሰልጥነዋል? ______
4. በተራ ቁጥር ሶስት ለተጠየቀውን ጥያቄ የሰጡት መልስ «አዎ» የሚል ከሆነ የሰለጠኑበት መስክ፣

| አብይ | | ንዑስ | |
|---|---|---|---|
| 4.1 | አማርኛ | ሀ. | እንግሊዝኛ |
| 4.2 | እንግሊዝኛ | ለ. | አማርኛ |
| 4.3 | ፔዳጎጂ | | |
| 4.4 | ሌላ ካለ ይግለጹ ____________________________________________ | | |

5. ሥልጠናውን ያጠናቀቁበት ዘመን ________
6. ለስንት ዓመት አስተምረዋል? ________
7. በ10ኛ ክፍል አማርኛን ለምን ያህል ዓመት አስተምረዋል? ______
8. ሙያዎን ለማሻሻል የተሳተፉበት ወርክሾፕ ካለ ይዘርዝሯቸው

| የወርክሾፑ ስም | የተሳተፉበት ዘመን |
|---|---|
| ሀ. _______________ | _________________ |
| ለ. ______________ | _________________ |
| ሐ. ______________ | _________________ |

## ክፍል ሁለት

### በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎችን አነዳደፍ የሚመለከቱ ጥያቄዎች፣

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምርጫ ያላቸውን መልሳቸውን በመክበብ፣ የሌላቸውን ደግሞ በጽሑፍ ይመልሱ።

1. መርሀ-ትምዓርቱን ለማስተማር ይገለገሉበታል?

   ሀ. እገለገልበታለሁ ለ. አልገለገልበትም

2. ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃቸው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

   ሀ. ናቸው ለ. አይደሉም

3. ለጥያቄ ሁለት የሰጡት መልስ «አይደሉም» የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?

   ሀ. ዓላማዎቹ በውስጣቸው የያዟቸው የባሕሪ ለውጥ ዓይነቶች የክፍል ደረጃውን የሚመጥኑ ስለመሆናቸው

   ለ. ዓላማዎቹ እንዲያመለክቱ የተፈለገው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት በግልጽ የተቀመጠ ስለመሆኑ

   ሐ. ዓላማዎቹ ለተግባራዊነታቸው የሚጠይቋቸው ይዘቶች በክፍል ደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች ሊረዷቸው የሚችሉ ስለመሆናቸው

   መ. ዓላማዎቹ ለተግባራዊነታቸው የሚጠይቋቸው ይዘቶች በመርሀ-ትምህርት ውስጥ የተካተቱላቸው ባለመሆኑ

   ሠ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ____________________________________

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

4. ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

   ሀ. ይችላሉ ለ. አይችሉም

5. ዓላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል፣

ሀ. ይችላሉ ለ. አይችሉም

6. ለጥያቄ አምስት የሰጡት መልስ «አይችሉም» የሚል ከሆነ፣ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?

ሀ. ዓላማዎቹ የክፍል ደረጃውን የማይመጥኑ በመሆናቸው
ለ. ዓላማዎቹ ከተማሪዎቹ ምን እንደሚጠበቅ ለይቶ በማመልከት ተማሪዎቹ ለዓላማዎቹ ተግባራዊነት የድርሻቸውን እንዲወጡ ስለማያስችሏቸው
ሐ. ለተግባራዊነታቸው የሚጠይቁት ጊዜ ረጅም በመሆኑ
መ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ ______________________________
______________________________________________
______________________________________________

7. ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ነው የተጻፉት?

ሀ. አዎ ለ. አይደለም

8. ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው ይመስልዎታል?

ሀ. አላቸው ለ. የላቸውም

9. ዓላማዎቹ የሚያሳዩት ምንድነው?

ሀ. ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ
ለ. ተማሪው እንዲማረው የሚፈለገውን የይዘት ዝርዝር
ሐ. ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነትና ባሕሪው የሚገለጥበትን ሁኔታ
መ. መምህሩ ማድረግ ያለበትን ተግባር
ሠ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ ______________________________
______________________________________________
______________________________________________

10. ዓላማዎቹ ተማሪዎች እንዲያሳዩት የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ ነው የተጻፉት?

ሀ. አዎ ለ. አይደለም

11. ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ ይመስልዎታል?

ሀ. ይሰጣሉ ለ. አይሰጡም

12. ለጥያቄ አሥራ አንድ የሰጡት መልስ «አይሰጡም» የሚል ከሆነ ለየትኛው የቋንቋ ክሂል ወይም የእውቀት ዘርፍ የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ ይጥቀሱ::
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

## ክፍል ሦስት

## በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችን አደረጃጀት የሚመለከቱ ጥያቄዎች፣

1. በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

    ሀ. ይመጥናሉ ለ. አይመጥኑም ሐ. በከፊል ይመጥናሉ

2. በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይመስልዎታል?

    ሀ. አላቸው ለ. የላቸውም ሐ. በከፊል አላቸው

3. በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ይመስልዎታል?

    ሀ. ከፍተኛ ለ. መካከለኛ ሐ. ዝቅተኛ

4. ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ የሚያስችሉ ይመስልዎታል?

    ሀ. ያስችላሉ ለ. አያስችሉም ሐ. በከፊል ያስችላሉ

5. ለጥያቄ አራት የሰጡት መልስ «አያስችሉም» ወይም «በከፊል ያስችላሉ» የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?

    ሀ. ዓላማዎቹና ይዘቶቹ ዝምድና የሌላቸው በመሆኑ
    ለ. ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን የማይመጥኑ መሆናቸው
    ሐ. ይዘቶቹ ዓላማዎችን ከዳር ለማድረስ የሚያስችል ያደረጃጀት ብቃት ስለሚጐላቸው
    መ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ ____________________
    ____________________
    ____________________

6. የይዘቶቹ አደረጃጀት ምን ይመስላል?

    ሀ. ከቀላል ወደ ከባድ የሚንዝ ነው

ለ. የደረጃ ልዩነት ሳያሳይ የሚጓዝ ነው

ሐ. ቀዳሚው ለተከታዩ መሠረት እንዲሆን በሚያስችል መንገድ የተዋቀረ ነው

መ. ከ«ሀ» ና «ሐ» ትክክል ናቸው

ሠ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ ______________________________

______________________________

______________________________

7. የይዘቶቹ አደረጃጀት ተከታታይነት የተጠበቀ ይመስልዎታል?

ሀ. ተጠብቋል ለ. አልተጠበቀም ሐ. በከፊል ተጠብቋል

8. ለጥያቄ ሰባት የሰጡት መልስ «ተጠብቋል» ወይም «በከፊል ተጠብቋል» የሚል ከሆነ የይዘቶቹ ተከታታይነት መጠበቁን የሚያመለክቱ ጥቂት ምሳሌዎችን ይጻፉ

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

9. የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት የተጠበቀ ይመስልዎታል?

ሀ. ተጠብቋል ለ. አልተጠበቀም ሐ. በከፊል ተጠብቋል

10. የይዘቶቹን ቅደም ተከተል ለዋውጠው ቢያስተምሩ በትምህርቱ ሂደት ውጤታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ ያለ ይመስልዎታል?

ሀ. አለ ለ. የለም

11. ለጥያቄ አሥር የሰጡት መልስ «የለም» የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል?

ሀ. ተማሪው የትኛውንም ይዘት አስቀድሞ ቢማር ለውጥ ስለሌለው ነው

ለ. ይዘቶቹ ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ነው

ሐ. ይዘቶቹ አንዱ ለሌላው መሠረት በመሆን ያልተደራጁ በመሆኑ ነው

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ሠ. ሌላ መልስ ካለም ይጥቀሱ ______________________________

______________________________

______________________________

12. ይዘቶችን የሚያስተምሯቸው እንዴት ነው?

ሀ. አደረጃጀታቸው ሳይለወጥ ነው
ለ. የራሴን ቅደም ተከተል በመስጠት ነው
ሐ. የራሴን ይዘት በማዘጋጀት ነው
መ. አንዳንዱ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ያላቸውን ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ አንዳንዱ ደግሞ የራሴን ቅደም ተከተል በመስጠት ነው፡፡
ሠ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ ______________________________
______________________________
______________________________

13. ለጥያቄ አሥራ ሁለት የሰጡት መልስ «ለ» ወይም «መ» ከሆነ ምክንያትዎ ምንድነው?

ሀ. ለማስተማር እንዲቀለኝ በማሰብ
ለ. ከቀላል ወደ ከባድ እንዲሄድ ለማድረግ
ሐ. ጠቃሚ ጠቃሚዎችን ለመምረጥ
መ. ሌላ መልስ ካለዎ ይጥቀሱ ______________________________
______________________________
______________________________

14. ይዘቶቹ በክፍል ደረጃ ከሚሰጡ ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር የሚደጋገፉ ይመስልዎታል?

ሀ. ይደጋገፋሉ ለ. አይደጋገፉም

15. ለጥያቄ አሥራ አራት የሰጡት መልስ «ይደጋገፋሉ» የሚል ከሆነ ከየትኛው የትምህርት ዓይነት ጋር እንደሚደጋገፉ ለይተው ያመልክቱ

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

« አባሪ ስ »

## በሥርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት
## ለአማርኛ ትምህርት ክፍል ባለያች የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

1. ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

2. ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

3. ዓላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

4. ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ነው የተጻፉት?

5. ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው ይመስልዎታል?

6. ዓላማዎቹ ምንን የሚያሳዩ ይመስልዎታል?

7. ዓላማዎቹ ተማሪዎች እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ የተጻፉ ይመስልዎታል?

8. ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተማጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ ይመስልዎታል?

9. በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልታል?

10. በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይመስልዎታል?

11. ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው ብለው ያስባሉ?

12. ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ ብቃት ያላቸው ይመስልዎታል?

13. ይዘቶቹ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የተደራጁ ይመስልዎታል?
14. ይዘቶች ተከታታይነታቸው ተጠብቆ የተደራጁ ይመስልዎታል?

15. የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ብለው ያምናሉ?

16. በ10ኛ ክፍል የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክፍል ደረጃው ከሚሰጡት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የሚደጋገፉ ይመስልዎታል?

« አባሪ ሐ »

# ቃለ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ በመሆን ከተመረጡት ውስጥ በሥርአተ ትምህርት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ይገኙበታል፡፡ የትምህርት ክፍል ባለሞያዎች መረጃ እንዲሰጡ የተደረገው በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ በቃለ መጠይቅ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስትና አራት ሥር ጥያቄዎች «ጥ»፣ ለጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች ደግሞ «መ» በማለት ቀርበዋል፡፡

## ቃለ መጠይቅ - 1

1. ጥ - ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሲሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርገው መነደፋቸው ግልጽ ነው፡፡ ይሄ የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም፡፡ ባይሆን የክፍል ደረጃውን ይመጥናሉ ይ? ብለህ ብትጠይቀኝ የተሻለ ይመስለኛል፡፡ በዚህም በኩል ቢሆን የተማሪዎቹን የእድሜና የክፍል ደረጃ እንዲመጥኑ ተደርገው የተዘጋጁ በመሆኑ ችግር አይታይባቸውም፡፡

2. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆነ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹ ተማሪዎች ካሉበት አካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ሙሉ ለሙሉ ይስማማሉ ማለት ያስቸግራል፡፡ በተቻለ መጠን ይህን ሁኔታ እንዲያሟሉ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ ዋናው ነገር መርሀ - ትምህርቱን ስናዘጋጅ በመስክ ጉብኝት በመላ ሀገሪቱ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መረጃ ለማሰባሰብ እንደሞከርን ልገልጽልህ እወዳለሁ፡፡ ዋናው የመረጃ ምንጫችንም ይሄው ነበር፡፡ በዚህ መረጃ ላይ ተመሥርተን ነው የቀረጽናቸው፡፡

3. ጥ - ዓላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ጥያቄህ ከእኛ ይልቅ ለመምህራን የቀረበ ነው፡፡ ይሁንና እንደትምህርት ባለሞያነታችን የማስተማሪያ መሣሪዎችን ለማሻሻል መረጃ የምንሰበስበው እንድም ከመምህራን በመሆኑ በዚህ ረገድ ያገኘነው መረጃ የለም፡፡

ይህም ሲባል ግን እኛም በበኩላችን መጽሐፍቱን በመገምገም የምንለው ነገር አይኖርም ማለት አይደለም:: ባይበዛም ዓላማዎቹ ችግር እንዳለባቸው በራሳችን የምናየው ነገር አለ:: ይህም በቅርቡ በምናደርገው የማሻሻል ሥራ ይስተካከላል ብዬ አስባለሁ::

4. ጥ - ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ነው የተጻፉት?

በሀ - ቅድም እንደገለጽኩልህ በቅርቡ በምናደርገው የማሻሻል ሂደት እናሻሽለዋለን ብለን ካሰብነው ውስጥ አንዱ አሁን የጠየከኝ ጥያቄ ነው:: ዓላማዎቹ መያዝ የሚገባቸውን ሁሉ አልያዙም:: እኔ በታይለር ሞዴል አምናለሁ:: በዚሁ መሠረት ልናስተካክላቸው እንችላለን ብዬ አስባለሁ:: የተማሪውን ባሕሪ ከማመልከት አልፈው እንዲሄዱ ለማድረግ መሞከራችን አይቀርም::

5. ጥ - ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው ይመስልዎታል?

በሀ - ዓላማዎቹ ጥሩ አቀራረብ ነው ያላቸው:: ከቃላት ወደ ዐ.ነገር፣ ከዐ.ነገር ወደ አንቀጽ፣ ከአንቀጽ ወደ ድርሰት እያለ የሚሄድ የባሕሪ ለውጥ ዓይነትን የሚጠይቁ ናቸው:: በዚህ ረገድ ችግር ያለባቸው አይመስለኝም::

6. ጥ - ዓላማዎቹ ምንን የሚያሳዩ ይመስልታል?

በሀ - ይህ ጥያቄ ቀደም ሲል ከጠየከኝ ጋር የሚመሳሰል ይመስለኛል:: እንደነገርኩህ ዓላማዎቹ ተማሪው ምን ዓይነት የባሕሪ ለውጥን ማሳየት አለበት የሚለውን የሚመልሱ ናቸው::

7. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎቹ እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ የተጻፉ ይመስልዎታል?

በሀ - በጥያቄህ ውስጥ የተገለጸው ችግር ይታያል:: እርግጥ ነው ዓላማዎቹ ግልጽነት ይጎላቸዋል:: አጠቃላይ መልክ ነው የሚታይባቸው:: የቀረቡበትም ቋንቋ አጠቃላይነት ነው የሚነበብበት:: ይህ ደግሞ መስተካከል የሚገባው ጉዳይ ነው::

8. ጥ - ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ ይመስልዎታል?

መ - የተመጣጣኝነት ጥያቄ ዋናው የሥርአተ - ትምህርት ቀጥሎም የመርሀ - ትምህርት ጥያቄ ነው፡፡ መመጣጠን ከሌለ ሥራው እንደሚዛባ የታመነ ነው፡፡ በመሆኑም ዓላማዎቹ ለቋንቋው ትምህርት የተመጣጠነ ትኩረት እንዲሰጡ ተደርገው ተነድፈዋል፡፡

9. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

መ - በመጽሐፍ ዝግጅት ውስጥ መሠረታዊ የሆነውን ጥያቄ ነው የጠየከኝ፡፡ በዚህ ረገድ ሙሉ ለሙሉም ባይባል አብዛኛዎቹ የክፍል ደረጃውን እንደሚመጥኑ ለመናገር ይቻላል፡፡ የቀሩትም ቢሆን የክፍል ደረጃውን ይመጥናሉ ተብለው ነው የተመረጡት፡፡ ይሁንና ግን በሂደት ሲታዩ ሊሻሻሉ የሚገባ መሆኑ ተስተውሏል፡፡

10. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - ቋንቋውን ከማስተማር ውጭ ሌላ ነገር የሚያስተምር ይዘት በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛል ብዬ አልገምትም፡፡ ሁሉም በክፍል ደረጃው የሚሰጠውን የቋንቋ ትምህርት ለመስጠት እንደሚችሉ ታውቆ ነው የተመረጡት፡፡ ጠለቅ ብለን ካየነው አንድን ነገር ስንመርጥ ለመረጥንበት ጉዳይ ይጠቅመናል፣ ያስፈልገናል ብለን በመወሰን ነው፡፡ ስለዚህም ምርጫና ተገቢነት አብረው ነው የሚሄዱት፡፡ ይህን ስልህ ግን ይዘቶቹ ሁሉ አንድም ነቀፋ የለባቸውም ማለቴ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብህ፡፡ በማስተማሩ ሂደት እየተፈተሹ የሚሻሻሉ ይኖራሉ፡፡

11. ጥ - ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው ብለው ያስባሉ?

መ - የይዘቶቹ የቅድምያ ትኩረት በክፍል ደረጃው የሚሰጠውን የቋንቋ ትምህርት ማስተማር ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ይዘቶቹ የሚመረጡበት ምክንያት የለም፡፡ ባጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ ነው፡፡

12. ጥ - ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ዘከዳር ለማድረስ ብቃት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - በመሠረቱ ይዘቶች ሲመረጡ እንዲሁ መቼም አይመረጡም:: ማለቴ መመዘኛዎችን ተጠቅመን ነው የምንመርጣቸው:: ዓላማም አንድ መመዘኛ ነው:: ስለዚህም ከአላማ ጋር የሚቃረን ይዘት ካለ መጽሐፉ እራሱን በራሱ ይቃረናል ማለት ነው:: በ10ኛ ክፍል መርሀ - ትምህርት ውስጥ ያሉት ይዘቶች ግን ሁሉም ባይባልም ባመዛኙ ዓላማውን ከዳር ለማድረስ ይችላሉ ብዬ ለመናገር እችላለሁ::

13. ጥ - ይዘቶቹ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የተደራጁ ይመስልዎታል?

መ - በቅርቡ የሁለተኛ ደረጃ ማለትም ከ9 - 12ኛ ክፍል የሚያገለግሉ የመምህራን መምሪያ ያዘጋጀን በመሆኑ የይዘቶቹን የአደረጃጀት ብቃት ከሥር መሠረቱ ለማየት ችለናል ብዬ እገምታለሁ:: የመምህሩን መምሪያ ስንሰራ ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄዱ መሆኑን አስተውያለሁ:: ከቀላል ወደ ከድ ሲባል ከቃላት ይጀምርና ወደ ዐ.ነገር፣ ከዛም ወደ አንቀጽ፣ ከአንቀጽ ደግሞ ወደ ድርሰት ደረጃ ያድጋል ማለት ነው:: ይሄን ያመጣሁት ምሣሌ እንዲሆንህ ነው::

14. ጥ - ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ተጠብቆ የተደራጁ ይመስልዎታል?

መ - ጥያቄህ የተደጋገመ ይመስለኛል:: ይሁንና ግን ሙሉ ለሙሉ ነው ባልልህም የይዘቶቹ ተከታታይነት መጠበቁን አምናለሁ:: ይህን ስልህ በመማማሩ ሂደት እየታየ ሲታረም የሚችል ችግር የለም ማለቴ አይደለም::

15. ጥ - የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ብለው ያምናሉ?

መ - በመሠረቱ የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ማለት ይቻላል:: ለዚህም ከመጽሐፉ ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ የሚቻል ይመስለኛል:: ይህ በመጽሐፍ ዝግጅት ወቅት ወሳኝ ጉዳይ ነው::

16. ጥ - በ10ኛ ክፍል የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክፍል ደረጃው ከሚሰጡት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የሚደጋገፍ ይመስልዎታል?

መ - ውህደት የሚለው ጽንሰ - ሃሣብ ግልጽ መሆን አለበት:: ውሕደት ትምህርቱ በሚሰጥበት የክፍል ደረጃ በሚገኙ ትምህርቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው:: በዚህ ረገድ ይዘቶቹ በዛው የክፍል ደረጃ ከሚገኙት የትምህርት ይዘቶች ጋር እንዲገናኙ፣ እንዲዋሀዱ ተደርገው ተደራጅተዋል:: ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የተማሩትን በእንግሊዝኛ ውስጥ ያገኙታል::

## ቃለ መጠይቅ - 2

1. ጥ - ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - የዓላማዎቹን ተግባራዊነት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ነው ማየት ያለብን:: በዚህ ረገድ ዓላማዎቹ ችግር ያለባቸው ይመስለኛል:: ግልጽነት የጎደለውን ነገር ደግሞ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቸግር ትረዳኛለህ ብዬ እገምታለሁ::

2. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - መርሀ - ትምህርቱ ከመሠራቱ በፊት በተለያዩ ጊዜያት የመስክ ጉብኝት በማድረግ ለአዲሱ መርሀ - ትምህርት ዝግጅት የሚጠቅሙ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንደተሞከረ አስታውሳለሁ:: በ1982 ዓ.ም. የተካሄደው ሲምፖዚየም ለዚህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል:: በዚህ ሲምፖዚየም የተለያዩ ጥናቶች ቀርበዋል:: ብዙ መረጃዎችንም አግኝተናል:: በመሠረቱ ዓላማዎቹ ከተማሪዎቹ አካባቢ ጋር ካልተጣጣሙ ቋንቋውን ማስተማሩ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? በተቻለ መጠን ዓላማዎቹ በተማሪዎቹ አካባቢ ተግባራዊ ጠቀሜታ ያላቸው እንዲሆን ተደርጓል::

3. ጥ - ዓላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ይህ ጥያቄ ከምጣኔ ጋር የተያዘ ይመስለኛል:: ማለቴ ትምህርቱ ለዓመቱ ተመጥኖ ነው ወይ የተዘጋጀው? የሚል ይመስላል የጥያቄው መንፈስ:: ለዚህ ጥያቄ ደግሞ የተሻለ መልስ የሚገኘው ከመምህራን ነው:: እኛም ደግሞ ስለማስተማሪያ መሣሪያዎችመረጃ የምናገኘው አንድም ከነሱ በመሆኑ እስከ ዛሬ መጽሐፍቱን ለማሻሻል ባሰበሰብናቸው መረጃዎች ስለዚህ ጉዳይ የሚያነሣ አላጋጠመኝም::

4. ጥ - ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ነው የተጻፉት?

መ - ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመሻት አሁን መርሀ - ትምህርቱን ገልብጠን ብናይ ምላሽ እናገኛለን:: ከመምህራንም ያሰባሰብነው መረጃ የችግሩን መኖር አሳይቷል:: ችግሩን ስልህ ዓላማዎቹ ተግባራዊ ሆነው የሚታዩበትን መንገድ ይዘው አለመነደፋቸውን ማለቴ ነው:: ጉዳዩ በዓላማ አመሠራረት ላይ ጥንቃቄን የሚሻ ነው:: በቅርቡም የመስኩ ባለሞያዎችን በመቅጠር መጽሐፍቱን ለማሻሻል አስበናል:: አንድ ሥርአተ-ትምህርት አምስት ዓመት ብቻ ነው ማገልገል ያለበት:: ስለዚህ ልናሻሽለው አስበናል:: ችግሩንም ለማስወገድ እንሞክራለን::

5. ጥ - ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው ይመስልዎታል?

ሀ - በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ዓላማዎች አደረጃጀት ተቀባይነት አለው:: ተማሪዎቹ ደረጃቸውን እንደጠበቁ የሚያሳድጋቸው ነው::

6. ጥ - ዓላማዎቹ ምንን የሚያሳዩ ይመስልታል?

ሀ - ቀደም ሲል ስጠየከኝ ጥያቄ በሰጠሁህ መልስ ላመለክትህ እንደሞከርኩት ዓላማዎቹ መግለጫ መንገዳቸውን አልያዙም:: በዚህም መሠረት ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ብቻ መያዛቸው በግልጽ ይታያል:: ይህ ግን በቂ ነው ማለት አይደለም:: ዓላማዎቹ የሚጎላቸው ነገር አለ:: ይህም በቀጣይ ሂደት መሻሻሉ አይቀርም::

7. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎቹ እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ የተጻፉ ይመስልዎታል?

ሀ - በዚህ ረገድ ዓላማዎቹ ችግር አለባቸው:: የዚህም ችግር ዋናው መንስኤ ዓላማዎቹ የተቀረጹበት ቃላት ናቸው:: ብዙዎቹ ዓላማዎች ባንድ ገ ዜ ብዙ መልእክት በሚያስተላልፉ ቃላት ተነድፈዋል:: ይህ መሆን አልነበረበትም:: ውሱን የባሕሪ ለውጥ አያመለክቱም:: ይህ ደግሞ አንባቢውን ያሳስታል:: እኔና አንተ በአንድ መንገድ አንረዳቸውም:: ይህ መሻሻል ያለበት ጉዳይ መሆኑን አምናለሁ::

8. ጥ - ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ ይመስልዎታል?

ሀ - የዓላማዎቹ ትኩረት የተዛባ ነው:: አንዱን የትምህርት ክፍል ከሌላው አስበልጦ የማየት ባሕሪ ይታይባቸዋል::

9. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

ሀ - ጥያቄው የማዛዘንን ጉዳይ የሚመለከት ከሆነ ጥሩ ነው:: ይሄውም ይዘቶቹ ምን ያህል የክፍል ደረጃውን የጠበቁ ናቸው የሚል ከሆነ ጥያቄህ፣ በመካከለኛ ሁኔታ ነው ብዬ መልስ እሰጣለሁ:: ምክንያቱም ሙሉ ለሙሉ ለማለት ባያስደፍርም ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ይዘቶች የክፍሉን ደረጃ ይመጥናሉ:: ይህ ጥያቄ በመጽሐፍ ዝግጅ ወቅት በቅድሚያ መልስን የሚሻ ጥያቄ ነው:: ይሄን ጥያቄ ባግባቡ ያልመለሰ የመጽሐፍ ዝግጅት ዋጋ የለውም::

10. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይመስልዎታል?

ሀ - የይዘቶቹን ተገቢነት በተመለከተ የ10ኛ ክፍል ብቻ ሳይሆን የሌሎቹም ክፍሎች መርሀ - ትምህርቶች ችግር አለባቸው::

11. ጥ - ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው ብለው ያምናሉ?

ሀሀ - እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን አንድ ነጥብ ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ባመዛኙ ቋንቋውን ለማስተማር ካላቸው ተገቢነት ጋር ተለይቶ የሚታይ አለመሆኑን ነው:: ስለዚህ እንደተገቢነታቸው ሁሉ ለቋንቋውም ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት አመርቂ አይደለም::

12. ጥ - ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ ብቃት ያላቸው ይመስልዎታል?

ሀሀ - ቀደም ሲል ይዘቶቹ ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት አመርቂ አለመሆኑን ነግሬአለሁ:: በሌላም በኩል ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ እንደሆነ የገለጽኩልህ ይመስለኛል:: በዚህም ሁኔታ ይዘቶቹ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከዳር ለማድረስ ይችላሉ ማለት ይቸግራል::

13. ጥ - ይዘቶቹ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የተደራጁ ይመስልዎታል?

ሀሀ - ሙሉ በሙሉ ባይሆንም መጠነኛ ያደረጃጀት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል:: ይችላል ስልህ ችግር አለ ማለቴ ነው::

14. ጥ - ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ተጠብቆ የተደራጁ ይመስልዎታል?

ሀሀ - በዚህ ረገድ ይዘቶቹ ችግር የለባቸውም ማለት ይቸግራል:: ይሁንና ግን መችግሩ በጣም የጎላ አይደለም:: ይህ ችግር የሚታይባቸው ይዘቶች ጥቂት እንደሆኑ መግለጽ እችላለሁ:: ባመዛኙ ግን የይዘቶቹ ተከታታይነት ተጠብቆ ተደራጅተዋል::

15. ጥ - የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ብለው ያምናሉ?

ሀሀ - ይህ ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ይመስለኛል:: በመጽሐፍ ዝግጅት የቅድሚያ ትኩረትን የሚሻ ጥያቄ ነው:: በዚሁ መሠረት ይዘቶቹን ከገመገምናቸው ተለጣጣቂነታቸው ተጠብቆ ነው የተደራጁት ለማለት ይቸግራል::

16. ጥ - በ10ኛ ክፍል የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክፍል ደረጃው ከሚሰጡት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የሚደጋገፍ ይመስልዎታል?

ሀሀ - የይዘቶቹን ጎናዊ ወይም አምዳዊ ቅንብር በተመለከተ ችግር ያለ ይመስለኛል:: ይህን በተመለከተ ባለፈው ዘመን የተሠሩትን መጽሐፍት እንዳስታውስ ያደርገኛል:: ይሄውም የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍቱ ሁሉ እግረ መንገዳቸውን ለተማሪች የሚጠቅም ተጓዳኝ እውቀት እየሰጡ መሄድ አለባቸው በሚል ተነሳሽነት እጅግ ተበላሽተው ነበር ማለት ይቻላል:: አሁን ደግሞ በፊት የተሠራውን ስህተት ለማረም በተደረገው ሙከራ የቋንቋው ትምህርት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ሊኖረው የሚገባው ትስስር ከጥያቄ ውስጥ የገባ ይመስለኛል::

## ቃለ መጠይቅ - 3

1. ጥ - ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሲሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ይሄማ ካልሆነ የምንሠራውን አናውቅም ማለት ነው:: ተማሪዎች ዓላማዎቹን ተግባራዊ ሲያደርጓቸው ካልቻሉ ለማነው የተጻፉትእንላለን? በእኔ በኩል ዓላማዎቹ የክፍል ደረጃውን እንዲመጥኑ ተደርጎ መነደፋቸው እውነት ነው::

2. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹን በመስክ ጉብኝትና በ1982 ዓ.ም. ከተካሄደው ሲምፖዚየም ካሰባሰብነው መረጃ በመነሳት ለመንደፍ ሞክረናል:: ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት በሚኖሩበት አካባቢ ሲጠቅማቸው ይገባል:: ይህን መርህ ተከትለን ልንነድፋቸው ሞክረናል::

3. ጥ - ዓላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሲሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹ ተግባራዊ የሚሆኑት በተመረጡላቸው ይዘቶች መሆኑ ይታወቃል:: እነዚህ ይዘቶች ስላሉ ብቻ ደግሞ ዓላማዎቹ ተግባራዊ ሲሆኑ ይችላሉ ማለት አይደለም:: ይዘቶቹን በዓመቱ ውስጥ አስተምሮ ለመጨረስ ካልተቻለ ዓላማዎቹ ተግባራዊ ሲሆኑ አልቻሉም ማለት ነው:: ይሁንና ግን ይዘቶቹ ለዓመቱ ትምህርት ተመጥነው የተዘጋጁ ቢሆኑ በዓመቱ ውስጥ ይጠናቀቃሉ:: ዓላማዎቹም በዓመቱ ውስጥ ተግባራዊ ይሆናሉ ማለት ነው:: በግሌ እስካሁን ባደረኩት የመስክ ጉብኝት ይሄ ችግር ተከስቶብኛል የሚል መምህር አላጋጠመኝም::

4. ጥ - ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ነው የተጻፉት?

መ - ዓላማዎቹ መያዝ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱን ክፍል ብቻ መያዛቸውን ተገንዝበናል:: ይህ ደግሞ በሂደት ሲታረም የሚችል ጉዳይ ነው::

5. ጥያቄ - ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - የምትጠይቀኝ ነገር የይዘት ጉዳይ ይመስለኛል:: ይሁንና ግን ዓላማዎቹም ቢሆኑ ይህንኑ ሥርአት ጠብቀው እንደተደራጁ ይገባኛል::

6. ጥ - ዓላማዎቹ ምንን የሚያሳዩ ይመስልታል?

መ - ዓላማዎቹ ከምትህርት በኋላ ተማሪዎች የሚያሳዩትን የባሕሪ ለውጥ ብቻ እንዲገልፁ ተደርገው ነው የተጻፉት:: ይሄ ግን በቂ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ወደፊት በምናደርገውም የማሻሻል ሥራ መልስ ያገኛል ብዬ አስባለሁ::

7. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎቹ እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ የተጻፉ ይመስልዎታል?

መ - እዚህ ላይ ግልጽ ነገር ይታያል:: ይሄውም ጥያቄህ ዓላማዎቹን ስትነድፉ የተጠቀማችሁበት ቋንቋ ምን ይመስላል? የሚል እንደሆነ የተረዳሁህ ይመስለኛል:: በግልጽ እንደሚታየው ዓላማዎቹ የቀረቡበት ቋንቋ አጠቃላይነት አለው:: ይህም ደግሞ ችግር መኖሩን ያመለክታል:: በቅርቡም የምናደርገው እርማት ለዚህ ተግባራዊ ምላሽ እንደሚሰጥ አምናለሁ::

8. ጥ - ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘከርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ ይመስልዎታል?

መ - አንድ የቋንቋ ትምህርት ለቋንቋው ክሂሎችና እውቀቶች የተለያየ ትኩረት አይሰጥም:: ሁሉንም በእኩል ዓይን ማየት ይኖርበታል:: በዚህ መርህ መሠረት ዓላማዎቹ ተዘጋጅተዋል::

9. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

መ - ይሄ ብዙ የሚያከራክር ጥያቄ አይደለም:: ምክንያቱም አንድ የማስተማሪያ መጽሐፍ ስናዘጋጅ የመጀመሪያው ጥያቄ በመጽሐፉ ወ ውስጥ የምናካትታቸው ለትምህርት የሚቀርቡ መሠረታዊ ነገሮች ሁሉ የተማሪውን የክፍል ደረጃ ይመጥናሉ ወይ? የሚለው ሲሆን ይህንን ለመመለስ ካልቻልን ግን የማስተማሪ መጽሐፍ አዘጋጅተናል ለማለት ይቸገራል:: ይህንንም ስል ግን ይዘቶቹ ምንም እንከን አይወጣላቸውም ማለት አይደለም:: በሂደት ሲሻሻሉ የሚገባቸው ይዘቶች ያሉ ቢሆንም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ግን የክፍሉን ደረጃ ይመጥናሉ ብዬ ለመናገር እችላለሁ::

10. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - ይህ ጥያቄ በራሱ ሌላ ጥያቄ ይፈጥራል:: ይሄውም የመረጥናቸው ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ከሌላቸው ለምን እንመርጣቸዋለን?

ይዘቶችን የምንመርጠው ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢ ናቸው ብለን በመሆኑ ሁለቱ ተነጣጥለው የሚሄዱ አይደሉም፡፡ ጥያቄህን በትክክል ተረድቼው ከሆነ ተገቢነት ሳይኖረው የተመረጠ ይዘት በመጽሐፉ ውስጥ የምታገኝ አይመስለኝም፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንዶች ይህን በመጠኑም ቢሆን ሲያሟሉ ባይችሉም በየጊዜው በምናደርገው ግምገማ ይሻሻላሉ፡፡ በቅርቡም ባለሞያዎችን ቀጥረን የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ በዝግጅት ላይ ነን፡፡

11. ጥ - ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው ብለው ያስባሉ?

መ - ይሄ ጥያቄ ቀደም ሲል ከጠየከኝ ጥያቄ ጋር አብሮ ይሄዳል፡፡ ቀደም ሲል እንዳመለከትኩት ይዘቶቹ ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት ከፍተኛ በመሆኑ ለቋንቋውም ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ ነው፡፡

12. ጥ - ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ ብቃት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - አሁንም ይህ ጥያቄህ ከተገቢነት ጋር አብሮ የሚሄድ ይመስለኛል፡፡ ማለትም ይዘቶቹ ተገቢነት አላቸው ስንል ካላማው ጋር ያላቸውን ስምረት ማመልከታችን ነው፡፡ ካላማው ያፈነገጠ ይዘት ምኑን ተገቢ ሆነው እንላለን? አሁንም እንድታስተውለው የምሻው ነገር ቢኖር የምሰጥህ መልስ ይዘቶቹን ሁሉ ወደ ፍፅምና የሚወስዳቸው እንዳልሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ጠንካራ ይዘቶች አሉ ሰል ደካማ ይዘቶች በጥቂቱም ቢሆን ሲኖር እንደሚችሉ አትዘንጋ፡፡

13. ጥ - ይዘቶቹ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የተደራጁ ይመስልዎታል?

መ - ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ይመስለኛል፡፡ የማስተማሪያ መጽሐፍት ስናዘጋጅ ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ የሚያስኬደውን መንገድ ተከትለው መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ እኛም በቅርቡ ከ9 - 12ኛ ክፍል የመምህራን መምሪያ ያዘጋጀን በመሆኑ የይዘቶቹን አደረጃጀት በጥንቃቄ ለማየት ችለናል፡፡ በዚህም ወቅት በግሌ እንደተገነዘብኩት የይዘቶቹ አደረጃጀት ተገቢውን መልክ የያዘ ነው፡፡

14. ጥ - ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ተጠብቆ የተደራጁ ይመስልዎታል?

መ - ይህ ጥያቄ ቀደም ሲል ከጠየከኝ ጥያቄ ጋር የሚሄድ ይመስለኛል? ባልሳሳትም አንድ ሳይሆኑ አይቀሩም:: መቼም መቶ በመቶ እርግጠኛ ለመሆን ባይቻልም ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ተጠብቆ ስመደራጀታቸው ጥርጥር የለውም::

15. ጥ - የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ብለው ያምናሉ?

መ - ለዚህም ጥያቄ ያለኝ መልስ ለቀዳሚው ጥያቄ ከሰጠሁት መልስ የተለየ አይሆንም:: በመሠረቱ ይዘቶቹ ተለጣጣቂነታቸው ተጠብቆ መደራጀታቸውን ሳረጋግጥልህ እወዳለሁ:: አለበዚያማ ችግር ነው:: ይዘቶቹ ተለጣጣቂነታቸው ተጠብቆ ካልተደራጁ የትምህርቱ ሂደት እያደገ አይሄደም::

16. ጥ - በ10ኛ ክፍል የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክፍል ደረጃው ከሚሰጡት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የሚደጋገፍ ይመስልዎታል?

መ - በዚህ ረገድ ችግር አለ ብዬ አልገምትም:: ይህንን ለማረጋገጥ መጽሐፍቱን ማገላበጥ ይቀላል:: ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያገኙት እውቀት በሌላ ትምህርት ከሚያገኙት እውቀት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ተደርጓል::

## ቃለ መጠይቅ - 4

1. ጥ - ዓላማዎቹ በክፍል ደረጃው በሚገኙ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹ የክፍሉን ደረጃ በመመጠን ረገድ ችግር ያለባቸው አይመስለኝም:: ይሁንና ግን ባቀራረባቸው በኩል ችግር አያጡም:: ግልጽነት ነው ችግራቸው:: እንኳን ተማሪው መምህራንም ዓላማዎቹ ስለሚሉት ነገር የተለያየ ግንዛቤ ይኖራቸዋል የሚል እምነት ነው ያለኝ::

2. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎች ባሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - ይህ ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ይመስለኛል:: ተማሪዎች እንዲያሳዩ የፈለግነው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ከተማሪው ባሕል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ጋር የሚጋጭ ከሆነ ችግር እየፈጠርን ይመስለኛል:: በሌላም በኩል ተማሪው እንዲያሳየው የተፈለገው የባሕሪ ለውጥ ተማሪው ባለበት አካባቢ ተግባራዊ ጠቀሜታ ከሌላው ተማሪውን በከንቱ እያለፋነው መሆኑ ይታወቃል:: ስለዚህም እዚህ ችግር ውስጥ እንዳንገባ በተለያዩ ጊዜያት በሀገሪቱ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሰበሰብናቸው መረጃዎች ጠቅመውናል:: በመረጃ ላይ ተመሥርተን የነደፍናቸው በመሆኑ በዚህ በኩል ችግር አለባቸው የሚል እምነት የለኝም::

3. ጥ - ዓላማዎቹ በተሰጠው የትምህርት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስልዎታል?

መ - እዚህ ላይ አንድ ነገር ይታየኛል:: ይህ ጥያቄ በክፍል ውስጥ መጽሐፉን እየተጠቀመበት ለሚገኘው መምህር የሚገባ ይመስለኛል:: የበለጠ መረጃ የሚገኘው ከመምህሩ መሆኑ ይሰማኛል:: መቼም ለየትኛውም ሥራችን ከፍተኛው የመረጃ ምንጫችን መምህራን በመሆናቸው መጽሐፉን ለማሻሻል መረጃ ስንሰበስብ ስለችግሩ መረጃ የምናገኘው ከነሱና ከተማሪዎቻቸው ነው:: በዚህ ረገድ ግን ችግር አለ የሚል መረጃ ከመምህራን ያገኘንበት ቀን ትዝ አይለኝም:: እኔም በራሴ መጽሐፍቱን ስመረምር በዚህ በኩል ችግር ያለ አይመስለኝም::

4. ጥ - ተማሪዎች ዓላማዎቹን ከዳር ማድረሳቸውን ለማሳየት ማድረግ ያለባቸውን በመግለጽ ነው የተጻፉት?

መ - ዓላማዎቹ መንገዳቸውን ይዘዋል ወይ? ከሆነ ጥያቄህ መልሴ አይደለም ነው:: መጽሐፍቱ በሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ በሀገሪቱ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሞክረን ነበር:: ትልቁ ኮመንታቸውም ዓላማዎቹ ግልጽ አይደሉም የሚል ነው::

5. ጥ - ዓላማዎቹ በእድገት ተከታታይነት ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - ዓለማዎቹ በዚህ ረገድ ችግር የለባቸውም ማለት ይቻላል:: ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ባሕሪን የያዙ ናቸው::

6. ጥ - ዓላማዎቹ ምንን የሚያሳዩ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹ በውስጣቸው የያዙት ከተማሪው የሚጠበቀውን የባሕሪ ለውጥ ነው:: ከዚህ ባሻገር የያዙት ነገር የለም::

7. ጥ - ዓላማዎቹ ተማሪዎቹ እንዲያሳዩ የተፈለገውን የባሕሪ ለውጥ ዓይነት ለመረዳት በማያዳግት መንገድ የተጻፉ ይመስልዎታል?

መ - ዓላማዎቹ ግልጽ ናቸው ወይ? ነው የምትለኝ? ጥያቄህ ይሄ ከሆነ ግልጽ አይደሉም መልሴ ነው:: የምሰጥህ መልስ ምክንያታዊ ነው:: ይሄውም ዓላማዎቹ የተነደፉባቸው ቃላት የአጠቃላይነት ባሕሪ ያላቸውና የተወሰነ የባሕሪ ለውጥ አይነትን ስለማያመለክቱ ነው::

8. ጥ - ዓላማዎቹ ለቋንቋው ክሂሎችና የእውቀት ዘርፎች ተመጣጣኝ ትኩረት የሚሰጡ ይመስልዎታል?

መ - የጥያቄው አቀራረብ ጥሩ ነው:: ይሄውም እኩል ትኩረት ይሰጣሉ ወይ? ብትለኝ ኖሮ ለመመለስ እቸገራለሁ:: የጠየከኝ ግን የተመጣጣኝነት ጉዳይ በመሆኑ ዓላማዎቹ የተመጣጣኑ ትኩረት ለየትምህርት ክፍሎቹ እንደሚሰጡ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ::

9. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የተማሪውን የክፍል ደረጃ የሚመጥኑ ይመስልዎታል?

መ - ይዘቶቹ የክፍል ደረጃውን እንዲጠብቁ ተደርገው መዘጋጀታቸው አያጠራጥርም:: እዚህ ላይ ግን ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጥቂት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: ይሁንና ግን በመጽሐፍ ዝግጅት ወቅት የተማሪዎች እድሜና የክፍል ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ እኛም በዝግጅነታችን ወቅት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተነዋል::

10. ጥ - በመርሀ - ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - ይዘቶቹ በክፍል ደረጃው ቋንቋውን ለማስተማር ይችላሉ:: ይህንንም ዓላማ ከዳር ለማድረስ ብቃት አላቸው ብዬ አምናለሁ:: መቼም ተገቢነት የሚለው ጥያቄ ከጊዜ ጋርም የሚሄድ ይመስለኛል:: አሁን ባለንበት ሁኔታ ውስጥ ይዘቶቹ ቋንቋውን ለማስተማር ተገቢነት አላቸው:: በጊዜ ውስጥ ደግሞ መሻሻል ያለባቸውን እያሻሻልን እንሄዳለን::

11. ጥ - ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው ብለው ያስባሉ?

መ - 10ኛ ክፍል አስተምረህ ከሆነ ደዘቶቹ ከቋንቋው ትምህርት ሌላ ለምንም ነገር ትኩረት እንደማይሰጡ የምታውቅ ይመስለኛል:: የቅድሚያ ትኩረታቸው የቋንቋው ትምህርት ነው::

12. ጥ - ይዘቶቹ የትምህርቱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ ብቃት ያላቸው ይመስልዎታል?

መ - ይሄ ጥያቄ ወደ መጠን የሚወስደን ይመስለኛል:: ይሄውም ምን ያህሉ ናቸው ከዓላማው ጋር የሚስማሙት? ወደሚለው የሚያዘነብል ይመስላል:: ሙሉ ለሙሉ ባልልህም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ከዓላማው ጋር ይስማማሉ:: በጣም ጥቂት የሆኑት እንከን አያጡም:: ይህ ደግሞ በሂደት የሚስተካከል ጉዳይ ነው::

13. ጥ - ይዘቶቹ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የተደራጁ ይመስልዎታል?

መ - ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአጠቃላይ ወደተናጠል የሚያስኬደውን አደረጃጀት ተከትለው ነው የተደራጁት:: ባለፈው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያገለግል የመምህር መምሪያ የሠራን ሲሆን በዚህም ጊዜ እንዳስተዋልኩት የይዘቶቹ አደረጃጀት ችግር የለበትም::

14. ጥ - ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ተጠብቆ የተደራጁ ይመስልዎታል?

መ - ይዘቶቹ ተከታታይነታቸው ተጠብቋል ማለት ይቻላል:: ይህ መልስ ግን ሙሉ ለሙሉ ነው የሚለውን አያመለክትም:: በዚህም በኩል ችግር አይታይም ለማለት ባይቻልም ከፍተኛውን እጅ የያዙት ይዘቶች ተከታታይነታቸው ተጠብቆ ነው የተደራጁት::

15. ጥ - የይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ተጠብቋል ብለው ያምናሉ?

መ - በአንድ የመጽሐፍ ዝግጅት ወቅት በቅድሚያ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን ነጥብ አሁን የጠየከኝ ጥያቄ ነው:: ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ መሄድ አለባቸው:: እኛም ይህንኑ መርህ ተከትለን ይዘቶቹን እንዳደራጀናቸው ይሰማኛል::

16. ጥ - በ10ኛ ክፍል የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በክፍል ደረጃው ከሚሰጡት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የሚደጋገፍ ይመስልዎታል?

መ - ይዘቶቹ ከሌሎች የትምህርት ክፍሎች ጋር ያላቸው ዝምድና ተጠብቋል ብዬ ለመናገር ይቸግረኛል:: ተጠብቋል ለማለት ከደፈርኩ ደግሞ ለዚህ ተጨባጭ ማስረጃ መስጠት የሚያስፈልገኝ ይመስለኛል:: በዚህ ረገድ ብዙ ሥራ ይቀረናል ብዬ አስባለሁ::

« አባሪ መ »

## በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የቋንቋ መሠረተ ሃሣቦችን ያውቃሉ
2. ድርሰት መጻፍ ይችላሉ
3. የቃላት ችሎታን ያዳብራሉ
4. ምዕላዶችን ያውቃሉ
5. የቋንቋውን አሰካክ ያውቃሉ
6. የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ሃሣቦችን ያገናዝባሉ
7. ተጠያቂያዊ አስተሳሰብን ያዳብራሉ
8. የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ሃሣባቸውን ያዳብራሉ
9. ድርሰት የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ
10. የቋንቋውን አሰካክ ያውቃሉ
11. ፍሬ ሃሣቦችን ከዝርዝር ሃሣቦች አንብቦ መለየት ይችላሉ
12. ድርሰት የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ
13. የልቦለድ አጻጻፍን ያውቃሉ
14. የግጥም አጻጻፍን ያውቃሉ
15. የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ሃሣቦችን ይገነዘባሉ
16. የተወሰነ ሃሣብን በራስ አባባል የማቅረብ ዝዴን ያዳብራሉ
17. ድርሰት የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ
18. የኢልቦለድ አጻጻፍን ያውቃሉ
19. የልቦለድ አጻጻፍን ያውቃሉ

በአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ - ትምህርት ውስጥ የታቀፉ ይዘቶችና በይዘቶቹ አማካኝነት ተማሪዎቹ እንዲያከናውኗቸው የተወሰኑ የማስተማር - መማር ሂደት ተግባራት አደረጃጀት መግለጫ

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| የቋንቋ መሠረተ - ሀሣቦች | • ስለ ቋንቋ የመግባቢያ መሣሪያነት ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • ስለ ቋንቋ አመጣጥ ይገነዘባሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • ስለ ቋንቋ ምንነት፣ አገልግሎትና ምንጭ ይናገራሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| | • ስለ ቋንቋ ምንነት፣ አገልግሎትና ምንጭ ይፅፋሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| | • ስለ ቋንቋ አመጣጥ ቃለ መጠይቅ ያካሂዳሉ | ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| | • ስለ ቋንቋ አመጣጥ በቃለ መጠይቅ ያገኙትን ሃሣብ ቁሳካላዊ ወይም ሃሣባዊ መሆኑን ይገመግማሉ | ትችት - ግምገማ |
| | • ስለ ቋንቋ አመጣጥ በቃለ መጠይቅ ሃሣብ በመሰብሰብ የራሳቸውን አስተያየት ጨምረው ያመጣሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| | • ስለ ቋንቋ አጀማመርና መለያየት ታሪካዊ መፃሕፍት አንብበው ይረዳሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| | • ስለ ቋንቋ አጀማመርና መለያየት ታሪካዊ መጻሕፍት ያቀረቡት ሃሣብ ቁሳካላዊ ወይም ሀሣባዊ በመሆኑ ላይ ይወያያሉ | ትችት - ትንተና |
| | • በንግግርና በፅሕፈት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • የጽሕፈትን አገልግሎት ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| ቃላትን አገጣጥሞ መጻፍ | • ያልተሟሉ ዐ. ነገሮችን በተስማሚ ቃላትና ሀረጐች ያሟላሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| | • ያልተሟሉ አንቀጾችን በተስማሚ ቃላትና ሀረጐች ያሟላሉ | ሽግግር _ በሥራ ላይ ማዋል |
| | • ቃላትን አገጣጥመው ዐ. ነገርን ይሠራሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| | • በዐ. ነገርም ሆነ በጽሑፍ ውስጥ የማያስፈልግ የቃላት ድግግሞሽን ሳይጠቀሙ መጻፍ ይችላሉ | ተግባቦት - እራስን መግለጽ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | • የተለያዩ ባሕርይ / ማለት የስያሜ፣ የገላጭ ወዘተ ... / ያላቸውን ቃላት በዐ. ነገር ውስጥ በማስገባት መጠቀም ይችላሉ<br>• ባንድ ጊዜ ብዙ ነገር የሚያመለክቱ ቃላትን ፍቺ ይለያሉ<br>• ባንድ ጊዜ ብዙ ነገር የሚያመለክቱ ቃላትን በመተርጎም በነዚያ ቃላት ዐ. ነገር መሥራት ይችላሉ<br>• ከተለያዩ ሣጥኖች ውስጥ ቃላትን ወስደው በማገጣጠም ዐ.ነገር ይመሰርታሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር _ በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት _ ማስታወስ |
| የቃል ቀጥታ ትርጉም | • የተለያዩ ቃላትን ትርጉም ያውቃሉ<br>• ከጽሑፍ ውስጥ የጽሑፉን ዋና ዋና ሀሣቦች የያዙ ቃላትን ትርጉም መለየት ይችላሉ<br>• በዐ. ነገር ውስጥ በቀጥታ ትርጉማቸው ያልገቡ ቃላትን መለየት ይችላሉ<br>• በዐ. ነገር ውስጥ በቀጥታ ትርጉማቸው ያልገቡ ቃላትን በመለየት በቀጥታ ትርጉማቸው ዐ. ነገር ሊመሠርቱባቸው ይችላሉ<br>• በዐ. ነገር ውስጥ በቀጥታና በአገባብ ትርጉሙ የገባ ቃልን ለይተው ያመለክታሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘ |
| ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት | • ከምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ መስጠት ይችላሉ<br>• ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ በመስጠት በዐ. ነገር ውስጥ በማስገባት መገልገል ይችላሉ<br>• በተስማሚ ቃላት ባዶ ቦታዎችን መሙላት ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - መረዳት |
| ገላጭ - | • የስም ገላጭ የጐደላቸውን ዐ. ነገሮችን በትክክል ማሟላት ይችላሉ<br>• ከዐ. ነገሮች ውስጥ ስሞችንና የስም ገላጮችን መለየት ይችላሉ<br>• ገላጮችን እንደ ስም በመጠቀም ልዩ ልዩ ዐ. ነገሮች ለመሥራት | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| የስም ገላጭ | ይችላሉ<br>• ከገላጮች መካከል ጥያቄን ለማቅረብ የሚያገለግሉትን ለይተው ያውቃሉ<br>• ከገላጮች መካከል ጥያቄን ለማቅረብ በሚያገለግሉት በትክክል ይጠቀማሉ<br>• የመስተአምርን አገልግሎት ለይተው ያውቃሉ<br>• በመስተአምር በሚገባ ሊጠቀሙ ይችላሉ | ዕውቀት - ማስታወስ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| የግል ገላጭ | • ከዐ. ነገሮች ውስጥ የግስ ገላጮችን ለይተው ማውጣት ይችላሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ዐ. ነገሮች ውስጥ ተገቢውን የግስ ገላጮች ማስገባት ይችላሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ የግስ ገላጮችን በትክክል በዐ. ነገር ውስጥ ሊገለገሉባቸው ይችላሉ<br>• የግስ ገላጮች ሌሎች የግስ ገላጮችን በሚገልጹበት ሁኔታ በዐ. ነገር ውስጥ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ | ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| በቃል ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት | • በቃል ውስጥ ያሉ ድምጾች ሲጠብቁና ሲላሉ የሚያመጡትን የትርጉም ልዩነት በዐ. ነገር ውስጥ ለማሳየት ይችላሉ<br>• ከተሰጣቸው የቃላት ዝርዝር ውስጥ የሚጠብቁትንና የማይጠብቁትን ቃላት ልዩነት ያውቃሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| የቃላት አመሠራረት - ቅጥያዎችን በቃል | • ለደረጃው በሚመጥኑ የቃላት ግንድ ላይ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን መጨመር ይችላሉ<br>• በመድረሻና በመነሻ ላይ ቅጥያዎች የተጨመረባቸው የቃላት ግንድ የሚያሳዩትን የቅርፅና የትርጉም ለውጥ ይረዳሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| ግንድ ላይ በመጨመር | • ድርጊት ፈጻሚን ወይም ባለቤትን የሚያመለክቱ መድረሻ ቅጥያዎችን በቃል ግንድ ላይ በመጨመር የባለቤት ዝርዝርን ያውቃሉ<br>• የፆታ፣ የመደብና የቁጥር እንዲሁም ወሳኝ የመድረሻ ቅጥያዎችን አጠቃቀም በሚገባ ይለማመዳሉ<br>• ማሰሪያ አንቀፆችን እንዳያስሩ የሚያደርጉ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችንና በነሱም ምክንያት በቃላቱ ግንድ ላይ የሚፈጠረውን የቅርፅና የፍቺ ለውጥ ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| የቃላትን ቅርፅ በፆታ በመደብና በቁጥር መለያየት /ኢንፍሌክሽን/ | • መድረሻ ቅጥያዎች የቃላትን ቅርፅ በመቀየር የድርጊት ፈጻሚውን ማንነት፣ ጾታውንና ቁጥሩን የሚያሳዩ መሆናቸውን ተማሪዎቹ በሚገባ ይረዳሉ<br>• ቁጥራቸው ነጠላ የሆነ ድርጊት አመልካች የቃላት ግንድ ፆታን መለያ ያላቸው መሆኑንና የብዙ ቁጥር ቅርፅ ያላቸው ግን ከወል በስተቀር ሌላ ፆታን በቅርጻቸው ላይ የሚያሳዩ መሆናቸውን ተማሪዎች ይረዳሉ<br>• በግስ ቃላት ግንድ ላይ የፆታ፣ የመደብና የቁጥር ቅጥያዎችን መጨመር የሚያስከትለውን የትርጉም ለውጥ ይረዳሉ<br>• ልዩ ልዩ ስሞችን በፆታና በቁጥር ይለያሉ<br>• የፆታና የቁጥር አስካክ የጎደላቸውን ዐ. ነገሮች ማስተካከል ይችላሉ<br>• አክብሮትንና የብዙ ቁጥርን በሚገልፁ ቅርፆች መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| አንቀፅ ከሆነ የቃላተ ግንድ ራሳቸውን | • ለደረጃው ከሚመጥኑ የግስ ቃላት ግንድ ስም መሰልና ገላጭ መሰል ቃላትን ማውጣት ይችላሉ<br>• ለደረጃው ከሚመጥኑ ዐ. ነገሮች ውስጥ ስም መሰልና ገላጭ መሰል | ሽግግር - መረዳት |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| የቻሉ ስም መሰሎችና ገላጭ መስሎች ቃላትን ወዘተ... ማውጣት | ቃላትን መለየት ይችላሉ<br>• ስርወ ቃላትን አውጥተው ማሳየት ይችላሉ<br>• የቃላት ግንድ፣ ስም መሰልና ገላጭ መሰል ቃላት ተዘበራርቀው ከሚገኙበት ዝርዝር ውስጥ ሁሉን በየዓይነቱ መለየት ይችላሉ<br>• ለደረጃው ከሚመጥኑ የቃላት ግንድ የሚያወጧቸውን ስም መሰልና ገላጭ መሰል ቃላት በዐ. ነገር ውስጥ ሊገለገሉባቸው ይችላሉ | ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - መረዳት |
| የቃል: የሀረግና የዐ.ነገር ልዩነት | • በአማርኛ ውስጥ ሀረግ በቅርፅ ደረጃ ሲታይ ከአንድ በላይ ቃላት ያሉት ማለት አለመሆኑን ያውቃሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ዐ. ነገሮች ውስጥ የገቡ ረዘም ያሉ ሀረጎችን በአንድ ቃል፣ ሀረግ ወይም አጠር ባሉ ሀረጎች ሊተኩዋቸው የሚያስችል እውቀት ያገኛሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ቃላት ነጠላና ድርብ ዐ. ነገር በትክክል መሥራት ይችላሉ<br>• በነጠላ ዐ. ነገርና በድርብ ዐ. ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ዐ. ነገሩን በመሥራት ይረዳሉ<br>• ድርብ ዐ. ነገርን በልዩ ልዩ የዐ. ነገር መልኮች ይሠራሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| የሆሄያትና የቃላት በሥርአት መደርደር የትርጉም ለውጥ ማምጣት | • የቃላት አደራደር ልዩነት የትርጉም ልዩነት የሚያመጣ መሆኑን በሚገባ ይረዳሉ<br>• የተሰጣቸውን ቃላት ብቻ በሥርአት በመደርደር ልዩ ልዩ ዐ. ነገሮችን መሥራት ይችላሉ<br>• አሰላለፋቸው የተዘበራረቀ ለደረጃው የሚመጥኑ ቃላትን አስተካክለው የተሟላ ዐ. ነገር ማድረግ ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | • ከሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ የቃላት አደራደር ስህተት የሚታይባቸውን ዐ. ነገሮች መለየት ይችላሉ<br>• ከሚያነቡት ጽሁፍ ውስጥ የቃላት አደራደር ስህተት የሚታይባቸውን ዐ. ነገሮች ማስተካከል ይችላሉ<br>• የዐ. ነገሮችን ቃላት አደራደር በመቀየር ዐ. ነገሮቹ ከበፊቱ የተለየ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ይችላሉ | ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| የቃላትን፣ የሀረ ጐችንና የዐ. ነገሮችን ትርጉም አንብቦ መረዳት | • ለደረጃው ከሚመጥኑ የተለያዩ ዐ. ነገሮች ውስጥ የተወሰኑ ቃላትን በማውጣት ትርጉማቸውን ከአገባባቸው ሊያወጡ ይችላሉ<br>• ባዶ ቦታ ያላቸውን ዐ. ነገሮች በትክክለኛዎቹ ቃላት መሙላት የሚያስችል እውቀት ያገኛሉ<br>• የቃላትን ልዩ ልዩ አገባባዊ ፍቺ በዐ. ነገር ውስጥ ሠርተው ማሳየት ይችላሉ<br>• በፊት የሚያውቋቸውን ቃላት በዐ. ነገር ውስጥ ሲያገኟቸው ከአገባባቸው ትርጉማቸውን መናገር ይችላሉ<br>• አገባባዊ ትርጉማቸው የሚለያይ ሀረጐችን በዐ. ነገር ውስጥ ሊገለገሉባቸው ይችላሉ<br>• በውስጠ ታዋቂነት በቀሩና ፈጽሞ ባልተገለጹ ፍንጭ በሌላቸው ሃሣቦች መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ<br>• ግልጽነት የጎደላቸውን ዐ. ነገሮች ግልጽነታቸውን ማሟላት ይችላሉ<br>• ለደረጃው ከሚመጥን ጽሁፍ ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት የቀሩ ሃሣቦችን የሚገልፁ ቃላት የጎደሏቸውን ዐ. ነገሮች ይለያሉ<br>• በውስጠ ታዋቂነት የቀሩ ሃሣቦችን የሚገልፁ ቃላት የጎደሏቸውን ዐ. | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - ማስታወስ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - መረዳት |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | ነገሮች ማሚያዎቹን ልዩ ልዩ ቃላት መስጠት ይችላሉ<br>• በውስጠ ታዋቂነት የቀሩ ሃሣቦችን የሚገልፁ ቃላት የጎደሏቸውን ዐ. ነገሮች አሟልተው በእነዚህ ዐ. ነገሮች የተገለጸውን ሃሣብ በሌላ አባባል መግለጽ ይችላሉ<br>• በውስጠ ታዋቂነት የቀሩ ሃሣቦች የሚገኙባቸው ዐ. ነገሮች ከጽሁፍ ይልቅ ብዙ ጊዜ በንግግር ውስጥ የሚሠራባቸው መሆኑን ከነምክንያቱ ያውቃሉ | ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ልዩ ልዩ የንባብ መመሪያዎችን መከተል | • የሥርአተ - ነጥቦችን አገልግሎት ጠብቀው ማንበብ ይችላሉ<br>• የተለያዩ መመሪያዎችን በማንበብም ሆነ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ሊነጋገሩባቸው ይችላሉ<br>• የተለያዩ መመሪያዎችን በማንበብም ሆነ በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ<br>• በምንባብ ወይም በጽሁፍ የቀረቡ ዝርዝር መመሪያዎችን ተከትለው መሥራት ይችላሉ<br>• ከቀረበላቸው ጽሁፍ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችንና መመሪያዎችን በመከተል መመለስ ይችላሉ<br>• ስለ አንዳንድ ነገሮች የራሳቸውን መመሪያ በማውጣት በሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ<br>• በቅርብ ቀን በልዩ ልዩ ድርጅቶች የወጡ መመሪያዎችን ይዘት በደረጃቸው ይረዳሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ዕውቀት - ማስታወስ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| የውይይት | • ለደረጃው በሚመጥኑ ርእሶች ላይ ሥርአት ጠብቀው መወያየት ይችላሉ<br>• በሥርአታዊ /ፎርማል/ ውይይት ተካፋይ በሚሆኑበት ጊዜ ርእሱን | ተግባቦት - እራስን መግለጽ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| ሥርአት | እንደችሎታቸውና ዝንባሌያቸው መከፋፈል እንደሚጠቅም ይረዳሉ<br>• ተካፋይ የሆኑበትን ንኡስ ርዕስ የሚመለከቱ ከአድማጮች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በሚገባ መመለስ ይችላሉ<br>• በውይይት ውስጥ መተቸት ተፈላጊ መሆኑን ይረዳሉ<br>• የውይይት ሪፖርተር /ፀሀፊ/ ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ያውቃሉ<br>• በውይይት ያዳመጧቸውን ዋና ዋና ሀሣቦች በሚገባ ማጠናቀርና ማቅረብ ይችላሉ<br>• በውይይት ውስጥ የስብሰባ ሥርአቶችን /ፓርላሜንታሪ ፕሮሲጆር/ መከተል ወሳኝ መሆኑን ያውቃሉ<br>• በስብሰባና በውይይት ውስጥ የሊቀመንበርን ተግባር በዝርዝር ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - ማስታወስ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| የክርክር ሥርዓት | • የተከራካሪ አሸናፊ የሚወሰነው በሚያቀርበው ነጥብ ብዛትና በማስረጃው ጥንካሬ መጠን መሆኑን በሚገባ ይረዳሉ<br>• ሁለት ተቃራኒ ሁኔታዎችን ማነፃፀር የአከራካሪ ነጥቦች መሠረታዊ መልክ መሆኑን ያውቃሉ<br>• አከራካሪ ሃሣቦችን መመሥረት ይችላሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥን ርእስ ላይ ሥርአትን ጠብቀው፣ የራሳቸውን ዳኛ መርጠው መከራከር ይችላሉ<br>• ያዳመጧቸውን ዝርዝር ፍሬ ነገሮችና ከተከራካሪዎቹ መካከል ድክመት ያዩበትን ወገን በመለየት ሃሣባቸውን በማስረጃ እየደገፉ ማቅረብ ይለማመዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ትችት - ግምገማ |
| | • በጭውውትና በክርክር መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| የጭውውት ሥርዓት | • በጣም አስፈላጊ ካልሆነና በደንብ ያልተብራራ ካልመሰለ በስተቀር በሌሎች የጭውውት ተካፋዮች የተጠቀሰን ሃሣብ መድገም ፀያፍ መሆኑን ይረዳሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ርእሶች ዙሪያ በመዘጋጀት የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢዎችን ወይም አክተሮችን መስለው መቅረብ ይለማመዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ማዋሀድ |
| የቤተ መጻሕፍት /በተለይ/ የመጻሕፍት አፈላለግ አጠቃቀም | • በካታሎግ እየተጠቀሙ የሚፈልጓቸውን ልዩ ልዩ መጻሕፍት ለማግኘት ይችላሉ<br>• የሚፈልጓቸውን መጻሕፍት ለይቶ ለማምጣት በአጠቃላይ የመጻሕፍት አደራደር /ሳይንስ፣ ፍልስፍና፣ ሥነ ጽሁፍ ወዘተ.../ ሊገለገሉ ይችላሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| በቡድንና በተናጠል ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ | • የድምጾችን መነሳትና መውደቅ፣ በዐ. ነገርና በዐ. ነገር መካከል መኖር የሚገባውን የድምጽ አገታት ወዘተ... እየጠበቁ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ ይችላሉ<br>• አንድን ጽሁፍ ድምጽን ከፍ አድርጎ በሚነበብበት ጊዜ በዐ. ነገሮችና በአንቀጾች መጨረሻ ላይ ከአድማጮች ጋር የዓይን ግንኙነት አስፈላጊ መሆኑን ይረዳሉ<br>• ድምጽን ከፍ አድርጎ የማንበብ ተግባር እንደጽሁፉ ይዘት በእጆችና በሌላም የሰውነት ክፍል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችንም እንደሚጠይቅና ይህም ሃሣቡ ለአድማጮች በግልጽ ሁኔታ ለማቅረብ እንደሚረዳ ይገነዘባሉ | ዕውቀት - ማስታወስ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ጥሩ የማንበብ | • ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ፍሬ ነገሮችን ለመቅሰም የታሪኩን ቅደም ተከተል ጠብቆ የማንበብ ልምድን ያዳብራሉ | ሽግግር - መረዳት |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| ልምዶችን መመሥረት | • ለደረጃቸው የሚመጥኑ ርእሶችን ሰጥቶ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ደራሲያን ስለ ርእሶቹ የተጻፉ ጽሁፎችን በመሰብሰብ እያመሳከሩ በማየት የማጥናት ልምድ ያዳብራሉ<br>• አንድ ጽሁፍ በሚነበብበት ጊዜ ሃሣቡን በደንብ ለመረዳት ተያይዘው የሚገኙትን ሥእላዊ መግለጫዎች በትኩረት መመልከት ጠቃሚ ልምድ በመሆኑ ይህንኑ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ጠቃሚ ልምድ ያገኛሉ<br>• ያነበቡትን ነገር ሁሉ እንደ እውነተኛ ነገር ላለመውሰድና እርግጠኛነቱን ለመመርመር የመጣር ልምድ ያዳብራሉ | ትችት - ትንተና<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ትችት - ትንተና |
| በዝግታ አንብቦ ሃሣብን መረዳት | • በደረጃው ጠለቅ ያሉ ጽሁፎችን በዝግታ በማንበብ አንዳንድ ተዘዋዋሪ ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ<br>• የዝግታ ንባብ ፍጥነትም ቢሆን በልምምድ የሚሻሻል መሆኑን ይገነዘባሉ<br>• የዝግታ ንባብ ፍጥነታቸውን ያሻሽላሉ<br>• ጥናታዊ ንባቦች ሁሉ በዝግታ መነበብ የሚጠይቁ መሆናቸውን ይገነዘባሉ<br>• የዝግታ ንባብ ከብዙ ትኩረት፣ እንዲሁም ማመሳሰል ጋር የተያያዘ መሆኑን ይገነዘባሉ | ትችት - ትንተና<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| በፍጥነት አንብቦ ሃሣብን መረዳት | • በሚያነቡበት ጊዜ አይኖቻቸው ቃላትን በተናጠል ሳይሆን ሀረጎችን፣ ከተቻለም ዐ. ነገሮችንና አንቀፆችን በአንድ ጊዜ በማየት ማንበብ ይችላሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ አጠር አጠር ያሉ ጽሁፎችን በተወሰነ ጊዜ በፍጥነት በማንበብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ<br>• አጠር አጠር ያሉ ጽሁፎችን በተወሰነ ጊዜ በፍጥነት በማንበብና የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በመመለስ የንባብ ፍጥነታቸውን ያሻሽላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| በአሰሳ አነባበብ<br><br>የሚፈለጉ ነጥቦችን ማግኘት | • የሚፈለጉ ነጥቦችን በአሰሳ ንባብ ለማግኘት ከጽሁፉ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ሥእሎች፣ ግራፎች፣ ሠንጠረዦች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይረዳሉ<br>• በአሰሳ ንባብ አማካኝነት የሚፈለጉ ነጥቦችን ለማግኘት ከጽሁፉ ጋር ተያይዘው የሚገኙ ሥእሎችን፣ ግራፎችን፣ ሠንጠረዦችን፣ ርእሶችንና ንኡስ ርእሶችን ወዘተ... መገልገል ይችላሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ጽሁፎችን በአሰሳ መልክ በማንበብ ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br><br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br><br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| ከቅርጻ ቅርጽ የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • ለደረጃው የሚመጥኑ ቅርጻ ቅርጽን ተመልክተው የተረዱትን ሃሣብ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ<br>• ከአካባቢያቸው የሚገኙ አንዳንድ ቅርፃ ቅርጽን እንዳመቺነቱ እያሰበሰቡ አምጥቶ በመመርመር አንዳንድ አጠቃላይ ሃሣቦችን ማግኘት ይችላሉ<br>• ከአካባቢያቸው ሰብስበው ካመጧቸው ቅርጻ ቅርጽ የተረዱትን ሃሣብ በክፍል ውስጥ ይነጋገሩበታል | ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br><br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br><br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| ከሥእላ ሥእሎች የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • ተከታታይ ታሪክ የያዙ ሥዕሎችን በመመልከት ታሪኩን ይረዳሉ<br>• ሲመለከቷቸው የሚመሳሰሉ፣ ሆኖም ልዩነት ያላቸውን ለደረጃው የሚመጥኑ አንድ ዓይነት ሥእሎችን ልዩነታቸውን በንግግር ወይም በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ<br>• አስደናቂና ጥልቀት ያላቸውን ሥዕላ ሥዕል በማምጣት የገባቸውን ሃሣብ ለጓደኞቻቸው ይገልጻሉ<br>• በመሰላቸውና በሚችሉት መጠን አንዳንድ ሃሣቦችን በሥዕል ለመግለጽ ይችላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br><br>ትችት - ትንተና<br><br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br><br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
| --- | --- | --- |
| ከፎቶግራፎች የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • ፎቶግራፎች እንደ ሥዕላ ሥዕል ሁሉ በጽሁፍ ውስጥ ጣልቃ እየገቡ አንዳንድ ሃሣቦችን ለማጉላትና ለማብራራት እንደሚያገለግሉ ያውቃሉ<br>• የተወሰኑ ፎቶግራፎችን በማየት የሚረዱትን ሃሣብ በንግግር መግለጽ ይችላሉ<br>• የተወሰኑ ፎቶግራፎችን በማየት የሚረዱትን ሃሣብ በጽሁፍ መግለጽ ይችላሉ<br>• ፎቶግራፎችን አዘጋጅተው በማምጣት ተከታታይ ሃሣብን ወይም ታሪክን ለማቅረብ ማገልገላቸውን ማሳየት ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| ከግርጌ መግለጫ /ካፕስን/ የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • የግርጌ መግለጫዎች አጭር፣ ግልጽና ዋናውን ሃሣብ አሚልተው የሚያሳዩ ሆነው መዘጋጀት ያለባቸው መሆኑን ያውቃሉ<br>• በደረጃቸው ሃሣቡ ለሚገባቸው ፎቶግራፎችና ሥዕላ ሥዕል ተገቢ የግርጌ መግለጫ ማዘጋጀት ይችላሉ<br>• ከግርጌ መግለጫዎች የተለየ ባህሪዎች ምን ምን እንደሆኑ ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ከሠንጠረዥ የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • በሠንጠረዥ ተደግፈው የቀረቡ ምንባቦችን ሃሣብ መረዳት ይችላሉ<br>• በቃላት ለመግለጽ በጣም የሚንዛዙትንና ተነጻጻሪ ሃሣቦችን ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ሠንጠረዥ ትልቅ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ያውቃሉ<br>• በሠንጠረዥ ሊቀርቡ የሚችሉ ዝርዝር ሃሣቦችን በደረጃቸው በሠንጠረዥ አደራጅተው ሊያቀርቡ ይችላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ማዋሀድ |
| | • በካርታ ሊገለፁ የሚችሉ ሃሣቦችን በደረጃቸው ለይተው ያውቃሉ<br>• በካርታ ሊገለፁ የሚችሉ መሰል ሀሣቦችን በካርታ ላይ ማደራጀት ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ማዋሀድ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| ከካርታ የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • ለደረጃው የሚመጥኑ ካርታዎችን በመመርመር የሚያሳዩትን ሀሣቦች መተርጐም ይችላሉ<br>• በካርታ አማካይነት ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን ያውቃሉ<br>• በካርታ ለመገልገል ይችላሉ<br>• የአካባቢያቸውን ወይም የፈለጉትን አንድ ሥፍራና በውስጡ ያሉትን በጣም አስፈላጊ ቦታዎች የሚያሳይ ካርታ በማዘጋጀት በካርታ መጠቀም ይችላሉ<br>• ለአንድ ጽሁፍ ማብራሪያ የሚሆን ካርታን ከጽሁፉ ጋር አገናዝበው የተሟላ ሃሣብ ማግኘት ይችላሉ | ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| ከተጨማሪ ማብራሪያ /አፔንዴክስ/ የመረጃ ሀሣቦችን ማግኘት | • በተጨማሪ ማብራሪያና በዋና ጽሁፍ መካከል ያለው ግንኙነትና ልዩነት ይለያሉ<br>• በዳረጃው ጥናት አድርገው አንድ መጠነኛ ጽሁፍ ከነተጨማሪ መግለጫው ማዘጋጀት ይችላሉ<br>• የግርጌ ማስታወሻ የተባለው በየገፁ ግርጌ የሚጻፍ መሆኑን ይገነዘባሉ<br>• የግርጌ ማስታወሻ ተግባር ምን ምን እንደሆነ በዝርዝር ይረዳሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| ከግርጌ ማስታወሻ /ፉት ኖት/ የመረጃ ሃሣቦችን ማግኘት | • የግርጌ ማስታወሻን አጻጻፍና አጠቃቀም በዝርዝር ያውቃሉ<br>• በአንድ ገጽ ላይ ከአንድ በላይ የግርጌ ማስታወሻ የሚጠይቁ ሃሣቦች ካሉ ሃሣቦቹን አንዱን ከሌላው መለየት በሚያስችሉ ምልክቶች መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን ይረዳሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥን ርዕስ አንድ መጠነኛ ጥናት አድርገው ጽሁፍ በማዘጋጀት የግርጌ ማስታወሻ አጠቃቀምን ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ማዋሀድ |
| ዐ. ነገርን | • ቅደም ተከተላቸው የተዛባ ዐ. ነገሮችን በማስተካከል የተሟላ ዐ. ነገር | |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| አገጣጠም አንቀጽ መጻፍ | ሊያደራጁ ይችላሉ<br>• ቅደም ተከተላቸው የተዛባ የአንድ አንቀጽ ዐ. ነገሮችን አስተካክለው አንድ አንቀጽ ማድረግ ይችላሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ርዕሶች አንቀጽ የመጻፍ ችሎታ ያገኛሉ<br>• ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ ጅምር አንቀፆችን በሚገባ አሟልተው መጻፍ ይችላሉ | ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| የአያያዦች አጠቃቀም | • የአያያዥ ሆሄያትን፣ ቃላትንና ሀረጐችን አጠቃቀም ያውቃሉ<br>• በዐ. ነገር ውስጥ ያሉ አያያዦችን ትርጉማቸውን በማይለውጡ ሌሎች አያያዦች መተካት ይችላሉ<br>• በሀሣብ የሚገናኙ ዐ. ነገሮችን በአያያዥ ቅጥያዎችና ሀረጐች ማያያዝ ይችላሉ | ዕውቀት - ማስታወስ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| ዋናና ንኡስ ርእሶች፡ መንደርደሪያዎች | • ከዳመጡትና ካነበቡት ለደረጃው ከሚመጥኑ ይዘት ውስጥ ዋና ዋናና ዝርዝር ሃሣቦችን ለይተው ማቅረብ ይችላሉ<br>• ከሬዲዩ፣ ከቴሌቪዥንና ከልዩ ልዩ ስብሰባዎች፣ ውይይቶች ወዘተ... ካዳመጧቸው ንግግሮች የፈለጉትን መርጠው ዋናና ዝርዝር ሃሣቦችን በመለየት ያቀርባሉ<br>• ፍሬ ነገሮችና ዝርዝር ሃሣቦች የተምታቱበት ጽሁፍ በደረጃቸው ማስተካከል ይችላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል |
| ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች | • በደረጃቸው ማሳሰቢያዎችን /ሚሞዎችን/፡ አጫጭር ማስታወሻዎችን፣ የዘመድ ደብዳቤዎችን፣ የሥራ ደብዳቤዎችን መጻፍ ይችላሉ<br>• ስለ ማስታወቂያ /አድቨርታይዝመንት/ አዘገጃጀት ያውቃሉ<br>• የዘመድና የሥራ ደብዳቤዎችን በማዘጋጀት ልዩነታቸውንና | ትችት - ማዋሀድ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
| --- | --- | --- |
| | አንድነታቸውን ይለያሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ልዩ ልዩ ማስታወቂያዎችንና ማሳሰቢያዎችን በመሰብሰብ የቅርጽና የይዘት ልዩነታቸውን ይገነዘባሉ<br>• በደብዳቤ አጻጻፍ ውስጥ የአድራሻ ተስተካክሎ መጻፍ ያለውን ወሳኝነት ይረዳሉ<br>• በአንድ በተወሰነ ወቅት ሲፈጸም ያዩትን ድርጊት ዝርዝር በደብዳቤ መልክ ሁኔታውን ለማውቁ ጓደኞቻቸው ማቅረብ ይችላሉ<br>• በደረጃው የሀዘንና የግብገር ደብዳቤ አዘገጃጀትን ያውቃሉ<br>• የግብገር ደብዳቤ አዘገጃጀትን ያውቃሉ<br>• የግብገር ደብዳቤ መልስ አሰጣጥን ያውቃሉ | ትችት - ማዋሀድ<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| የአስተዋጽኦ አነዳደፍ | • ለደረጃው የሚመጥን አንድ ጽሁፍ አንብበው ወይም አንድን ንግግር አዳምጠው ያገኟቸውን ሃሣቦች በአጭር በአጭሩ በአስተዋጽኦ መልክ ለማዘጋጀት ይችላሉ<br>• አስተዋጽኦ መንደፍ ሀሣቦችን በዓይነት በዓይነታቸው ለመከፋፈልና የጽሁፍን ወይም የድርሰትን ድርጅ /ኦርጋናይዜሽን/ ለማሟላት ዋና መሣሪያ መሆኑን ይረዳሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ርእሶች ላይ ሃሣብ ሰብስበው ያገኙትን ሃሣብ በአስተዋጽኦ መልክ አደራጅተው ማቅረብ ይችላሉ<br>• በማንኛውም ርእስ ላይ አስተዋጽኦ ለመንደፍ መሠረቱ ስለርእሱ ሃሣብ ማግኘት መሆኑን ይገነዘባሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - እራስን መገለጽ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | • አስተዋጽኦ በጽሁፍ የሚቀርብን ነገር ለማደራጀት ብቻ ሳይሆን ንግግር ለማድረግ ሲፈለግ በማስታወሻነትም እንደሚያገለግል ይገነዘባሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| ሪፖርት አቀራረብ | • የአስተዋጽኦ ዝግጅት በሪፖርት አዘገጃጀት ሥራ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ ያውቃሉ<br>• አንድ ሪፖርት ጉዳዩን ብዙ ለማያውቁ፣ በቦታው ላልነበሩ ወይም ነገሩን በማስተዋል ላላጤኑ ሰዎች ሊቀርብ እንደመቻሉ መጠን ሀሣቡ ግልጽነትና ሥዕላዊነት እንዲሁም ትንታኔ ያለበት መሆን እንደሚገባው ያውቃሉ<br>• የሪፖርትን አዘገጃጀትና በውስጡ ሊይዛቸው የሚገባውን ነጥቦች በዝርዝር ያውቃሉ<br>• በስብሰባ ሪፖርት ወይም ቃለ ጉባዔና የአንድ ሥራ ክንውንን በሚመለከት በሚሰጥ ሪፖርት መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ መጻሕፍትን አንብበው ሪፖርት መስጠት ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| አንቀፆችን አገጣጥሞ አጭር ጽሁፍ መጻፍ | • ዐ. ነገሮች ተቀነባብረው አንቀፆች እንደሚመሰርቱ ሁሉ አንቀፆችም ተሳክተው ድርሰትን እንደሚመሰርቱ ማየት ይችላሉ<br>• እርስ በርስ ያልተያያዙ ስለ አንድ ርእስ የሚናገሩ አንቀጾችን በተገቢው አያያዦች ማቀናጀት ይችላሉ<br>• በደረጃው በዛ ያሉ አንቀፆችን የመጻፍ ችሎታ ያገኛሉ<br>• የሀሣብ ቅደም ተከተላቸው ያልተጠበቀ ለደረጃው የሚመጥኑ ጽሁፎችን አስተካክለው መጻፍ ይችላሉ<br>• በገላጭና በትረካ የድርሰት አጻጻፍ ሥልቶች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያመለክቱ ጽሁፎች በደረጃው ማዘጋጀት ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ትችት - ማዋሀድ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| የአንድ ድርሰት አንድነት ግጥምጥምነትና ትኩረት | • የቀረበላቸውን ድርሰት አንድነት፣ ግጥምጥምነትና ትኩረት ለይተው ማሳየት ይችላሉ<br>• የቀረበላቸውን ድርሰት አንድነት፣ ግጥምጥምነትና ትኩረት ለይተው በማሳየት በድክመቱና በጥንካሬው ላይ መነጋገር ይችላሉ<br>• የአንድ ድርሰት ሃሣቦች አንዱ በአንዱ ላይ በመገንባት እድገት እያሳዩ መሄድ ያለባቸው መሆኑን ይረዳሉ | ትችት - ትንተና<br>ትችት - ትንተና<br>እውቀት - መገንዘብ |
| ልዩ ልዩ የቃል ሥነ ጽሁፎች /ተረቶች፣ ምሣሌያዊ አነጋገሮች ወዘተ.../ | • በአካባቢያቸው በብዛት የተለመዱ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ሰብስበው ወደ ክፍል በማምጣት በፍቻቸው ምንነት ላይ መነጋገር ይችላሉ<br>• ሰብስበው ያመጧቸውን ምሣሌያዊ አነጋገሮች ጠቃሚነትና ጎጅነት ላይ መነጋገር ይችላሉ<br>• በጽሁፍ ውስጥ ተረትና ምሣሌዎችን መጠቀም የሚያስፈልገው በምን በምን ሁኔታ እንደሆነ ለይተው ያውቃሉ<br>• የቃል ሥነ ጽሁፍ፣ ለምሣሌ ተረትና ምሣሌያዊ አነጋገሮች የአንድ ኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነ ልቦናዊ ወዘተ... አጠቃላይ ሁኔታ ነፀብራቅ መሆናቸውን ይረዳሉ<br>• በተሰጣቸው ወይም እራሳቸው በመረጡት ርእስ አጠር ያለ የልቦለድ ጽሁፍ መጻፍና የጽሁፋቸውን መዋቅር በሚመለከት ለክፍል ጓደኖቻቸው ገለጻ ያደርጋሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ትችት - ግምገማ<br>እውቀት - መገንዘብ<br>እውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ትንተና |
| ሚስጥራዊ አነጋገ ሮችን መገንዘብና መተርጎም በነሱም መደነቅና | • ከዘይቤ ዓይነቶች መካከል ብዙ ጊዜ የሚሠራባቸውንና እውቅ የሆኑትን አገልግሎታቸውንና ልዩ ባሕሪያቸውን ያውቃሉ<br>• በአካባቢያቸው በብዛት የሚሠራባቸውን ዘይቤዎች ሰብስበው በዓይነት በዓይነታቸው መለየት ይችላሉ | እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደበበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| መገልገል-ዘይቤ | • ዘይቤ ከቅኔ የሚለይበትን ዋና ምክንያት ይረዳሉ | እውቀት - መገንዘብ |
| ቅኔ-<u>ምሣሌ</u> ስምና ወርቅ፣ ህብር፣ ምርምር | • የቅኔ ፍቺ ምን እንደሆነና ሁል ጊዜም በግጥም መልክ ብቻ እንደማይቀርብ ይረዳሉ<br>• በህብርና ምርምር ቅኔዎች መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ<br>• በአካባቢያቸው የሰሟቸውንና ከማንበብ ያገኟቸውን ቅኔዎች በመሰብሰብ እንደ ዓይነታቸው በምርምር፣ በኀብር ወዘተ... መለየት ይችላሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ቅኔዎችን በሰምና ወርቅ መሰንጠቅ ይችላሉ<br>• በደረጃው ቀለል ቀለል ያሉ ቅኔዎችን መቀኘት ይችላሉ | እውቀት - መገንዘብ<br>እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ትችት - ማዋሀድ |
| ሥነ ግጥም መግጠም፣ መለ ማመድና ባሕርያ ያቱንም መለየት | • ቤት መምታትና ቤት መድፋት ምን እንደሆነ ተግባራዊ በሆነ መንገድ ይረዳሉ<br>• አንድ ግጥም ከአንድ ማሰሪያ አንቀጽ በወጡ ዘሮች ቤት የመታና ቤት የደፋ እንደሆነ ፀያፍ መሆኑን ያውቃሉ<br>• ግጥም ዜማው መሰበርና አለመሰበሩ እንዴት እንደሚታወቅ ይረዳሉ<br>• የሰበሩና ያልሰበሩ ግጥሞችን መለየት ይችላሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ርእሶች ግጥም መግጠም ይችላሉ | ሽግግር - መረዳት<br>እውቀት - መገንዘብ<br>እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት<br>ትችት - ማዋሀድ |
| የሥነ ግጥቅምና የስድ ንባብ የቅርጽ ልዩነት | • ግጥም በቀለም ቁጥሩ እየተመጠነ የሚዘጋጅ መሆኑንና ስድንባብ ደግሞ እንደ ሀሣቡ ስፋትና እንደ ፀሀፊው ወይም ተናጋሪው ፍላጎት ዐ. ነገሮቹ ሊያጥሩና ሊረዝሙ የሚችሉ መሆናቸውን ይረዳሉ<br>• በስድ ንባብ ውስጥ ቤት መምታት አለመኖሩ ሌላው በግጥምና በስድ ንባብ መካከል ያለ ልዩነት መሆኑን ያውቃሉ<br>• ግጥም በቀለም እየተመጠነ የሚዘጋጅ በመሆኑ እንደ ዓይነቱ ማለት | እውቀት - መገንዘብ<br>እውቀት - መገንዘብ |

-130-

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | የወል፣ ሆያ ሆዬ፣ ሰንጎ መገን ከስድ ንባብ ይበልጥ ጉልህ የሆነ የድምጽ ስልትና የሙዚቃ ቃና ወይም ዜማ ያለው መሆኑን ያውቃሉ<br>• እንደ ስድ ንባብ ሁሉ በግጥም ውስጥ ሰዋስዋዊ ሥርዓቶች ዘወትር ላይጠበቁ መቻላቸውን ያውቃሉ<br>• ስድ ንባብ ሰዋስዋዊ ሕግጋትን የሚጠብቅ ሲሆን ግጥም ግን ይህን እንደሚያሟላ ያውቃሉ | እውቀት - መገንዘብ<br>እውቀት - መገንዘብ<br>እውቀት - መገንዘብ |
| የኢንዴክስ አጠቃቀም | • በደረጃው በኢንዴክስ መገልገል ይችላሉ<br>• ኢንዴክስ የሌላቸው መጻሕፍት ምን ምን እንደሆነ ያውቃሉ<br>• በተለያየ መልክ ማለት በአርእስት፣ በስሞች ኢንዴክሳቸው ከተከፋፈለ መጽሀፎች ሃሣብ ሰብስበው ማምጣት ይችላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>እውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት |
| የአውደ ጥበብ /ኢንሳይክሎፒ ዲያ/ አጠቃቀም | • በአውደ ጥበብና በመዝገበ ቃላት መካከል ስላለው ልዩነት በሚገባ ያውቃሉ<br>• በደረጃቸው በአውደ ጥበብ መገልገል ይችላሉ<br>• አውደ ጥበብ ከመዝገበ ቃላት ቀጥሎ የሚመጣ ዋነኛ መረጃ መጽሀፍ መሆኑን ይገነዘባሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ጽንሰ ሀሣቦችን ዝርዝር መግለጫ በአውደ ጥበብ በመጠቀም ያቀርባሉ | እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት |
| የድርጊቶችና የጊዜ ቅደም ተከተል | • አንድ ለደረጃውየሚመጥን ጽሁፍ ተመልክተው የድርጊቶችን የጊዜ ቅደም ተከተል መገንዘብ ይችላሉ<br>• የተሰጣቸውን ጽሁፍ የድርጊቶች የጊዜ ቅደም ተከተል ትክክለኛነትና ጉድለት መለየት ይችላሉ | ትችት - ትንተና<br>ትችት - ትንተና |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | • የድርጊቶችን ቅደም ተከተል የሚወስነው የድርጊቶቹ አፈጻጸምና የሚፈጸምበት ጊዜ በቅደም ተከተል መሆኑን ይረዳሉ<br>• ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቁ ልዩ ልዩ ድርጊቶችን ማስተካከል ይችላሉ<br>• ጅምር ጽሁፎችን የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተልን በመጠበቅ አሟልተው መጻፍ ይችላሉ<br>• በአንድ በተወሰነ ወቅት የገጠማቸውንና የሰሩትን ነገር በቅደም ተከተል አደራጅው በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ<br>• ቅደም ተከተላዊ አሠራር ያላቸውን ነገሮች እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ማቆም ወይም አፍርሶ እንደገና መሥራት የሚቻል ሲሆን፣ ጊዜን ግን መግታት የማይቻል መሆኑን ይረዳሉ | እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ትችት - ማዋሀድ<br>እውቀት - መገንዘብ |
| የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ል ዩ ነ ት | • ለአንድ ሁኔታ ውጤት የሆነ ነገር ለሌላ ሁኔታ መንስዔ ሊሆን መቻሉን ይረዳሉ<br>• ለደረጃው ከሚመጥኑ መነሻ ሃሣቦች ላይ ሊከተሉ የሚችሉ ውጤቶችን በጽሑፍ ወይም በንግግር ሊገለጹ ይችላሉ<br>• ለደረጃው ከሚመጥን ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ግጭቶችንና የየግጭቶቹን መንስዔዎች ለይተው ማውጣት ይችላሉ<br>• በደረጃቸው የመንስኤና የውጤትን ግንኙነት ማሳየት የሚችሉ ጽሑፎችን ማዘጋጀት ይችላሉ | እውቀት - መገንዘብ<br>ሽግግር - መረዳት<br>ትችት - ትንተና<br>ትችት - ማዋሀድ |
| እመደምደሚያ | • ለደረጃው ከሚመጥኑ ዝርዝር ሀሣቦች መደምደሚያ ሊያወጡ ይችላሉ<br>• አንድ ፀሐፊ ሀሣቦችን በእርግጠኛነት « ነው » በማለት ያቀረበበትን | ሽግግር - መረዳት |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| ወይም ውሣኔ ሀሣብ ላይ መድ ረስ - ሁኔታዎችን ተመልክቶ ነው እያሉ መደምደም | ለደረጃው የሚመጥን ጽሑፍ ተመልክተው እንደዚያ ለማለት ያስቻሉትን ዝርዝር ማስረጃዎች ጥንካሬ ለመገምገም ይችላሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥን ርዕስ ላይ ጥናት አድርገው « ነው » ከሚያሰኝ መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ዝርዝር ሀሣብ ሊያቀርቡ ይችላሉ | ትችት - ግምገማ<br>ትችት - ማዋሀድ |
| ሁኔታዎችን ተመልክቶ «ይሆናል» እያሉ መደምደም | • የወደፊት ሁኔታን በማያጠራጥርና በሚያጠራጥር መልክ የሚናገሩ ለደረጃው የሚመጥኑ ጽሑፎችን መለየት ይችላሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥን ርዕስ ላይ ጥናት አድርገው «ይሆናል» በሚል አካሄድ ጽሑፍ አዘጋጅተው ማቅረብ ይችላሉ<br>• ስለ ወደፊት ሁኔታ በሚያጠራጥርና በማያጠራጥር መልክ የሚገልፁ ጽሑፎችን በመመልከት በልዩነታቸው ላይ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሊከራከሩ ይችላሉ | ትችት - ግምገማ<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ትችት - ትንተና |
| አንድን ነገር ወይም ሁኔታ ከሌላ ወይም ተመሣሣይ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ /አናሎጂ/ | • አንድን በደንብ ያልታወቀ ሀሣብ ለመግለጽ ወይም ለማብራራት ቀደም ሲል ጽንሰ ሀሣቡ ግልጽ በሆነና ተመሳሳዩ በሆነ ነገር አማካይነት ማብራራት እንደሚቻል ይረዳሉ<br>• ለደረጃው በሚመጥኑ ርዕሶች ላይ ተመሳሳይ ሁኔታዎችን በማገናዘብ የሚያብራራ ጽሑፍ ያዘጋጃሉ<br>• የተወሰኑ ዝርዝር ሀሣቦችን በመውሰድ የሚገናዘቡትን በአንድ ላይ መመደብ ይችላሉ<br>• የተወሰኑ ዝርዝር ሀሣቦችን ወስደው ይገናዘቡ ዘንድ በአንድ ላይ የመደቧቸውን ሀሣቦች የሚገናዘቡበትን ሁኔታ በጽሑፍ ወይም በንግግር መግለጽ ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ትችት - ትንተና<br>ትችት - ግምገማ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | • ተመሳሳይ ከሆኑ ርዕሶች ስለ አንድ ውስጣዊ ሁኔታ በዝርዝር የሚገልጽ ጽሑፍ ተመልክተው ስለ ሁለተኛው ርዕስ ሊባሉ የሚችሉትን ዝርዝር ነጥቦች መስጠት ይችላሉ | ትችት - ትንተና |
| የሚያስፈልጉና የማያስፈልጉ ዝርዝር ሀሣቦችን መለየት | • አንድን ለደረጃው የሚመጥን ጽሑፍ ተመልክተው ለይዘቱ መብራራት አስፈላጊ የሆኑትንና ያልሆኑትን ሀሣቦች መለየት ይችላሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ርዕሶችን አስፈላጊ በሆኑ ነጥቦች ብቻ በመግለገል ሊያብራሩ ይችላሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| የማወዳደር ችሎታ | • በቃላት አመራረጥ፣ በአሰካክ፣ በሀሳብ ቅደም ተከተል ወዘተ... ጉድለት ያለበትና የሌለበትን ጽሑፍ ተመልክተው ሁለቱን በማወዳደር ልዩነታቸውን በጽሑፍ ወይም በንግግር ማብራራት ይችላሉ<br>• ተቀራራቢነት ያላቸውን ለደረጃው የሚመጥኑ ሁለት ሀሣቦች በማወዳደር የተሟላ ጽሑፍ ማቅረብ ይችላሉ<br>• ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ተመልክተው ግንኙነታቸውንና ልዩነታቸውን በጽሑፍ ወይም በንግግር መግለጽ ይችላሉ<br>• ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸውን ሀሣቦች መለየት ይችላሉ<br>• ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ያላቸውን ሀሣቦች ልዩነት ይረዳሉ | ትችት - ትንተና<br>ትችት - ማዋሀድ<br>ትችት - ትንተና<br>ትችት - ትንተና<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| በጥሞና በስሜታዊ አስተያየት መካከ ያለው ልዩነት | • የኅብረተሰብ ዕድገትና የጊዜ ሁኔታ የአንድን ነገር ወይም ሀሣብ ሀቅነት እንደሚወስን ይረዳሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ጽሑፎችን በመመርመር በውስጣቸው ያሉትን ሀቆችና የግል አስተያየቶች መለየት ይችላሉ<br>• ሀቅ የሆኑ ጽንሰ ሀሣቦች ለሌሎች ተመሳሳይ ሀሣቦች ትክክለኛነት እንደ ማስረጃ ሊያገለግሉ፣ የግል አስተያየቶች ግን ራሳቸው ማስረጃ ፈላጊዎች | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ትንተና |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | መሆናቸውን ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| ፍሬ ሀሣቦችን በማስታወሻ መያዝ | • ለደረጃው ከሚመጥኑ ጽሑፎች ውስጥ ፍሬ ነገሮችን በመምረጥ ማስታወሻ መያዝ ይችላሉ<br>• አንድን ነገር አዳምጠው የተገነዘቧቸውን ፍሬ ነገሮች በማስታወሻ መያዝ ይችላሉ<br>• ማስታወሻ መያዝ መዘንጋትን ለመከላከል እንደሚረዳ ያውቃሉ<br>• ማስታወሻ የሚያዘው በአጠረና ለፅሐፊው በሚገባ መንገድ መሆኑን ይገነዘባሉ<br>• ማስታወሻ ለሌላም ሰው የሚረዳ መሆኑን ይገነዘባሉ<br>• ማስታወሻ ፍሬ ነገሮችን በሥርአት ተንትኖ የሚያሳይ መሆን እንዳለበት ይገነዘባሉ<br>• ስለ ተደመጠና በአካባቢ ስለታየ ወይም ከንባብ ስለተገኘ ነገር ብቻ ሳይሆን ለጊዜው ትዝ ያለንን ነገር በማስታወሻ የመያዝ ልምድ ማግኘት በእለት ኑሮ ውስጥ ጠቃሚ መሆኑን ይገነዘባሉ | ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| አንድን ርዕስ ጉዳይ በራስ አባባል ማቅረብ | • አንድን ሀሣብ በራስ አባባል ማቅረብ ማለት ፍሬ ነገሮችን ሳይቀንሱ አባባልን ማለት የግል ቋንቋን መጠቀም ማለት መሆኑን ይገነዘባሉ<br>• አንድን ሀሣብ በራስ አባባል ለመግለፅ የበፊቱን የሀሣብ ቅደም ተከተል እንድንጠብቅ እንደሚያስገድድ ይረዳሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ልዩ ልዩ ጽሑፎችንና ሥዕላ ሥዕልን በራሳቸው አባባል ማቅረብ ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - እራስን መግለፅ |
| አንድን ዓይነት ሀሣብ | • አንድን ዓይነት ሀሣብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ ማለት ሀሣቡን መተርጐምና ማብራራት ማለት መሆኑን ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ | • ለክፍሉ ደረጃ የሚመጥኑ ጽሑፎችን በመመልከት ሃሣብ ሳይለውጡ በሌላ አባባል ማለት ይችላሉ<br>• አንድን ሀሣብ በልዩ ልዩ አባባል ለመግለጽ የዐ. ነገሮችን አገባብ መለዋወጥ እንደሚጠቅም ይለማመዳሉ<br>• ለሥዕላ ሥዕል ሀሣብ በተለያየ መንገድ ከሚገለፅባቸው መንገዶች ውስጥ መሆናቸውን ይለማመዳሉ | ተግባቦት - እራስን መግለፅ<br>ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል<br>ሽግግር - መረዳት |
| የማሳጠርና የማስፋፋት ዘዴ | • ጽሑፍን ወይም ንግግርን በማሳጠር ተግባር የተናጋሪውን ወይም የጸሐፊውን አባባል እንዳለ መውሰድ ተገቢ አለመሆኑን ይረዳሉ<br>• በደረጃቸው ጽሑፍን በአንድ ሶስተኛ አሳጥረው ማቅረብ ይችላሉ<br>• ማሳጠር ከማጠቃለል የሚለይባቸውን ነጥቦች ያውቃሉ<br>• ለደረጃው የሚመጥኑ ልዩ ልዩ አጠቃላይ ሀሣቦችን በማስፋፋትና በማብራራት ሊያቀርቡ ይችላሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - አንብቦ መረዳት<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ተግባቦት - እራስን መግለጽ |
| ውጥን ታሪክ መጨረስ | • ለደረጃው የሚመጥን ጅምር ታሪክ በተገቢው መልክ አሟልተው ማዘጋጀት ይችላሉ<br>• አንድን ውጥን ታሪክ ሁለት ሰዎች በተለያየ መንገድ ሊጨርሱት እንደሚችሉና አጨራረሱ ብዙ ጊዜ የሚወስነው ውጥኑን በሚያሟላው ሰው የሀሣብ ስፋትና ጥበት መሆኑን ይረዳሉ<br>• በውጥን ታሪክና በመንደርደሪያ ሀሣብ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ | ተግባቦት - እራስን መግለጽ<br>ዕውቀት - መገንዘብ<br>ዕውቀት - መገንዘብ |
| የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ | • የአንድን ግለሰብ የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ ጠቃሚ የሆኑ የግለሰቡን ሁኔታ የሚገልፁ ዝርዝር ነጥቦች የሚገኙበትን ዘዴ ያውቃሉ<br>• ሰዎች ስለራሳቸው የጻፉቸውን የሕይወት ታሪክ ጽሑፎች በማየት የአጻጻፋቸውን ቴክኒክ ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ<br>ትችት - ትንተና |

| ይዘቶች | የማስተማር መማር ሂደት ተግባራት | ተግባራቱ የተመደቡበት የትምህርት ክፍል |
|---|---|---|
| | • የራስን የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ ምን ምን ማድረግ እንደሚገባ ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| የግለሰብ የሕይወት ታሪክ | • የሕይወት ታሪካቸው በሌሎች ሰዎች የሚጻፍላቸው ሰዎች ምን ዓይነት አስተዋጽኦ ያላቸው እንደሆኑ ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • የግለሰብ የሕይወት ታሪክ አቀራረብ ቴክኒክና ትኩረት ምን እንደሆነ ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • የግለሰቦችን የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ ሀሣብ መሰብሰብ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች ይረዳሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • በቅርብ ከሚያውቋቸውና ተግባራቸው ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ ነው ከሚሏቸው ግለሰቦች መካከል መርጠው የግለሰቦችን የሕይወት ታሪክ በመጻፍ የአዘገጃጀቱን ቴክኒክ ይረዳሉ | ትችት - ማዋሀድ |
| | • በፈጠራና በሀቀኛ ድርሰት መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ | ዕውቀት - መገንዘብ |
| | • ለደረጃው በሚመጥኑ ርዕሶች አጠር አጠር ያሉ የፈጠራ ጽሑፎች መጻፍ ይችላሉ | ትችት - ማዋሀድ |

## ቫሌትና ሪኒ  የቋንቋ ትምህርት አላማዎችንና ሙከራዎችን በእድገት ተከታታይነት ለማደራጀት የተጠቀሙበት የአሠራር ስልት

# የማዳመጥ ክሂል

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| ሜካኒካዊ ክሂሎች - መረዳት (ውስጣዊ) | ድምፆችን ይለያሉ<br><br>• መጥበቅና መላላት የሚያስከትለውን የመልዕክት ልዩነት መረዳታቸውን ይገልጻሉ<br>• በተማሩት መሠረት ነጠላና የብዙ ቁጥር ዐ.ነገሮችን መለየት ይችላሉ | • አንድን ቃል ከመሠረቱት ሆሄያት ውስጥ ተመሳሳዮቹን ለይታችሁ አመልክቱ<br>• አስቀድማችሁ ሲነበቡላችሁ ከምትሰሟቸው ቃላት ጋር ተመሳሳይ ያነባበብ ስልት ያላቸውን ቃላት በኋላ ሲነበቡላችሁ ከምትሰሟቸው ቃላት ውስጥ ለይታችሁ አመልክቱ<br>• ቀጥሎ ሲነበቡላችሁ የምትሰሟቸው ቃላት በማጥበቅና በማላላት የሚያሳዩትን ልዩነት ግለጹ<br>• ቀጥሎ ሲነበቡላችሁ የምትሰሟቸው ዐ.ነገሮች ነጠላ ወይም የብዙ ቁጥር መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ<br>• ሲነበቡላችሁ የምትሰሟቸውን ጥንድ ጥንድ ዐ.ነገሮች አንድነትና ልዩነት በመለየት አመልክቱ |
| ዕውቀት - መገንዘብ (ውስጣዊ) | • በቃል የሚተላለፉ ትእዛዞችን በመረዳት ተግባራዊ ያደርጋሉ | • በገፅ - ላይ የሚገኘውን ምንባብ ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ አንብቡ<br>• ስለምታዩት ሥዕል የተነበበው ምንባብ ትክክል ከሆነ «እ» |

-138-
ክፍል 2

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • ንግግሮችን መረዳታቸውን ይገልጻሉ<br>• በቃል የሚቀርቡላቸውን ገለፃዎች ሃሣብ በመያዝ ከትክክለኛው ሥዕል ጋር ማገናኘት ይችላሉ<br>• የዐ.ነገሮችን አንድነትና ልዩነት መረዳታቸውን ያሳሉ | ትክክል ካልሆነ ደግሞ «ው» በማለት አመልክቱ<br>• ቀጥሎ የሚቀርቡላችሁ ንግግሮች የያዙትን መልዕክት የያዘውን ዐ.ነገር በመምረጥ መልሱ<br>• ሲነበቡላችሁ የምትሰሟቸው ገለፃዎች ከያዙት መልዕክት ጋር የሚስማማ ሃሣብ ያላቸውን ሥዕሎች እየመረጣችሁ አመልክቱ<br>• መጀመሪያ ሲነበቡላችሁ ከምትሰሟቸው ዐ.ነገሮች ጋር የሃሣብ ግንኙነት ያላቸውን ዐ.ነገሮች መርጣችሁ አመልክቱ |
| ሽግግር - መረዳት (ውስጣዊ) | • ስዋስዋዊ ምልክቶችን መረዳታቸውን ይገልጻሉ<br>• ትክክለኛውን ስዋስዋዊ ቅርፅ በመምረጥ ዐ.ነገሮችን እያሟሉ ያሳያሉ<br>• በምንባብ ውስጥ የሚመጡ ቃላትን መልዕክት መረዳታቸውን ያሳያሉ<br>• ሲነበቡላቸው የሚያሰሟቸውን ዐ.ነገሮች መልዕክት መረዳታቸውን ይገልሉ | • ሲነበቡላችሁ በምትሰሙት ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ግሥ በአሁን ወይም በኃላፊ ጊዜ መነገሩን በመለየት ተናገሩ<br>• ዐ.ነገሩን ሙሉ የሚያደርገውን ስዋስዋዊ ቅርፅ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ<br>• ዐ.ነገሩን ሙሉ የሚያደርገውን ቃል የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ<br>• ሲነበብላችሁ በምትሰሙት መመሪያ መሠረት ሥዕል ስላችሁ አቅርቡ<br>• ሲነበብላችሁ የምትሰሙት ዐ.ነገር ከቀዳሚው ዐ.ነገር ጋር በሃሣብ የሚገናኝ ከሆነ «አዎ»፣ ካልሆነ ደግሞ «አይደለም» |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| | • ሲነበቡላቸው የሚሰሟቸውን አንቀጾች ሃሣብ መረዳታቸው ያሳያሉ<br><br>• የሚቀርቡላቸውን ምልልሶች ሃሣብ መረዳት ይችላሉ | በማለት መልሱ<br>• የመጀመሪያውን ዐ.ነገር ሃሣብ የሚቀጥል ሃሣብ የያዘውን ዐ.ነገር በመምረጥ መልሱ<br>• ሲነበቡላችሁ የምትሰሟቸው አንቀጾች የያዙት ሃሣብ ከመጀመሪያው አንቀጽ ሃሣብ ጋር የሚገናኝ ከሆነ «አዎ» ካልሆነ ደግሞ «አይደለም» በማለት መልሱ<br>• ሲነበብላችሁ በምትሰሙት አንቀፅ ሃሣብ መሠረት ዐ.ነገሩን ሙሉ የሚያደርገውን አማራጭ የያዘውን ተራ ቁጥር በመምረጥ መልሱ |
| ተግባቦት አንበቦ መረዳት (ውስጣዊ) | • ሲነበብላቸው የሰሙትን ጽሑፍ አጠቃላይ መልዕክት መረዳታቸውን ይገልጻሉ<br><br>• ፈጠን ባለ ሁኔታ የሚደረጉ ምልልሶችን መልዕክት መረዳት ይችላሉ<br><br>• በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚቀርቡ የዜና | • የሚከተለውን ምንባብ አዳምጣችሁ ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች በቃል ወይም በጽሑፍ መልሱ<br><br>• ሲነበብላችሁ የሰማችሁትን ምንባብ ሃሣብ በቃል ወይም በጽሑፍ ባጭሩ አቅርቡ<br>• ቀጥሎ የምትሰሟቸው ሃሣቦች ቀደም ሲል ካዳመጣችሁት ምልልስ ሃሣብ ጋር የሚገናኙ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለይታችሁ ተናገሩ<br>• በማታው የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | መልዕክቶችን መረዳት መቻላቸውን ያሳያሉ<br><br>• በቃል የሚቀርቡላቸውን ገለፃዎች አብይ ሃሣብ ባጭሩ ማቅረብ ይችላሉ | ፕሮግራም የሚቀርበውን ዓለም አቀፍ ዜና መልዕክት ባጭሩ ጽፋችሁ አምጡ<br>• የምትሰሙትን ገለፃ አብይ ሃሣብ ለይታችሁ ባጭሩ ጽፋችሁ አቅርቡ |
| ትችት - ትንተና (ውስጣዊ) | • በቀጥታ ያልተነገሩ ግን የሚነበቡላቸው ጽሑፎች ከያዙት ሃሣብ ተነስተው ሊባሉ የሚችሉ መልዕክቶችን መረዳታቸውን ያሳያሉ<br><br>• በአንድ ንግግር ወይም ምንባብ ውስጥ ለንግግሩ ወይም ለምንባቡ መልዕክት መጉላት ጠቃሚ ሚና የተጫወቱትን ቃላት፣ ሐረጎች ወይም ዐ.ነገሮች በመለየት ለማመልከት መቻላቸውን ያሳያሉ | • ቀጥሎ የሚነበብላችሁን ምንባብ ወይም የሚቀርብላችሁን ምልልስ በማዳመጥ ከነሱ በኋላ ሲነበቡላችሁ የምትሰሟቸው ዐ.ነገሮች ተጠያቂያዊ በሆነ መንገድ ከምንባቡ ወይም ከምልልሱ መነገሩን በመለየት አመልክቱ<br>• የሚከተለውን ንግግር አዳምጣችሁ የተናጋሪውን ሁኔታ በይበልጥ የሚያመለክተውን ገላጭ አመልክቱ<br>• የሚከተለውን ምንባብ አዳምጣችሁ የፀሐፊውን ስሜት፣ አመለካከት የሚገልጹትን ቃላት፣ ሐረጎች ወይም ዐ.ነገሮች ለይታችሁ አመልክቱ |
| - መመዘን (ውስጣዊ) | • ሲነበብላቸው የሚያዳምጡትን ምንባብ ለመመዘን መቻላቸውን ያሳያሉ | • የሚከተለው ምንባብ በቃል ሲነበብላችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች ከተነበበላችሁ ምንባብ ማስረጃ በመጥቀስ መልሱ<br>• ሲነበብላችሁ ያዳመጣችሁት ምንባብ የቀረበበትን ቋንቋ ብቃት በተመለከተ ያላችሁን አስተያየት ተናገሩ<br>• ሲነበብላችሁ ያዳመጣችሁት ምንባብ የቀረበበት ቋንቋ ምንባቡ ከያዘው ሃሣብ ጋር ያለውን ሥምረት ግለጹ |

# የመናገር ክሂል

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| ሜካኒካዊ ክሂል ግምረት (ውጫዊ) | • ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ምንባብ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ ይችላሉ<br>• በክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት መሠረት በማድረግ ለሚጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት ይችላሉ | • የተሰጣችሁን ምንባብ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡ (የድምጽ አወጣጥ ይተኮርበታል)<br>• የሰዓት ቆጣሪውን ተመልክተህ ሰዓቱን ተናገር |
| ዕውቀት ማስታወስ (ውጫዊ) | • የተሰጣቸውን ምንባብ በጥራት ማንበብ ይችላሉ<br>• ቀደም ሲል የሚያውቋቸውን ስዋስዋዊ ሥርዓቶች ተጠቅመው ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት ይችላሉ<br>• በተመሳሳይ አገባብ ውስጥ ተመሳሳይ ቃላትና አገላለፅ ተጠቅመው ምላሽ መስጠት ይችላሉ<br>• በተመሳሳይ አገባብ ውስጥ ተመሳሳይ ስዋስዋዊ መዋቅሮችን ተጠቅመው ምላሽ መስጠት ይችላሉ<br>• በተማሩት መሠረት ተገቢውን መግቢያ መስጠት ይችላሉ<br>• የተማሩትን መዋቅርና ቃላት ተጠቅመው ንግግር ማቅረብ ይችላሉ | • የተሰጠህን ምንባብ በጥራት አንብብ (በድምጽ አወጣጥ ጥራት፣ በድምፅት፣ በሥርዓተ ነጥብ ላይ ትኩረት ይደረጋል)<br>• በተሰጣቸው ቁልፍ መሠረት ተገቢ የሆነውን ሥርዓት ተጠቅመው ምላሽ ይሰጣሉ (ከመጽሐፍ ለውጡ ጥያቄዎች፣ ከቴፕ ለተወሰዱ ጥያቄዎች)<br>• ከተሰጠው ማብራሪያ፣ ከቀረበው ሥዕል ጋር የተያያዙትን ጥቄዎች ትክክለኛውን ገለጻ በመስጠት ጥያቄዎችን መልሱ<br>• በተሰጣችሁ ቁልፍ መሠረት ትክክለኛውን አጠቃቀም በመከተል ምላሽ ስጡ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| ሽግግር በሥራ ላይ ማዋል (ውጫዊ) | • በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ቀላል የሆኑ ቅየራዎችን ማድረግ ይችላሉ | • በተማራችሁት ያለዋወጥ ሕግ መሠረት ከአንዱ የንግግር ክፍል ወደ ሌላው የንግግር ክፍል በመለወጥ ምላሽ ስጡ (ቅፅሎችን ወደ ስም ወዘተ...)<br>• በተሰጣችሁ መመሪያ መሠረተ የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች በመለወጥ ምላሽ ስጡ:: አስፈላጊውን ለውጥ ሁሉ ማድረጋችሁን አትዘንጉ<br>• አንድ መዋቅርና ቁልፍ ቃል ሲሰጣችሁ ቁልፍ ቃሉን በተሰጣችሁ አገባብ ውስጥ በመጠቀም ምላሽ ስጡ<br>• በተሰጣችሁ አገባብ ውስጥ ቁልፍ ቃሉን በመጨመር መልሱ:: አስፈላጊውን ለውጥ ሁሉ ማድረጋችሁን አትዘንጉ<br>• የሚከተሉትን በራሳችሁ ሁኔታ፣ በተነበበላችሁ ታሪክ፣ በቀረበላችሁ ሥዕል ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች መልሱ<br>• በቀረበላችሁ ውይይት ውስጥ ተሣታፊዎች ሁኑ |
| | • የተለያዩ ሁለት ሰዎችን አስመስለው መጫወት ይችላሉ | • ከናቱ ጋር የሚነጋገር ልጅን አስመስለህ ተጫወት<br>• ከጓደኛህ ጋር የጉዞ ወዘተ... ዕቅድን እንደምታወጣ ሆነህ አስመስለህ ተነጋገር<br>• እንደ ሕፃን ልጅ በማስመሰል ተናገር |
| | • አረፍተ ነገሮችን በተገቢው አጣማሪዎች ማጣመር | • የሚከተሉትን ጥንድ ዐ.ነገሮች በአጣማሪዎች በማጣመር |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | ይችላሉ፡፡ አስፈላጊውንም ለውጥ ያደርጋሉ<br>• የድምጽ አወጣጥ ሕግጋትን በተለያዩ ቃላት ላይ ተግባራዊ ያደርጋሉ<br>• የተማሩትን ቃላትና ስዋስው በአዲስ ሁኔታ ውስጥ መጠቀም ይችላሉ<br>• በተሰጣቸው ቁልፍ መሠረት አዳዲስ ዐ.ነገሮችን መመሥረት ይችላሉ<br>• በምልልስ ውስጥ መሣተፍ ይችላሉ | አንድ ዐ.ነገር አድርጓቸው<br>• ቀጥሎ ከተሰጡት ቃላት ውስጥ በዜማ አወጣጥ የማይመሳሰሉትን ለይታችሁ አውጡ<br>• ቀጥሎ የተሰጡትን ጥንድ ጥንድ ቃላት ሲነበቡ ተመሳሳይ ዜማ ካላቸው «አዎ» ከሌላቸው ደግሞ «አይደለም» በማለት መልሱ<br>• የሚከተሉትን ጥያቃዎች በኃላፊ ጊዜ መልሱ<br>• የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ከአሁን ጊዜ ወደ ኃላፊ ጊዜ ለውጣችሁ ጻፉ |
| ተግባቦት -እራስን መግለጽ (ውጫዊ) | • የራሳቸውን ሃሣብ በራሳቸው አቀራረብ መግለጽ ይችላሉ<br>• በሥዕል ላይ የሚያዩትን እንቅስቃሴና ተግባር ሁሉ በቃል መግለጽ ይችላሉ<br>• ሃሣባቸውን በትክክል ማስተላለፍ ይችላሉ | • ለ - ደቂቃ በራስህ ወይም መምህሩ በሚሰጥህ ርዕስ ላይ ንግግር አድርግ<br>• የምታዩትን የመጽሔት ሥዕላዊ፣ ሥዕዊ ትረካ በቃል ግለጹ<br>• ለጓደኞቻችሁ ቃለ መጠይቅ አቅርቡ<br>• የዕረፍት ጊዜያችሁን እንዴት እንደምታሳልፉ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • ለሚጠይቃቸው ሁሉ አስፈላጊውን መረጃ መስጠት ይችላሉ | • አንድን ሥራ ለምሣሌ ወጥ መሥራት፣ ልብስ ማጠብ ወዘተ... እንዴት እንደምታከናውኑ ተናገሩ<br>• ያነበባችሁትን መጽሐፍ ታሪክ ባጭሩ በክፍል ውስጥ ተናገሩ<br>• ለአንድ የውጭ አገር ዜጋ እንዴት አቅጣጫ እንደምታመለክቱት ተናገሩ<br>• ከጓደኞቻችሁ ጋር በስልክ እንዴት እንደምታወሩ አስመስላችሁ አቅርቡ<br>• ቤተሰቦቻችሁ አንድ ነገር እንድታደርጉ፣ ለምሣሌ ሽር ሽር እንድትሄዱ፣ ውሃ ዋና እንድትሄዱ እንዲፈቅዱላችሁ እንዴት እንደምታሳምኗቸው ተናገሩ<br>• መምህራችሁን አንድ ነገር እንዲያደርጉላችሁ፣ ለምሣሌ የፈተና ጊዜ እንዲያራዝሙላችሁ እንዴት እንደምታሳምኗቸው ተናገሩ |
| ትችት - ማዋሀድ (ውጫዊ) | • ከሚናገሩበት ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆነ አቀራረብ፣ ድምፀት፣ ቃላት፣ ወዘተ... ተጠቅመው መናገር ይችላሉ<br>• የተለያዩ ስሜታዊ ሁኔታዎችን የሚያንፀባርቁ ንግግሮችን ማድረግ ይችላሉ | • ለተለያዩ ሰዎች፣ ለምሣሌ ለአያታችሁ፣ ለጓደኛችሁ፣ ለመምህራችሁ ወዘተ... የምታሳዩአቸውን ትህትና በክፍል ውስጥ አስመስላችሁ አቅርቡ<br>• ሀሣባችሁን ለማስተላለፍ የምትጠቀሙባቸውን የተለያዩ አቀራረቦች፣ ለምሣሌ የቁጣ፣ የፍርሀት ወዘተ... አቀራረቦች ተጠቅማችሁ ተናገሩ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • በተለያዩ የእድሜ ደረጃዎች ከሚገኙ ሰዎች ጋር ሃሣብ መለዋወጥ ይችላሉ<br>• ባጋጣሚ ከሚያገኛቸው ሰዎች ጋር ሰላምታን አድናቆትን መለዋወጥ ይችላሉ | • አደጋ የተከሰተበትን አንድ ፊልም ወይም የተከሰተን አደጋ የሚያሳይ ሥዕል ዓይታችሁ የአደጋውን ምክንያት ግለፁ |

# የማንበብ ክሂል

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | መከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| ሜካኒካዊ ክሂል- መረዳት (ውስጣዊ) | • የሆሄያትን ቅንጅት ይለያሉ<br>• ሲነበቡላቸው የሚሰሟቸውን ዐ.ነገሮች አንድነትና ልዩነት ይለያሉ | • የምትመለከቷቸው ሆሄያት አንድ መሆናቸውን ወይም መለያየታቸውን አመልክቱ<br>• ጥንድ ጥንድ ሆነው የሚነበቡላችሁ ዐ.ነገሮች ተመሳሳይ ከሆኑ « ተ » ልዩነት ካላቸው ደግሞ « ል » በማለት አመልክቱ |
| ዕውቀት - መገንዘብ (ውስጣዊ) | • ተዛማጅነት ያላቸውን ድምፆች ወይም ቃላት በጽሑፍ መልካቸው ይለዩአቸዋል<br>• የተለያዩ የሆሄያት ቅንጅት ኖሯቸው ተመሳሳይ ያነባበብ ሥልት ያላቸውን ቃላት ለይተው ያሳያሉ<br>• ተዛማጅነት ያላቸውን ቃላት መረዳታቸውን ያሳያሉ<br>• ምሣሌያዊ አነጋገሮችን ወይም ቃላትን ከፍቻቸው ጋር ማዛመድ ይችላሉ<br>• የተሰጣቸውን ጽሑፍ ሃሣብ በመረዳት ማንበብ ይችላሉ | • በደብተራችሁ ላይ ከጻፋችኋቸው ቃላት ውስጥ በቃል ከሚነበቡላችሁ ውስጥ ከተገኙ በሥራቸው አስምሩባቸው<br>• ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተለየ የአነባበብ ዜማ ያለውን ቃል ከባችሁ አመልክቱ<br>• ከምታዩት ሥዕል ጋር ተመሳሳይ መልዕክት ያለውን ዐ.ነገር ተራ ቁጥር በመክበብ አመልክቱ<br>• ዐ.ነገሩ የሚያስተላልፈውን ሃሣብ የያዘውን ሥዕል ተራ ቁጥር በመክበብ አመልክቱ<br>• ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላትና ዐ.ነገሮች በሃሣብ ከሚስማሟቸ ሥዕሎች ጋር አዛምዱ<br>• በዐ.ነገሩ ውስጥ ለተሰመረበት ምሳሌያዊ አነጋገር ወይም ቃል ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ፍቺ የሚሆነውን በመምረጥ አዛምዱ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ ሃሣብ ባጭሩ አቅርቡ<br>• ከጋዜጣ ላይ ያነበባችኋቸውን ምንባቦች ርዕሶች ዘርዝሩ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
| --- | --- | --- |
| | • ከምንባብ የወጡ ቃላትን ከትክክለኛ ፍቺቻው ጋር ማገናኘት ይችላሉ<br>• ክፍት ቦታ ያላቸውን ዐ.ነገሮች ከተሰጧቸው አማራጮች ውስጥ በመምረጥ ማሟላት ይችላሉ | |
| ሽግግር - መረዳት (ውስጣዊ) | • በምንባብ ውስጥ የሚመጡ ቃላትን መረዳታቸውን ያሳያሉ<br>• ዐ.ነገሮችን አንብበው መረዳታቸውን ያሳያሉ<br>• መጀመሪያ የተነበበላቸውን ዐ.ነገር የሚቋጨውን ዐ.ነገር መርጠው መቋጨት ይችላሉ<br>• የዐ.ነገሮችን የሃሳብ ግንኙነት መለየት ይችላሉ<br>• የዐ.ነገሮችን ሃሳብ መመርመር ይችላሉ | • በዐ.ነገሩ ውስጥ ከተሰመረባቸው ቃላት ጋር በፍቺ የሚዛመዱትን ቃላት የያዙትን ሆሄያት በመክበብ አመልክቱ<br>• ዐ.ነገሩን ሊያሟላ የሚችለውን ቃል የያዘውን ሆሄ መርጣችሁ መልሱ<br>• የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች በተለየ አቀራረብ ግለጿቸው<br>• ከተዘረዘሩት ዐ.ነገሮች ጋር በሃሳብ የሚገናኙትን ሥዕሎች የያዙትን ተራ ቁጥሮች በመክበብ አመልክቱ<br>• ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ዐ.ነገሩን በተሻለ ሁኔታ ሙሉ የሚያደርገውን በመምረጥ መልሱ<br>• የመጀመሪያውን ዐ.ነገር ሃሳብ በመቀጠል የተጻፈውን ዐ.ነገር የያዘውን ተራ ቁጥር በመክበብ አመልክቱ |
| ተግባቦት - አንብቦ መረዳት (ውስጣዊ) | • ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በመረዳት ያነባሉ | • ባነበባችሁት ጽሑፍ ላይ ተመስርታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄች መልሱ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ ሃሳብ በቃል ወይም በጽሑፍ ባጭሩ አቅርቡ<br>• ካነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ በጣም ጠቃሚ የምትሏቸውን ፃፉ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • የተሰጣቸውን ጽሑፍ በጥራት ማንበብ መቻላቸውን ያሳያሉ<br>• ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመሥርተው ጽሑፉን የሚመለከት ጽሑፍ ጽፈው ማቅረብ ይችላሉ | • በዐ.ነገሮቹ ውስጥ ከሥራቸው የተሰመሩባቸውን ቃላት ወይም አባባሎች ፍቺ ጻፉ<br>• በተሰጣችሁ ጊዜ ውስጥ የቀረበላችሁን ጽሑፍ መልዕክት በመረዳት አንብቡ<br>• የቀረበላችሁን ጽሑፍ በ __ ደቂቃ ውስጥ አንብባችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ<br>• ባነበባችሁት ጽሑፍ ላይ ተመሥርታችሁ የጸሐፊውን ዓላማ፣ የትረካ አንጻር፣ የቋንቋ አመራረጥ ወዘተ... የሚመለከት ጽሑፍ ጽፋችሁ አቅርቡ |
| ትችት - ትንተና (ውስጣዊ) | • የተሰጧቸውን ወይም በግላቸው የሚያነቧቸውን ምንባቦች መተንተን ይችላሉ<br>• የሚያነቡትን ጽሑፍ ውጤታማነት መመዘን ይችላሉ<br>• ያነበቡትን ጽሑፍ መገምገም ይችላሉ<br>• ባነበቡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉና ይፋ ያልሆኑ ሃሣቦችን መረዳታቸውን ይገልጻሉ | • ቀጥሎ የተቀመጠው ሃሣብ ካነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ ተጠያቂያዊ በሆነ መንገድ የተነገረ ከሆነ «ዕውነት» ካልሆነ ደግሞ «ሀሰት» በማለት አመልክቱ<br>• ያነበባችሁት ጽሑፍ ጸሐፊው በጻፈው ሁኔታታ ላይ ያለውን አመለካከት፣ የትረካ አንጻር፣ ያጻጻፍ ይትባህል፣ የጽሑፉን አላማ በመተንተን ጽፋችሁ አቅርቡ:: የምትደርሱበትንም የውሣኔ ሃሣብ ካነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ በመጥቀስ በማስረጃ አስደግፋችሁ አቅርቡ::<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ አደረጃጀት፣ ጸሐፊው አላማውን ለማሳካት ያደረገውን ጥረትና ውጤታማነቱን፣ የቋንቋውን ተገቢነት፣ ያጨራረስና የአንባቢውን ልብ ለመሳብ ያለውን ብቃት በመገምገም ከምትሰጡት የማሻሻያ ሃሣብ ጋር በጽሑፍ አቅርቡ |

# የጽሕፈት ክሂል

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| ሜካኒካዊ ክሂሎች - ማምረት (ውጫዊ) | • በቃል ሲነበብላቸው የሰሙትን ዐ.ነገር መጻፍ ይችላሉ<br>• ምንም ለውጥ ከራሳቸው ሳያደርጉ አንድን ዐ.ነገር ሊተካ የሚችል ሌላ ዐ.ነገርን መጻፍ ይችላሉ | • ሲነበብላችሁ የምትሰሙትን ዐ.ነገር ጻፉ<br>• ከሥራቸው የተሰመረባቸውን ቃላት በቅንፍ ውስጥ በተሰጡት ቃላት እየቀያየራችሁ እንደገና ጻፉ |
| ዕውቀት - ማስታወስ (ውጫዊ) | • በተማሩት መሠረት ትክክለኛውን ስዋስዋዊ ቅርጽ መጻፍ ይችላሉ<br>• በቃል ሲነበብላቸው ተገቢውን ሥርአተ ነጥብ በማስገባት መጻፍ ይችላሉ<br>• በቃል ሲነበብላቸው በተሰጣቸው ክፍት ቦታ ትክክለኛውን ቃል ወይም ስዋስዋዊ ቅርጽ ማስገባት ይችላሉ | • በተሰጣችሁ ክፍት ቦታ ትክክለኛውን ገላጭ በማስገባት ጻፉ<br>• በሚሰጣችሁ መመሪያ መሠረት በቃል ሲነበብላችሁ ተገቢውን ሥርአተ ነጥብ በማስገባት ጻፉ<br>• በቃል ሲነበብላችሁ በትክክል በማዳመጥ ክፍት ቦታዎቹን የሚያሟሉትን ቃላት ወይም ስዋስዋዊ ቅርጾች ከምንባቡ ውስጥ በመውሰድ አሟልታችሁ ጻፉ |
| ሽግግር - በሥራ ላይ ማዋል (ውስጣዊ) | • በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ዐ.ነገሮችን እየለዋወጡ መጻፍ ይችላሉ | • የተዘረዘሩትን ቁልፍ ቃላት ተጠቅማችሁ ዐ.ነገሮቹን እንደገና ጻፉ<br>• የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች ከአሁን ጊዜ ወደ ኃላፊ ጊዜ በመለወጥ ጻፉ<br>• በቅንፍ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላት ዐ.ነገሩ ከተጻፈበት ጊዜ ጋር በማስማማት ጻፉቸው<br>• የሚከተሉትን ምልልሶች ወደ ትረካ፣ ትረካዎቹን ደግሞ ወደ ምልልስ በመለወጥ ጻፉቸው<br>• የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ወደ ጥያቄ በመለወጥ ጻፉቸው<br>• በሚከተሉት ዐ.ነገሮች በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት አስገገ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | መከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት ድርሰት መጻፍ ይችላሉ<br>• ከተሰጣቸው አማራጭ ስዋስዋዊ ቅርጾች ውስጥ በመምረጥ ዐ.ነገሮችን ማሟላት ይችላሉ<br>• በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት የዐ.ነገሮችን ስዋስዋ ቅርጽ በመለወጥ መጻፍ ይችላሉ<br>• በተሰጣቸው ቁልፍ መሠረት አንድን ዐ.ነገር እየለወጡ መጻፍ ይችላሉ:: አስፈላጊውንም ለውስጥ ደርጋሉ | • ከከተሉት ቃላትና ሀረጋት በስዋስዋዊ አገባባቸው ትክክል የሆኑ ዐ.ነገሮችን መሥርቱ<br>• በዐ.ነገሮቹ ውስጥ ያሉትን ስሞች ወደ ተውላጠ ስሞች በመለወጥ እንደገና ጻፉቸው<br>• የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ ዐ.ነገሮች በቅንፍ ውስጥ ያሉትን አጣማሪ ቃላት በመጠቀም እያጣመራችሁ ጻፉቸው<br>• የተማሯቸውን ስዋስዋዊ ቅርጾች በመጠቀም ድርሰት መጻፍ ይችላሉ<br>• ዐ.ነገሩን ሙሉ የሚያደርገውን ስዋስዋዊ ቅርጽ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ<br>• በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን ግሶች ወደ ብዙ ቁጥሮች በመለወጥ እንደገና ጻፉ:: ሌሎችንም አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን ማድረጋችሁን አትዘንጉ |
| ተግባቦት - እራስን መግለጽ (ውጫዊ) | • ሃሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ይችላሉ | • እራሳችሁ በመረጣችሁት ወይም መምህራችሁ በመረጡላችሁ ርዕስ ላይ አንድ አንቀጽ፣ ድርሰት ወይም ምልልስ ጻፉ<br>• ያንድን መጽሔት ሥዕል በጽሑፍ ግለጹ<br>• በቅርብ ወይም በውጭ ለሚገኝ የብዕር ጓደኛችሁ ደብዳቤ ፃፉ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • ወደፊት ሊሰማሩበት ስለሚፈልጉት የሥራ ዓይነት ድርሰት መጻፍ ይችላሉ<br>• ስለ ቅርብ ጓደኞቻቸው በጽሑፍ ገለጻ መስጠት ይችላሉ | • አንድ ነገር፣ ለምሳሌ ወጥ እንዴት እንደሚሠራ በጽሑፍ አስረዱ<br>• ሕይወት ስለሌላቸው ነገሮች፣ ለምሳሌ ስለወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ጥቁር ሰሌዳ ወዘተ... ሰዎች ያላቸውን የጋራ ግንዛቤ የሚያሳይ ዘገባ ጻፉ |
| ትችት - ማዋሀድ (ውጫዊ) | • ተገቢውን ይትባህል፣ ድምጸት፣ ቋንቋ በመጠቀም ሃሳባቸውን ለመግለጽ መቻላቸውን ያሳያሉ<br>• አስተያየት አዘል ዘገባ መጻፍ ይችላሉ | • የሥራ ደብዳቤ ጽፋችሁ አቅርቡ<br>• ትረካ፣ ምልልስ፣ ገለጻ፣ ቀበሌኛ የያዘ አጭር ልቦለድ ጽፋችሁ አቅርቡ<br>• በተወሰነ ነጥብ ላይ ተመርኩዛችሁ ለምሳሌ ስለ ሽምግልና ስለፍቅር፣ ስለ ልጅነት ወዘተ... ዘገባ ጽፋችሁ አቅርበ<br>• ትክክል ነው ብላችሁ ስለተቀበላችሁት ነገር ትክክለኛነት ለማሳየት የሚሞክር ዘገባ ጻፉ<br>• አንድን የቋንቋ ትምህርት ምን ተወዳጅ ሊደርገው እንደሚችል በመግለጽ አስተያየታቸውን በጽሑፍ መስጠት ይችላሉ |

# የሥነ - ጽሑፍ ዕውቀት

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| ሜካኒካዊ ክሂሎች- ማምረት (ውጫዊ) | • ግጥምን በቃላቸው መያዝ ይችላሉ | • የተማራችሁትን ግጥም በማስታወስ ተናገሩ |
| ዕውቀት - መገንዘብ (ውስጣዊ) | • በሚማሩት የክፍል ትምህርት ወይም በሚያነቡት ምንባብ ውስጥ የቀረቡ ዕውነቶችን መገንዘብ ይችላሉ | • የሚከተሉትን ገፀባሕርያት ወይም ጥቅሶች ከሚገኙበት ሥራ ጋር አዛምዱ |
| ዕውቀት ማስታወስ (ውጫዊ) | • ደራሲዎችን፣ ስራዎቻቸውን፣ ገፀባሕርያትን፣ ጥቅሶችን ይለያሉ<br>• የሚያነቧቸው የተለያዩ ሥራዎች ዕውቀት ይኖራቸዋል<br>• ካነበቡት መጽሐፍ ውስጥ የወጣ ጥቅስን የትኛው ገፀባሕርይ እንደተናገረው መለየት ይችላሉ<br>• የሚያነቧቸውን መጽሐፍት ሃሣብ በመረዳት ይገልጻሉ | • የሚከተሉትን መጻሕፍት ደራሲዎች ስም ተናገሩ<br>• የሚከተሉት ገፀባሕርያት ወይም ጥቅሶች የሚገኙበትን መጻሕፍት ጥቀሱ<br>• በክፍል ውስጥ የተወያያችሁባቸውን ሥራዎች አብይ ሃሣብ ግለጹ<br>• የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጻሕፋችሁና በወሰዳችሁት ማስታወሻ ላይ ተመርኩዛችሁ መልሱ<br>• መምህራችሁ ስለ - ሥራ ያላቸውን አስተያየት ግለጹ<br>• በራሳችሁ አባባል በእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ ያለውን ሃሣብ ግለጹ<br>• ከሥሩ የተሠመረበትን የንግግር ክፍል ፍቺ ጻፉ<br>• የትኛው አማራጭ መልስ ዐ.ነገሩን በትክክል . ያሟላል |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለከቱ የሚያከናውኗቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | | • ደራሲዎችንና ሥራዎቻቸውን አዛምዱ |
| ሽግግር - መረዳት (ውጫዊ) | • የንግግር ክፍሎችን፣ ምጣኔዎችን፣ ዜማዎችን፣ ገፀባሕርያትን ይለያሉ<br>• ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያትን ይለያሉ<br>• ዕውቀታቸውን በአዲስ ውስጥ መጠቀም ይችላሉ | • በተሰጣችሁ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ዘይቤዎች፣ ቅኔዎች፣ ምሣሌያዊ ንግግሮች፣ ገጸባሕርያት ወይም ግጥሞች ለይታችሁ አመልክቱ<br>• የሚከተሉትን የግጥም ዓይነቶች ለዩ (ቡሄ በሉ፣ ሰንጎ መገን ወዘተ...)<br>• የሚከተሉትን ግጥሞች ምጣኔ ግለጹ<br>• የሚከተሉትን ግጥሞች ቀለም አመልክቱ |
| ተግባቦት - አንብቦ መረዳት (ውስጣዊ) | • የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም ሥልቶችን መረዳታቸውን ያሳያሉ (ምሣሌ - ዘይቤ፣ ምሣሌያዊ አነጋገር፣ ተረትና ምሣሌ)<br>• የአንድ ዘገባ፣ ጭውውት፣ ረጅም ልቦለድ፣ ወይም ግጥም መልዕክት መረዳታቸውን ይገልጻሉ<br>• ካነበቡት ጽሑፍ ውስጥ መርጠው የጽሑፉን ቅርጽና ይዘት ገምድና ይገልጻሉ<br>• በራሳቸው አባባል የቀረቡላቸውን ግጥሞች ሃሣብ ማብራራት ይችላሉ | • ከሥራቸው የተሠመሩባቸውን የንግግር ዓይነቶች ፍቺ ግለጹ<br>• ባነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ ደራሲው ለማለት ወይም ለማሳካት የፈለገውን ነገር ግለጹ<br>•<br>• |
| ትችት - ትንተና (ውስጣዊ) | ሥነ - ጽሑፋዊ ሥራዎችን ይተነትናሉ | • ባነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ ያለውን መዋቅር፣ ይትባሕል ግጭት፣ ወይም መልዕክት ግለጹ<br>• ባነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ የሴቶችን፣ የፍቅርን፣ የእድልን ሚና ግለጹ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ ለመጻፍ ደራሲው የተጠቀመበት ቋንቋ ዓላማውን ለማሳካት እንዴት እንደረዳው ግለጹ |

| የትምህርት ክፍል | የተማሪው የባሕሪ ለውጥ ዓይነት | ሙከራዎች - ተማሪዎች የባሕሪ ለውጡን ለማሳየት መቻላቸውን በተግባር እንዲያመለክቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት |
|---|---|---|
| | • ያነበቡትን መጽሐፍ መግለጽ ይችላሉ<br>• ያነበቧቸውን ጽሑፎች ጥቅምና ጉዳት መለየት ይችላሉ | • ያዕመ ታሪኩን አወቃቀር አሳዩ<br>• ባነበባችሁት ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ቀጥተኛና ተዛማጅ ፍቺ ግለጹ<br>• ያነበባችሁት ጽሑፍ ፀሐፊ ሕይወትና ሥራ ከጻፈው ጽሑፍ ጋር ያለውን ግንኙነት ግለጹ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ ድምፀት፣ ይትባህል፣ ዜማ ግለጹ |
| -መመዘን (ውስጣዊ) | • ያነበቧቸው መጽሐፍት ሥነ - ጽሑፋዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን በማመልከት ዘገባ መጻፍ ይችላሉ:: ስለሚጽፉትም ዘገባ ከመጽሐፉ ምሣሌ በመጥቀስ ማረጋገጫ ይሰጣሉ<br>• ያነበቡትን መጽሐፍ ሃሣብ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሃሣብ ያቀርባሉ:: ማሳመኛ ሃሣብንም ከራሳቸው ማቅረብ ይችላሉ<br>• ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን ከተለያዩ መስፈርቶች አኳያ መመዘን ይችላሉ | • ያነበባችኋቸዐው መጽሐፍት ሥነ ጽሑፋዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸው በመለየት ዘገባ አቅርቡ:: የምታቀርቡትንም ዘገባ ከመጽሐፉ ምሣሌ በመጥቀስ ማረጋገጫ ስጡ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ የምትቃወሙበትንም ሆነ የምትደግፉበትን ነጥብ በማብራራት ዘገባ አቅርቡ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ ከሥነ ጽሑፋዊ መስፈርቶች አኳያ መዝኑ፤ ውጤቱንም በጽሑፍ አቅርቡ<br>• ያነበባችሁትን ጽሑፍ ከራሳችሁ መስፈርት አኳያ በመመዘን ውጤቱን በጽሑፍ አቅርቡ |

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት ÷ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ::

ስም :- ዮሴፍ ደመቀ ውበቹ

ፊርማ:-

አድራሻ:- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ÷ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ÷ አዲስ አበባ::

የማስረከቢያ ቀን:- ግንቦት 15 / 1989 ዓ. ም.